
መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 41 ጥር 2011 ዓ.ም
ዋጋ 14.99





## የእነ በረከት ፍጻሜ!

### የክሱን ዝርዝር ይዘናል



“የሁሉም የኢትዮጵያዊ ብሔሮች ደም አንድ መሆኑ በዲ.ኤን.ኤ ተረጋግጧል”
ፐ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ



## “የወያኔ ትልቁ ክህደት ሀገሪቱን ወደብ አልባ ማድረጉ ነው”

“አሰብን የቆረቆረው አባቴ ነው”

አቶ ነአምን ዘለቀ

ግዮን


8 የኢሕአዴግ መስቀልያ መንገድ

13 ዘመን በቃላዊ ግጥም ሲዘከር
በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

19 ኢትዮጵያ የዮጎዝላቪያን ውድቀት መድገም የለባትም
ረ/ፕ ወንድማገኝ ታደሰ
ፕ/ር ፍሎሪያን ቢበር

21 የአልጋ ቁራኛ የሆነው ኢኮኖሚያችን
ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

23 ኢሕአዴግ ያከሰረው የዲፕሎማሲው ዓለም
ተስፋዬ ሽብሩ





14

"የወያኔ ትልቁ ክህደት ሀገሪቱን ወደብ አልባ ማድረጉ ነው"

አቶ ነአምን ዘለቀ







3

# የነ በረከት ፍጻሜ !






ቁጥር 40 ዕትም


ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ጥር 25
ይጠብቁን!





9

"የሁሉም የኢትዮጵያዊ ብሔሮች ደም አንድ መሆኑ በዲ.ኤን.ኤ ተረጋግጧል"

ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ

26 ፖለቲካና ሕግ ይራራቁ
ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

28 የሞራል እና የቁስ ልእልና ልሽቀት

# “ሕዝቡ ከጎኔ እስካለ የምፈራው ነገር የለም”

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዳቮስ ሲወዘርላንድ በተካሄደው የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ መድረክ ላይ ጥር 15 ቀን 2011 ዓ.ም ንግግር አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ ያላት አገራዊና ነባራዊ ሁኔታ ለውጭ ኢንቨስትመንት የተመቻቸ በመሆኑ በአፍሪካ ካሉት አገራት መካከል ኢንቨስትመንት ወደ አገር ቤት ከማስገባት ከቀዳሚዎቹ ተርታ ትሰላፋለች ብለዋል፡፡

የውጭ ባለሀብቶችም በኢትዮጵያ ያለውን ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የአገሪቱ ሪፎርም መሰረት ያደረገው “መደመር” በሚለው አገራዊ የለውጥ ፍልስፍና እንደሆነና ትርጉሙ “በጋራ አቅም መፍጠር” ማለት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ የመደመር ፍልስፍና በሶስት ነገሮች ላይ ተመስርቷል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በፖለቲካ በኢኮኖሚ እና በማኅበራ ዘርፎች ዙሪያ ትኩረት ያደረገ ነው ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያ ነፃና ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ ዝግጅት በማድረግ ላይ ነን፡፡ ከዚህ ቀደም አፋኝ የነበሩ ሕጎችን ደረጃ በደረጃ እያሻሻልን እናገኛለን፤ ይህ ሁኔታም በአገራችን ዴሞክራሲ እየተጠናከረ መምጣቱን ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል፡፡



ኢኮኖሚው እንዲያገግም ኢትዮጵያ በርካታ በመንግስት የተያዘ ተቋማት ወደ ግል የማዞር እንቅስቃሴ ላይ ነች፡፡ ይህ ሁኔታ የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዲፋጠንና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትንም ያረጋግጣል በማለት አገሪቱ እያደረገች ያለውን ለውጥ አስረድተዋል፡፡

በአገሪቱ ካሉ መልካም አጋጣሚዎችና እመርታዎች ባሻገር ግን በተለይም ለወጣቶች በቂ የሥራ ዕድል ከመፍጠርና እድገቱን ከማስቀጠል አንፃር አሁንም ፈተናዎች መኖራቸውንም አውስተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ትልቅ ራዕይ ሰንቃ በለውጥ ላይ የምትገኝ አገር መሆኗን የጠቀሱት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ችግሮች ቢኖሩም ሕዝቡ ከጎናቸው እስካለ ድረስ የምፈራው ነገር የለም ብለዋል፡፡ ለውጡም ወደ አገሪቱ ትልቅ ካፒታል ይዞ እንደሚመጣ ጠቁመዋል፡፡

# ለመቄዶንያ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ ተጀመረ

መቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ከ6 ዓመት በፊት የተቋቋመ የእርዳታ ድርጅት ነው፡፡ አሁን በማዕከሉ ውስጥ 2013 አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን ያሉ ሲሆን ድርጅቱን በተለያየ መንገድ የመንግሥት አካላትና ግለሰቦች እየረዱት ይገኛሉ፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት የአዲስ አበባ ክልል መስተዳድር ለድርጅቱ የሚሆን የውስጥ ለውስጥ መንገድ መስራት ጀምሯል፡፡ ይህ መንገድ በግቢ ውስጥ የሚገነባ ሲሆን 3200 ሜትር ካሬ አስፓልት 2700 ሜትር ካሬ የእግር መንገድ መንገድ ወይ በ5.2 ሚልየን ብር ወጪ እየተገነባ እንደሆነና ፕሮጀክቱም በ3 ወር ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ የመንገዶች ባለስልጣናት ዋና ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ሞገስ ለመጽሄታችን ገልፀውልናል፡፡

በተጨማሪም መስተዳድሩ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ፓርክን በድርጅቱ ውስጥ ያሉት አረጋውያን በፈለጉት ጊዜ እየሄዱ እንዲዝናኑበት የፈቀደ ሲሆን ይህ ፓርክ የህዝብ ፓርክ እንደመሆኑ መጠን በግል ንብረትነት ሳይሆን በፈለጉት ጊዜ እንዲዝናኑበት ብቻ ነው የሰጠነው ብለዋል፡፡

መቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ለብዙዎች የተቸገሩ ኢትዮጵያውያን ማረፊያ የሆነ ግብረ ሰናይድ ድርጅት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ድርጅቱ በማእከሉ ውስጥ እየሰራው ያለው ህንፃም እንዲጠናቀቅ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲረባረቡ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ኦዴፓና ኦነግ በሽምጋዮች ተስማሙ

የኦሮሞ አባ ገዳዎች፣ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲን (ኦዴፓ) ከኦነግ ጋር ጥር 14 ቀን 2011 ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ አሸማግለዋል:: ሁለቱ ወገኖች ልዩነቶቻቸውን በሰላም ለመፍታት መስማማታቸው ታውቋል::

የኦነግ (ሸኔ) ሊቀመንበር አቶ ዳውድ ኢብሳ ትጥቃቸው ለኦሮሞ ሕዝብና ለአባ ገዳዎች ማስረከባቸውን ገልፀዋል::አቶ ዳውድ ኢብሳም በኦዴፓና በኦነግ መካከል ጥሩ የሆነ ግንኙነት እንደሌለ ጠቅሰው ይህም መስተካከል እንዳለበት ተናግረዋል:: ወጣቶችም በተፈጠሩ ሀሰተኛ ነገሮች ተገፋፍተው ወደ ሌላ ችግር ሊገቡ እንደቻሉ ተናግረዋል::

በኦሮሞ ባህል ማዕከል በተካሄደው የዕርቀ ሰላማ የኦዴፓ ዋና ፀሃፊ ዶ/ር አለሙ ስሜ በበኩላቸው እኛ የምንፈልገው ሰላምን ማስፈን አንድነትን ማጠናከር እንጂ ከኦነግ ጋር ምንም ችግር እንደሌለባቸው ተናግረዋል::

ጨምረውም ማሰልጠኛ ጣቢያ ያሉ የኦነግ ሰለጣኞች ያሉበት ሁኔታ ማንኛውም ሰው በአካል ተገኝቶ መታዘብ ይችላል ብለዋል:: የኦነጉ ሊቀ መንበር ዳውድ ኢብሳም ሠራዊቱ ከገዥው ፓርቲ ተላቆ የመንግስት እንዲሆን ጠይቀው በአገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን የግንባሩ ፍላጎት መሆኑን ተናግረዋል::

አባገዳዎች በበኩላቸው ሕዝቡ ግጭት እንደማይፈልግ ይልቁንም ኢኮኖሚያዊ መሻሻልና ዕድገት ምኞቱ መሆኑን ጠቅሰዋል:: ግጭትን በማራገብና አንዱ የአንዱን ፓርቲ ለማጣጣል የሚደረግ ሩጫ መቆም እንዳለበት አሳስበዋል:: አባገዳዎች እና ሀደ ሲንቄዎች በመድረክ ላይ በአንድነት በመቆም በፓርቲዎች መካከል ዕርቅ እንዲሰፍንና ሰላም እንዲወርድ ያቀረቡት ጥያቄ በሁሉም አካላት ተቀባይነተ አግኝቷል::

የኦ ኤም ኤን መስራችና አክቲቪስት ጃዋር መሃመድ በበኩሉ ስምምነቱ ያለው በኦነግና በመንግስት መካከል ነው:: በዚህ መሃል እየገቡ የሚበጠብጡት ማስቆም አለብን:: መንግስትም በውስጥ ሆነው ግጭት የሚቀሰቅሱት ላይ እርምጃ መውሰድ አለበት:: አቶ ዳውድ ኢብሳም ወታደሮቻቸው ወደ ካምፕ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል::





# የነ በረከት ፍጻሜ !

## የክሱን ዝርዝር ይዘናል

የጥረት ኮርፖሬት የቦርድ አመራር የነበሩት አቶ በረከት ስምዖን እና የኮርፖሬት ሥራ አስፈፃሚ የነበሩት ታደሠ ካሣ ጥር 14 ቀን 2011 ዓ.ም በሕግ በቁጥጥር ስር ውለዋል:: ሁለቱ ግለሰቦች በቁጥጥር ሥር የዋሉት በመኖሪያ ቤታቸው እንደነበር ይታወቃል:: ከፍተኛ የብአዴን አመራሮች የነበሩት የታሰሩት በኮርፖሬቱ አመራርነታቸው ወቅት፣ ከፍተኛ የሃብት ብክነት በማድረስ ተጠርጥረው መሆኑን የአማራ መገናኛ ብዙኃን ድርጅት ዘግቧል:: ተጠርጣሪዎቹ በተያዙበት ዕለት ረቡዕ ጥር 15 ቀን ወደ ባህር ዳር ተወስደዋል:: የክልሉ ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዝጋለ ገበየሁ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት ከሆነ ተጠርጣሪዎቹ በክልሉ ፍርድ ቤት የሚዳኙ ይሆናል::

በሁለቱ የቀድሞ የብአዴን/ኢህአዴግ ቱባ ባለስልጣናት እስር ላይ አስተያየቱን የሰጠው የፌዴራሉ ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ ግን በአማራ ክልል የጥረት ኮርፖሬት ከፍተኛ አመራሮች የነበሩት "በረከት ስምዖን እና ታደሰ ካሳ" ስለመታሰራቸው የሚያውቀው ነገር እንደሌለ በሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ ዝናቡ ቱኑ አማካይነት አስታውቋል::

### የጥረት ዓላማና ውጤቱ

የቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) በተለያየ መንገድ ያካበተውን ጥሬ ሀብት ሰብስቦ በበጎ አድራጎት (ኢንዶውመንት) ስም "ጥረት ኮርፓሬሽንን" ከመሰረተ ሰንበትበት ብሏል:: ይህ ተቋም ከ20 ሚሊየን ብር በላይ መነሻ ካፒታል ይዞ ነበር የተቋቋመው፤ ድርጅቱ በዋነኝነት የአማራ ክልል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ታቅዶ የተመሰረተ እንደሆነ የብአዴን አመራሮች በመጥቀስ ባለቤትነቱ የአማራ ክልል ሕዝብ መሆኑንም ተናገረው ነበር፣ ሐቁ ከዚህ የራቀ ቢሆንም::

ጥረት የ20 ኩባንያዎች ባለቤት ሲሆን፤ በነዚህ ኩባንያዎች ሥር ለ11ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደፈጠረ ይነገርለታል:: ከ200 ሚሊዮን ብር በላይም ለማኅበራዊ ልማት ዘርፍ እና ለስፖርት አገልግሎት አውሏል የሚል መረጃ ከአመራሮቹ ሲሰነዘር ተደምጧል::

ይህ ግዙፍ ተቋም በሥሩ አቅፎ የያዛቸው 20 ኩባንያዎችን በሶስት ዘርፎች ከፍሎ ማየት ይቻላል:: ዳሽን ቢራ ፋብሪካ ዋነኛውና አንዱ ሲሆን ፣ከፋብሪካው ጋር ትስስር ያላቸው የብቅል፣ የቆርኪ፣ እና ፕላስቲክ ፋብሪካዎችንም በስሩ አካቶ ይዟል::

የትራንስፖርት ኩባንያዎቹ ደግሞ ጥቁር ዓባይ እና በከልቻ ናቸው:: በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ የባህር ዳር እና ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካን ሲያስተዳድር፤ ለእነዚህ ፋብሪካዎች አጋዥ የሆኑ ገንዳ፣ ውሃ፣ ጥጥ ማዳመጫ እና በአጠቃላይ የአምባሰል ንግድ ስራዎች የተሰኘው ድርጅት ባለቤትም ነው:: ከነዚህ ኩባንያዎች በተጨማሪ "አዚና እና ጣና ሞባይልን" የመሳሰሉ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች እና ሌሎች ጥቃቅን ተቋማት በስሩ ያስተዳድራል::

ጥረትን በቦርድ ሊቀመንበርነት ሲመሩ በነበሩት አቶ በረከት ስምዖን እና በወቅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በነበሩት አቶ ታደሰ ካሳ ባወጡት ሪፖርት ላይ "ጥረት ከ11 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል እና 500 ተሽከርካሪዎች አሉት" ብለው ነበር:: የአሁኑ የጥረት ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር አምላኩ አስረስ በበኩላቸው ስለ ጉዳዩ ህዳር 17 ቀን 2011 ዓ.ም ከ"በኩር ጋዜጣ" ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ሁለቱ የቀድሞ የድርጅቱ ኃላፊዎች የሰጡት መረጃ ከእውነት የራቀ የሐሰት መረጃ መሆኑ ይፋ አድርገዋል::

ዶ/ር አምላኩ ጥረት 2.7 ቢሊዮን የባንክ ዕዳ ያለበት መሆኑን ጠቅሰው 2.1 ቢሊዮን ብር የግል ሀብቱ ድርሻ ሲሆን፣ ከ11 ቢሊዮን ውስጥ 4.8 ቢሊዮኑ የጥረት ጥሬ ሀብት አይደለም፤ የጥረት ጥሬ ሀብት 5.1 ቢሊዮን ብር ብቻ መሆኑን ገልፀው ነበር::

በትራንስፖት ዘርፉ በቀድሞዎቹ የድርጅቱ አመራሮች የተገለፀውም መረጃ መሬት ላይ የሌለ ነጭ ውሸት መሆኑን የገለፁት ዶ/ር አምላኩ አምስት መቶ (500) ተሽከርካሪዎች በጥቁር ዓባይ እና በበከልቻ የትራንስፖርት ድርጅቶች በኩል አለ መባሉም ፍፁም ስህተት እንደሆነም ዋና ሥራ አስፈፃሚው አረጋግጠዋል::

ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የተሽከርካሪ ብዛት 348 ብቻ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 48ቱ ብቻ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት እንደሚሰጡ ተናግረዋል:: 300ዎቹ ያረጁና ለጥገና ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጡ መሆናቸውን፣ በአሁኑ ሰዓት ሥራ ላይ እንደማይገኙም ገልፀዋል:: በዚህ የተነሳ ጥረት 70 በመቶ የጭነት አገልግሎት የሚሰጠው በኪራይ (በኮንትራት) በመሆኑ ድርጅቱ በትራንስፖርት ዘርፍ ኪሳራ ውስጥ መግባቱን ተናግረዋል::

"ለጥረት ኪሳራ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የአመራር ብልሹነት ነው:: ጥረት በትርፋማ ስራዎች ላይ ተመስርቶ ገቢውን የማሳደግ ሥራ አልሰራም" የሚሉት ዶ/ር አምላኩ "ከባለሀብቱ ጋር ሽርክና የሚፈጠርበት አግባብም ትክክል አልነበረም" ብለዋል:: በደርጅቱ ውስጥ ዝርክርክነት ሰፍኖ መቆየቱን የጠቆሙት ኃላፊ "ጥረት ካሉት 20 ኩባንያዎች መካከል ሰባቱ በየዓመቱ ይከስራሉ" በማለት የአመራሮቹን ድክመት ያስረዳሉ::

ከሰባቱ ኩባንያዎች በየዓመቱ በአማካይ የ100 ሚሊዮን ብር ኪሳራ እንደሚያጋጥም የገለፁት ሥራ አስፈፃሚው ጥረትን ለኪሳራ የዳረጉ አመራሮች መረጃው ተጣርቶ

ቀጣዩን በገጽ 7 ይመልከቱ

# የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ፈተናዎች

መለክ ቢ..

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን መንበር ከያዙ በኂላ በኢትዮጵያ አጠቃላይ የፖለቲካ አካሄድ ላይ ሰፊ የሚባሉ ለውጦች ታይተዋል። ሰውየው የዚህ ዘመን ትውልድ ጥያቄ የፈጠራቸው መሪ እንደመሆናቸው ስልጣን እንደያዙ መገናኛ ብዙሃንን ያጥለቀለቁ ርዕሶችን በመፍጠር በአብዛኛው ሊባል በሚችል መልኩ ኢህአዴግ በህይወት እያለ ፍጹም ያሳልፋቸዋል ተብለው የማይጠበቁ የፖለቲካ ውሳኔዎችን አሳልፈዋል። እነዚህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሳኔዎች አየር ላይ ባለው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን መሬት ወርዶ በሚገኘው የተራው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ህይወት ላይ ለውጥ ማምጣት የቻሉ በመሆናቸው ገና ከማለዳው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ህዝባዊ ቅቡልነት እንዲረጋገጥ ሰፊ እድል ፈጥሯል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቀዳሚነት የተጠራቀሙ የህዝብ ብሶቶች ሊፈነዱ በተቃረቡበት ወቅት የደረሱ መሪ በመሆናቸው በጋለው ምጣድ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ በማፍሰስ ውጥረቱን ለማርገብ ችለዋል። የተወጠሩ የፖለቲካ ተቃውሞዎች ሊያስከትሉት የሚችሉትን የሃገራዊ ሰላምና ደህንነት መናጋት በጅምር ያስቀሩ ውሳኔዎችን ማሳለፍ የቻሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከኢህአዴግ ባህሪ ፍጹም በተለየ መንገድ ተጉዘው ከመጣው ጥፋት ሃገርን ታድገዋል። ታፍነው የሚፈነዱበትን ቀን ሲቆጥሩ የነበሩ ህዝባዊ ተቃውሞዎች እና ብሶቶች ተብላልተው እንዲናፈሱ ያደረጋቸው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ብልህ አቀራረብና ውጥረቶችን ያረገቡባቸው የፖለቲካ ውሳኔዎቻቸው ናቸው።

የፖለቲካ እስረኞችና ጋዜጠኞች ከእስር መፈታት፣ በፖለቲካ አመለካከታቸው ከሃገር የተሰደዱ ዜጎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደሃገር ቤት መመለስ፣ ከጎረቤት ሃገራት ጋር ሰላም መውረድ፣ ሌሎችም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች በቀላል ግለሰባዊ ፍላጎት የሚመጡ ሳይሆን ታስቦበት ፣ ትርፍና ኪሳራው ተለይቶ በሚሰላ የፖለቲካ ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው። በዚህ ረገድ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ የጉዟቸውን በር ወለል አድርጎ የከፈተላቸውንና በተከታታይ ሊያከናውኑት ላሰቡት ተግባር መንገዱን አሳምሮ የጠረገላቸው በነዚህ ውሳኔዎቻቸው ያገኙት የህዝብ ተቀባይነት ነው።

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ዶ/ር ዐቢይ አህመድ የአዲሱ ትውልድ ትግል ውጤት ናቸው። ስለዚህም ችግሩን በውስጡ ኖረው ያውቁታል። እንዳለመታደል ሆኖ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን ሲመሩ የነበሩ ባለስልጣናት ከታችኛው የህብረሰተብ ክፍል የመጡ ቢሆኑም በዶክተር አብይ ልክ መሬት ያለውን ህዝብ ግን የሚያውቁ አይደሉም። ህዝብ ስለዳቦ ሲያወራ እነርሱ ስለጠፈር ምርምር በማውራት መሪና ተመሪ ተላልፈዋል ተብለውም ሲተቹ ኖረዋል። ቋንቋቸው ከላይ የሚንሳፈፍ እንጂ ህዝብ በሚገባው እና የኔ ብሎ በሚያስበው ደረጃ ዝቅ ብሎ የሚሰማ ባለመሆኑ በማጠቃለያው ኢህአዴግ እና ህዝብ እንደባቢሎን ህዝቦች ሳይግባቡ የቀሩበትም ምክንያት ይኸው ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ከፊታቸው ያለውን መሪ አድርጎ ያስቀመጣቸውን ኢህአዴግን ሳይሆን ከጀርባቸው የቆመውን ለለውጥ የተነሳ ሃይል ተግነው ከፓርቲያቸው ባህሪ ማፈንገጣቸውም ይህንን ያመለግባባት በመግባባት ለመቀየር በማሰብ ነው።በርግጥም በቀድሞ "እኛ ብቻ" በሚሉ የፓርቲያቸው ጎምቱዎች ለጥላቻ ቢዳረጉም በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አንጀት ውስጥ መቀመጫቸውን በመጎዝጎዛቸው አሁን አሁን እርሳቸውን በክፉ የተናገረ ሁሉ የሃገር ጥፋት አቀጣጣይ እስኪመስል ድረስ ውግዘቱ እየደረሰበት ነው።

ዶክተር ዐቢይ በአንደበተ ርቱዕ አቀራረባቸው አብሮነትን እና ፍቅርን ከመስበካቸው ባሻገር በተገኘው መድረክ ሁሉ ከዘር ጥበት ወጥቶ ኢትዮጵያን ከፍ የማድረግ አዝማሚያ እንዲጎለብት መጣራቸው ከየትኛውም እርምጃቸው የላቀ ህዝባዊ ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል። ይህ ሰፊ የህዝብ ድጋፍ ኢህአዴግ እንደድርጅት ሰብስቤዋለሁ ከሚለው አራት ሚሊዮን አባል እና ሃያ ሚሊዮን ምናምን ደጋፊ ጋር ሲተያይ መሪ ከፓርቲ የተሻለ የህዝብ ተቀባይነት እንዳለው ማመላከቻ ሆኗል የሚሉ ብዙዎች ናቸው።ዶክተር ዐቢይ በፍቅር እና በይቅርታ ብቻ ህዝብና ሃገር እየመሩ አስተዳደራቸው እስካሁን በጉልህ ሃይል ሞክሮ በህግ ሰጥ ለጥ ማድረግ እንኳን ሳይጀምር የኢህአዴግ ወታደራዊ አገዛዝ የከረቸመውን በር መገንጠል ችለዋል።

ይህንን ስንል ግን ዶክተር ዐቢይ በርግጥም ምሉዕ በኩለሄ የሆነ አስተዳደር ይዘው ህዝቡ በሰላምና በደስታ ህይወቱን እየመራ ፣ ሀገርም ያለችግር እየተጓዘች ነወይ ብለን ስንጠይቅ ምላሹ ቅር ሊያሰኘን ይዳዳዋል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የለውጥ መንገድ በታሰበው መልኩ ተጠቃልሎ በስኬት ብቻ የተሞላ ነው ማለት አንችልም፣ እንዳለመታደል።

በየቦታው ብሄር ተኮርና ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ▶

ተባብሰዋል፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ከመኖሪያ ቀዬው ተሰድዷል፣ የመንጋ ፍርድ ፣ ዝርፊያና ማንአለብኝነት ተባብሷል፣ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶችም ደርሰዋል። በአጠቃላይ የሃገር ሰላም ደፍርሷል።እንደውም እያንዳንዱ እርምጃ ከበስተኋላው የፈጠራቸው ቅሬታዎች የርሳቸውን መንገድ ለመዝጋት ድንጋይ ለሚኮለኩሉ ሰዎች መነሻ እየሆነ ዛሬ ለዶክተር ዐቢይ አስተዳደር እንደስጋት መጠቀስ የሚችሉ ፈተናዎች ከፊት ተደቅነዋል። ይህ ጽሁፍ በእነዚህ ፈተናም ይባሉ እንቅፋት፣ ችግርም ይባሉ ተግዳሮት ፣ ብቻ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አካሄድ ላይ ሊደነቀሩ ይችላሉ ተብለው በሚታሰቡ ችግሮች ላይ ያተኩራል።

## “የተጨባጭ ለውጥ” ፍላጎቶች

በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባደረጉት ንግግር ያሉተን እዚህ ላይ ማስታወስ ላነሳነው አንደኛው እንቅፋት ማብራሪያ ሜዳ ይፈጥርልናል። “ተግባር ከቃል ይጀምራል። ቃል በራሱ የተግባር መጀመሪያም ነው። ያለቃል ተግባር ያለተግባር ውጤት የለም” ብለው ነበር። በርግጥም የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር በመጀመሪያው ቀን ህዝቡን የተዋወቀው በቃል ነው። በሲመተ ስነስርዓታቸው ላይ ያደረጉት አራት ገጽ ንግግር ሙሉ ቃል ነው። አንዳንዶች እንደሚሉት የጠቅላይ ሚኒስትሩን የወደፊት ዓላማ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ሮድ ማፕ ነው። ይህ በቃል የተሞላ ንግግር ስለመደመር እና አብሮ ስለመኖር፣ በሃገር ውስጥ ሰላም ፍቅርና ይቅር ባይነት ማንገስ፣በዚህም ያለፉ ቁስሎችን ጠግኖ አዳዲስ ቁስሎች እንዳይፈጠሩ ማድረግ፣ ከሁሉ በላይ ሁሉን አቀፍ ሰላም መፍጠር ላይ ያጠነጠኑ ቃሎች የታጨቁበት ነበር። አሁን የተነሳው ጥያቄ ለውጡ ቃል እንዲ የሚጨበጥ ተግባር አልሆነም የሚል ነው።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲስ የፖለቲካ አቅጣጫ በተለያዩ አካላት ግምገማ ለውጥ ወይስ ሽግግር ወደሚል የሁለት ሃሳቦች ተርጉም ተጉዟል። ለውጥ ሲባል ኢህአዴግ እንደፓርቲ ራሱን አድሶ መቅረቡ? ወይስ አዲስ ሃገር ገዢ ፓርቲ መምጣቱ፣ ወይስ ኢህአዴግ በርዮቱ እና በመዋቅሩ ቆሞ ሃገር መምራቱ ወይስ አዲስ አመራር ቀይሮ በድሮ ፓርቲ መቀጠሉ በሚሉት ላይ ልዩነቶች ተነስተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሜሪካ በሄዱበት ወቅት ኢህአዴግ ሃገር እንዲመራ አንፈልግም ያሉ አካላት እስከ ምርጫ 2012 ድረስ የሚያገለግል ብሄራዊ የሽግግር መንግስት እንመስርት ብለው ሲጠይቋቸው “እኔ ራሴ አሸጋግራችኋለሁ” ብለው ቃል በመግባት ያመጧቸው መሆኑን በማስታወስ አንዳንዶች ዶክተር ዐቢይ እያሸጋገሩ እንጂ ለውጥ እየመሩ አይደለም ሲሉ ይሞግታሉ።

በዚህ እሳቤ ብዙዎች የጠቅላይ ሚኒስተሩ አስተዳደር ቃል ላይ አትኩሮ የምንጨብጠው ለውጥ አላደለንም ብለው የተነገሩት ሁሉ መሬት እንዲወርዱ ጠይቀዋል። በአንድ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትክክለኛ ለውጥ እየመሩ ነው ብለው የሚከራከሩ አካላት ይህንን ለውጥ መቀበል ያልቻሉ የማስተዋል ችግር ያለባቸው ናቸው የሚል የግለ ሃሳብ ልዕልና ጥያቄ ያነሳሉ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተመዘገቡት የለውጥ መንገዶች በሴራ እና በመንግስት ግልበጣ አለያም በጦር ሃይል እና በአብዮት ለውጥ መምጣት አለበት ወይ ብለውም ይጠይቃሉ።በሰላማዊ መንገድ ደም ሳይፋሰስ የመጣ ለውጥ ዛሬ በተለያዩ ግጭቶች ደም እንደጎርፍ እንዲፈስስ ምክንያት ካልሆነ አስቀድሞም የተጨበጠ ለውጥ አልነበረም የሚሉት ወገኖች ደግሞ ሃገሪቱ በትክክለኛ እና በተለወጠ የህግ አስተዳደር እንዲሁም በተቀየረ ጦር ሃይል እና የፍትህ አካላት ውስጥ ካልሆነች በቀር የሰላም መደፍረስ እያለ ለውጥ ተመዝግቧል ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ይከብዳል ባዮች ናቸው።

ያም ይሁን ይህ ክርክሮቹ እንዳሉ ሆነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግን በሃገር አቀፍ ደረጃ በጉልህ የኢትዮጵያን ቅርጽ ያስተካከለ አስተሳሰብ በመፍጠር ለውጡ ከመሬትም አልፎ በኢትዮጵያውያን አተሳሰብ ውስጥ እንዲሰርጽ ማድርጋቸውን እንደአንድ ታላቅ ለውጥ ያዩታል። በተለይም ለዘመናት ተዘንግቶ በኖረው ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ስም የማሉ ኢትዮጵያውያን ይህንን የሚወዱትን ኢትዮጵያ የሚል ስም ተደጋግሞ ሲነገር ማድመጣቸው ብቻውን ለውጥ ነው ብለው እርካታቸውን ገልጸዋል። “ኢትዮጵያ ሲባል ሰምቼ ልሙት” ያሉ ሁሉ ባለፉት 27 ዓመታት ሲመኙት የኖሩት የኢትዮያዊነት ትርክት ቦታውን ይዞ ብሄርተኝነት ሲንኳሰስ መስማት በመቻላቸው ብቻ ጠግበዋል። ቤት ከተሰራ የሚኖርበትን መፍጠር ጊዜ ቢወስድም የሚያቅት ተግባር አይደለም ይላሉ ከጣሊያን ትርክት የሰሙትን ተውሰው። “ጣሊያኖች በቅድሚያ ጣሊያንን ፈጠሩ፣ ከዚያም ጣልያውያንን ፈጠሩ”።

በዋናነት የተጨበጡ ለውጦች ፍላጎት ያላቸው ወገኖች የሃገሪቱ የፖለቲካ መስመር ተለይቶ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ በተሻለ ሊበራሊዝምም ይሁን ምን ሃገርን ከሌሎች ዘመናዊ ሃገራት ጋር ሊቀላቀል የሚችልና በአለም ቋንቋ የሚያግባባ ዜሮ እልህ የሆነ ዓለም አቀፍ ርዕዮተ አለም ውስጥ ሆነን ማየት የሚሹ አሉ። በዋናነት ይህንን የሚሹት ዜጎች ዘንድ ያለው ጥያቄ ሃገር ተለውጣለች ከተባለ በግልጽ ህገመንግስቱ ተቀይሮ፣ የአስተዳደር ስርዓቱ ተለይቶ ታውቆ ፣ ያለፉ ከፋፋይ ስህተቶችን ያመጡ የፖለቲካ አካሄዶች ታርመው እና ህዝብን ወደ አንድ መሰብሰብ በሚያስችል አካሄድ ተቀይረው ማየት ነው። ይህ ደግሞ በርግጥም መሆን ያለበት ሲሆን ነገር ግን ጊዜ በአንድ ጀምበር የሚከናወን ባለመሆኑ አሁኑኑ ከቃል አልፎ የምንጨብጠው ለውጥ አምጡ ማለት ፖለቲካን አለማወቅ ነው የሚሉም ብዙዎች ናቸው።

ከዚህ ባሻገር ግን ዶክተር ዐቢይ ከሃገር ውስጥ ፖለቲካ ባሻገር በጎረቤት ሃገራት ግንኙነት፣ በኢኮኖሚ፣በምርጫና መሰል ዘርፎች የነካኳቸውና በጅምር ላይ ያሉ የለውጥ ስራዎች ያስመዘገቡት ውጤት እንዳለ ሆኖ ፍሬያቸው በይፋ እስኪደርስ ድረስ በራሳቸው ያልነበሩ ክስተቶች ስለሆኑ ለውጥ ናቸው ብሎ መጥቀስ አያዳግትም። ዛሬ ሃገሪቱ የተጨባጭ ለውጥ ሳይሆን ቃል የመግባት ደረጃ ላይ ናት የሚሉ በቅን ልቦና “ከመፍረዳችን በፊት በእውን የሚተገበረውን እንጠብቅ” ወደሚል ስሜት ያሸጋገራቸውም ይኸው የተጨባጭ ለውጥ እምነት ነው።

ከዚህ ባሻገር ግን ባለፉት ዐስር ወራት ውስጥ ኢትዮጲያ ዉስጥ ሊታሰብ የሚችል የሚይመሰል ፣ በቅርቡ ይሆናል ተብሎ ያልተጠበቀም ተስፋ ሰጭ እርምጃ በመንግስት ተወስደዋል:: ከነዚህም ዉስጥ የፖለቲካ እስረኞች መፈታት፣በትጥቅ ትግል መንግስትን ለማንበረከክ ሲሰሩ የነበሩ ቡድኖች ወደ አገር መግባት፣አፋኝ ህጎችን የመከለስ ስራ መጀመር ፣የመገናኛ ብዙሃን ምህዳሩን መክፈት፣የሰብዓዊ መብት ጥሰትና በሙስና የተጠረጠሩትን ለፍርድ ማቅረብ ወዘተ እንደአንድ ለውጥ ሲታይ የለውጥ እርምጃዎች ናቸው ብሎ መናገር አይገድም::

በተለያዩ አገራት ውስጥ የተካሄዱ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የሚደረጉ መንግስታዊ ለዉጦችን ለማጽናት እንዲሁም የተረጋጋ እና ዲሞክራሲያዊ ስራት ለማስፈን የሽግግር ወቅት ሰራዎች ወሳኝ ናቸው :: ኢትዮጲያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት በስልጣን ላይ ያለው እና ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ የሚመራው የለውጡ መሪ መንግስት በህዝባዊ ተቃውሞ እና ከፍተኛ ጫና እንዲሁም በገዥው ግንባር ውስጥ በተካሄደው የውስጥ ትግል የተወለደ መሆኑ ለለውጡ መነሻ መሆኑ ከግንዛቤ መግባት ያለበት ጉዳይ ነው::

## የመንግስት ማዕካላዊ ወጥነት ጥያቄዎች

ማዕከላዊ መንግስት ወጥነት ይኑረው የሚሉ ጥያቄዎች ተደጋግመው እየተደመጡ ነው። በርግጥም የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር የሚጎድለው የሚመስለው አንድ ነገር የማዕከላዊ መንግስቱ ሃይል የላላ መምሰሉ ላይ ነው። ማዕከላዊ መንግስት በአፈጣጠሩ የክልሎችን የበላይ ጠርናፊነት አረጋግጦ ሃገርን በቁመና መምራት በሚያስችል የህግ፣ የሃይል እና የመግባባት ስራ ላይ ጠንካራ ብቃት ያለው ማለት ነው። በአሁኑ ጊዜ ያለው የማዕከላዊ መንግስት አቋም የላላ እና በአብዛኛው ክልሎች በፈለጉት መንገድ የሚያሽከረክሩት አይነት ነው። ዶክተር አብይ የክልል ሳይሆን የማዕከላዊ መንግስት መሪ እንደመሆናቸው ሃይል እና የህዝብ ፍቃድ አስፈጻሚነትን ጠቅልሎ በያዘ መዋቅር ውስጥ ናቸው። ይህንን መዋቅር ግን በሚገባው መጠን መጠቀም አልቻሉም ወይም ከአቅም በታች እየተጠቀሙበት ነው እያሉ ነው ብዙዎች።

ለዚህ ሃሳብ ማጠናከሪያ ተደርገው ከሚቀርቡት ምሳሌዎች አንዱ ደግሞ የትግራይ ክልል ነው። አሁን የህወሃት ዳግም ምጽዓት ናፋቂዎች የከተሙበት የትግራይ ክልል ሃገርን የበደሉ ወንጀል ፈጻሚ ሰዎችን በስሩ አቅፎ ከፌዴራል መንግስቱ ጋር እንደ አንድ ሃገር እየተደራደረ እና እየተነጋገረ ሲታይ በርግጥም ማዕከላዊ መንግስትነት ማለት ምን ማለት ይሆን የሚል ጥያቄ ጭሯል። አንደ ማዕከላዊ መንግስት በሃገር ላይ ወንጀል ፈጽመው የሚፈለጉ አካላትን በመብቱ ተጠቅሞ በቁጥጥር ስር ሊያውል የሚችልበት አወቃቀር እያለው ነገር ግን (ምናልባትም ውጥረትን ባለመፈለግ) የላላ አቋም በመያዙ ምክንያት ሃይሉ የተዳከመ መስሎ እንዲታይ ምክንያት ሆኗል። አስተያየት ሰጪዎች የዶክተር ዐቢይ የማዕከላዊ መንግስት ወጥነት የሌለው ነው ብለው የሚተቹት በትግራይ ክልል ላይ ያለው አቋም ምንድነው ከሚል ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ሃይሉን በሌሎች ክልሎች ሲያሳይ ነበር ከሚል ማነጻጸሪያ ጋር ነው።

በጋምቤላ ክልል የአስተዳደር መዋቅሩ በሽኩቻ ሳቢያ ወደ ብሄር ተኮር ግጭት ሊያመራ የሚችል አጀንዳ መምዘዝ ሲጀምር ቤተመንግስት ድረስ ጠርተው በማደራደርና አመራሮቹን ከስልጣን እንዲወርዱ በማድረግ ጉዳዩን በአብዛኛው ችግር እንዳይሆን መፍታት መቻላቸው፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝብን የሚያምስ አጀንዳ ይዘዋል ባሏቸው አመራሮች ላይ እርምጃ መውሰዳቸው፣ በደቡብ ክልል አመራሮቹ በፍቃዳቸው ስራ እንዲለቁ ማዘዛቸውና ይህም ተግባራዊ መሆኑ ፣ ከዚህ በተለየም በሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት የነበሩትን አብዲ መሃመድ በቁጥጥር ስር አውለው እስር ቤት መጨመራቸውና ክልሉን ከለውጡ ጋር ለሚጓዙት አሳልፈው መስጠታቸው ወዘተ ሲታይ ይህ የፌዴራል

መንግስት ጥርስ ወጥነት ኖሮት በትግራይ ክልል ላይ ተግባራዊ ሊሆን ያልቻለበት ምክንያት ምንድነው ወደሚል ጥያቄ ወስዶትል።በየትኛውም ጉዳይ ይሁን ህዝብ እንደህዝብ የሚሸበርበት እና ፍርሃትና ‘መጡልህ’ ስሜት ውስጥ የማይግባበት አካሄድን ተከትሎ የትግራይን ክልልም ወደ ትክክለኛው የፌዴራል እዝ ማስገባትና ነገር ሳይጠጥር በፊት በውሃው ማስተካከል ከማዕከላዊ መንግስቱ የሚጠበቅ ተባር ነው ብለው የሚመክሩም ብዙ ናቸው።

## የተደራጀ ተቃዋሚ እና ያልተደራጀ ደጋፊ

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ግጭት አለ። ግጭት በባህሪው የሚኖር ቢሆንም በዚህ መጠን ኢትይጵያ ውስጥ አንድነት የጠፋበት እና ክልላዊ አካሄድ ሰፍኖ በብሄር ህዝብ የተቆራቆሰበት አጋጣሚ ግን አልታየም።

እስካሁን ግጭት አለመኖሩ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ሰፍኖ ስለመቆየቱ ዋስትና አይሆንም። ይልቅስ ግጭቶች ሳይታወቁ ተቀምጠው አመቺ የመተንፈሻ ጊዜ ሲያገኙ ናኙ የሚለው ሃሳብ የበለጠ ይገልጸዋል።

ግጭት የሚነሳው በሁለት ፅንፎች መካከል ነው ተብሎ ይታሰባል ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚመሩት የለውጥ መንፈስ ደጋፊዎች እና የለውጥ መንፈሱን በሚቃወሙት መካከል። የለውጡ መንፈስ ደጋፊዎች ብዙኃን ቢሆኑም በኢኮኖሚ እና በመዋቅር ገና አልተደራጁም። የለውጡ መንፈስ ተቃዋሚዎች የድርጅት መዋቅሩ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ አቅሙም አላቸው። ለዚህም ይመስላል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በገደምዳሜም ቢሆን ‘ለውጡን ጠብቁ’ የሚል መልዕክት በተደጋጋሚ ጊዜ ሲያስተላልፉ የተሰሙት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ይህንን የሃገር ሃብት ዘርፎ ገንዘብ አጥቦም ይሁን በህገወጥ ኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ ተንሰራፍቶ የገንዘብ አቅም ያዳበረው ሃይል እየተቃወማቸው ነው። ይህ ሃይል በጥቂት ሰዎች እጅ ስር የሆነ የሌባ ቡድን ነው። አሁን በአንድ ክልል ውስጥ መሽጎ ሃገርን እንደጠላት እያየ የለውጥ እንቅፋት መሆንን ህዝብ የማዳን ተልዕኮ እያስመሰለ ሴራውን ሲሸርብ በአንጻሩ ግን በቅን ኢትዮጵያዊነትና በተስፋ ዶክተር አብይን የሚደግፈው ቡድን ግን ይህን ያህል የተደራጀ አቅም የለውም። በመዋቅር ወስጥ ተሰግስጎ ለውጥ ላይ አይኑን የጣለውና የሚያደናቅፍበትን መንገድ የሚፈልገው የተደራጀ ሃይል አሁንም ሃገር የመተንኮስ ስራውን እየሰራ ነው። ለዚህም ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ በቤኒሻንጉል፣ በጉጂ፣በሶማሌ፣ በደቡብ እና በመሳሰሉት የሃገሪቱ አካባቢዎች በሙሉ በገንዘብ እየደገፈ፣ በመሳሪያ እያስታጠቀ እና በሃሳብ እየመረዘ ሰላምን ሲያባርር እና ግጭትን ሲቆሰቁስ ታይቷል።

የዶክተር አብይ አንዱ የለውጥ ፈተና ይህ ሃይል ነው። ጠቅልሎ ለማስወገድ ኢኮኖሚውን ከእጁ ማላቀቅ እና የመንግስት ተቋማትንም ማፅዳት ቀዳሚ ስራ ይሆናል። የደህንነት መስሪያ ቤቱ ሆነው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመግደል ያሴሩትን ለማጽዳት በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የተሰራውን የማጥራት ስራ እዚህ ላይ ያስታውሷል።

በአንጻሩ የለውጡ አካል የሚባሉት በአብዛኛው ከተቋም ይልቅ ግለሰቦች ናቸው። ይህንን የግለሰብ ድጋፍ 100 ሚሊዮን ላላት አገር የሚያስኬድ አይደለም። ለውጡን ከግለሰብነት ወደ ተቋም ማውረድ ይጠበቃል የሚባለው ለዚህ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማሪም እንዳሉት ለውጡን ስንደግፍ የምናየው ለውጥ ህጋዊ ዋስትና ያለው እንዲሆንና በተለይም በእንዳንዱ ተቋማት ላይ ለውጡ መዳረስና መሸተት እንዳለበት ባለመዘንጋት ነው ። ይህ ለውጥ ግለሰቦች ጋር ብቻ ለዚያውም ጠንካራ አቅም በሌለው ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ ከቆየ የመታጠፍ እድል እንዳያሰጋውም ፣ ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለለትን ለውጥ እንዳናጣውም ፍራቻ አለን የሚሉ አሉ።

## የአምባገነንነት ስጋቶች

የዶክተር ዐቢይን መንግስት ከሚያሰጉት ነገሮች አንዱ የመንግስት አምባገነን የመሆን እድል ነው። አምባገነንነት ከብቸኛው ዋስትናው ‘ቁጥጥርና ሚዛን’ (check and balance) ከተለየ መንግስት ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ይሄዳል። ይህ የሰላም ጊዜ ሃሳብ ነው። ነገር ገን ከሰላሙ ጊዜ በራቀ እንዲህ ባለ የግጭት ዘመን ላይ መንግስት ህግ ለማስከበር በሚወስዳቸው የጠመንጃ እርምጃዎች አምባገነን የመሆን እድሉ የሰፋ ነው። ህግን ለማስከበር ሀግ የመኖሩ ህልውና ጥያቄ ውስጥ ሲገባ ሰርዓትን ወደ ቀደመ ስፍራው የሚመልሰው ጠመንጃ ነው ብለው በሚያስቡት ዘንድ መንግስት በቀላል እርምጃ አምባገነን የመሆን እድል አለው። ይህንን ስርዓት እንጂ አንድ መሪ ብቻውን ታግሎ ሊያስቀረው የሚችል አይደለም።

ዛሬ ለስላሳ የሆኑ መሪዎች ዓላማቸው ሊደናቀፍ ሲል ወደ ጠንካራ እና ጨካኝነት መለወጣቸው በታሪክ የነበረ ሃቅ ነው። ከዓለማችን የምንግዜም አምባገነኖች አንዱ የሆነው ኢዲ አሚን በሥልጣን አፍላው ዘመን በምዕራባውያን ሚዲያዎች ሳይቀር የተንቆለጳጰሰ ሰው ነበር። ሰውን አምባገነን የሚያደርገው ተቋማዊ ነጻነት አለመኖሩ እና የግለሰቦች ሥልጣን አለመገደቡ ነው ይላል ሳይንሱ። አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የምናየውን ለውጥ ወደ አምባገነን የሚመሩት ነገሮች አሉ ወይ ለሚለዉ ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ ከወር በፊት ከመምህራን ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ባነሱት ሃሳብ መቋጨት ይቻላል።

‹‹ የኢትዮጲያ መንግስት አምባገነን ለመሆነን ጫፍ ላይ ያለ መንግስት ነው›› ። በአሁኑ ወቅት በአንንዳንድ የአገሪቱ ስፍራዎች ላይ የሚታየውን ግጭት የሚያስነሱ አካላት እንዲቆጠቡ ያሳሰቡበትን ይህንን ንግግር ቆም ብሎ ላሰበው የሰላም መንግስት አማራጭ ሲያጣ ሃይል ተጠቅሞ ሃገርን ለማዳን ከመስራት ወደኋላ አንደማይል ነው።

## የማንአለብኝ እና አሻጥር መንገዶች

ይህን ተስፋ ሰጭ ጅማሮ ሊያጨልሙ የሚችሉ በዝርዝር ሊጠቀሱ የሚችሉ ብዙ ጉዳዮች አሉ። ህግን ጥሶ ሰዎች “ህግ በእጄ” የሚሉበትን ስርዓት ከማየት የበለጠ ክፋት ግን የለም። መጤና ነባር የሚባሉ ትርክቶች ፣የመንጋ ፍርድ፤ግድያዎች፣ህገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውሮች፣ወዘተ የለውጥ እንቅፋቶች ቢሆኑም ብቻቸውን ግን ለውጥን አያጨልሙም። ለዶክተር አብይ አህመድ አስተዳደር ትልቁ ፈተና ግን ና ተብሎ ከተጠራ የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ጦር ተማዝዞ አለምአቀፍና ሃገራዊ ስመን ማጠልሸት ነው።ለምሳሌ ኦነግ በስንት ግልግል አሁን ጦሩን ለአባገዳዎች አደራ ሰጠሁ ቢልም የማዕከላዊ መንግስቱን ስልጣን በጦር የተገዳደረ ፓርቲ ነው። ህዝቡ ትዕግስት በዛ እስኪል ድረስ ባንክ እየዘረፈ እና ፖሊስ እየገደለ የቀጠለ ሃይል ለሃገር ሰላም መደፍረስ ምክንያት ቢሆን አይደንቅም። በቀጣይ ግን እንዲህ አይነት የፖለቲካ ውሳኔዎች ሲወሰኑ ግልጽ እና ተጠያቂ ከሆነ አሰራር ውጪ በስሜት ብቻ መነዳት እና ኑ ማለት የሚያስከፍለውን ዋጋ ታሪክ መዘግቦታል። አሁንም ያልጠራ ቢሆንም የኦነግ ጉዳይ ግን የማንአለብኝነት ፖለቲካ እና የአሻጥር ውጤት አንዱ መገለጫ ነው። በዚህ ከቀጠለ ብቻ የዶክተር ዐቢይ መጪ ፈተና ሊሆን የሚችልበት እድል አለ። ትጥቅ መፍታት ከነበረበት ድርጅት ጋር ደግሞ ውጊያ ማድረግ ፣የምጣኔ ሃብት አሻጥሮች እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ይህንን ለመመከት የተዳከመ መምሰል ለአስተዳደሩ ብቻ ሳይሆን ለሃገሪቱ መረጋጋትም እንደስጋት ከሚታዩት ውስጥ ይገኙበታል።

ዶ/ር ሰሚር የሱፍ Current situation in Ethiopia opportunities and challenges በሚለው ጥናታቸው ያስቀመጧቸው የዚህ ዘመን ለውጥ ተግዳሮቶች ስናይ ለዶክተር ዐቢይ ቀጣይ ፈተናዎች ሊሆኑ ይችሉ ይሆን ብለን እንጠይቃለን።

- **የብሄር ክፍፍል ፈተና** (ethnic division challenge) ፣ ይህ መከፋፈል ባለበት የተረጋጋ ዴሞክራሲ ማስፈን ከባድ ነው፣ የተረጋጋ ሃገር መምራትም ያቅታል።
- **የምጣኔሃብት ፈተና** (Economic challenge) ፣ በሽግግር ጊዜ ኢኮኖሚን ማሻሻል ከባድ ቢሆንም የፖሊሲ አለመሻሻል፤ የሃብት ክፍፍሉ በጥቂት ሰዎች ብቻ መያዝ አደጋ አለው።
- **የማይፈለግ የተቋማት ውርስ** (unwanted Institutional legacy ) አገሪቱ በሽግግር ላይ እንደመሆኗ መጠን አዲስ ተቋማት አለመኖራቸው ችግር ሆኖ በተለይ ፖሊስ እና መከላከያ፣የፍትህ ተቋማት አለመለወጥ፣የብሄር ፌድራሊዝም መኖር የግለሰብ ለውጥ እንጅ የተቋም ለውጥ የለም የሚለውን ያጠናክራል።
- **ድሎችን የማስቀጠል ፈተና** ፣ሶስተኛው ጠቅላይ ሚንስትሩ እስከ አሁን ያስመዘገቧቸውን ድሎች እንዴት ያስቀጥላሉ? የሚለው ነው። ከኢትዮጵያና ኤርትራ ጉዳይ ብንነሳ አገራቱ በቀጣይ በሚስማሙባቸው ጉዳዮች ይደሳታሉን? የኢትዮጵያንስ ጥቅም እንዴት ማስከበር ይቻላል? የሚሉትን መመልከት ያስፈልጋል።
- **የመልስ አልባ ኢኮኖሚ ጥያቄዎች ፈተና**፣ የብር የመግዛት አቅም መቀነስ አንድምታዎችአገሪቱ ከውስጣዊ የፖለቲካ ውጥረትና የደህንነት ስጋቶች በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ መሰናክሎችም ያሉባት መሆኑ የጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ አህመድን አስተዳደር ፈተና ውስጥ መክተቱ አይቀሬ ነው።በለንደን የምጣኔ ሐብት መምህሩ ዶክተር ነመራ ገበየሁ “ፖለቲካዊ መሰናክሎች ችላ ባይባሉም የበለጠ የሚያሰጉት ግን የምጣኔ ሀብት ፈተናዎች ናቸው” እንዳሉት ነው።

ጠቅለል ባለ አነጋገር እንደ ኢትዮጵያ ባለች ከባድ ሃገር ውስጥ የአዲሱ መሪ ዶክተር አብይ አመራር ሂደት ፈተና ባያጣውም ህዝብ ከጎኑ እስካለ ድረስ ብቻ በሂደት ዋጋ ከፍሎም ቢሆን ፈተናውን ማለፉና ሃገርንም በሚፈለገው ደረጃ ላይ አስቀምጦ ውርስ ትቶ ማለፉ አይቀሬ ነው።

# የነ በረከት . . .

ከገጽ 3 የዞረ




እና ተሰንዶ ወደ ሕግ መላኩን ተናግረው ነበር:: በህግ አግባብ የሚወስደውን እርምጃ በተመለከተም በቅርቡ ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን መጠቆማቸው የሚታወስ ነው::

የአዴፓ ማዕከላዊ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ምግባሩ ከበደ ከጥቂት ወራት አስቀድሞ ለአማራ ቴሌቪዥን እንደገለጹት የቦርድ ኃላፊው አቶ በረከት ስምዖን እና ዋና ሥራ አስፈፃሚው የነበሩ አቶ ታደሰ ካሳ ከማዕከላዊ ኮሚቴነት የታገዱት በጥረት ውስጥ በፈጠሩት ደካማ አሰራር የተነሳ ነው ብለው ነበር:: በወቅቱ አስፈፃሚዎቹ ላይ ፖለቲካዊ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን ሂደቱን ተከትሎም ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ መናገራቸው የሚዘነጋ አይደለም::

## አቶ በረከት ስምኦን ከብአዴን አመራርነት ስለታገዱበት ይህን ተናግረው ነበር፣

“የታገድኩባቸውን ምክንያቶች አላምንባቸውም:: ምክንያቱም ሁለቱም [ክሶች] መሠረተ ቢስ ናቸው:: የአማራ ሕዝብን አይጠቅሙም:: የለውጥ ኃይሎች አይደሉም:: ጥረትንም ችግር ፈጥረውበታል ነው የሚሉት:: ሁሉም መሠረተ ቢስ ናቸው:: ለአማራ ሕዝብ አይጠቅሙም የሚለው እኛ ዕድሜ ልካችንን ለራሳችን ሳናስብ በአማራ ክልል ነው ስንታገል የኖርነው:: ’ክልሉ ተለውጧል፤ አድጓል፤ ተሻሽሏል፤ ባለፉት 25 ዓመታት ወደፊት ተራምዷል’፥ ሲሉ የነበሩ ሰዎች ይህን [ለውጥ] ወይ ብቻችን አምጥተነዋል ማለት አለባቸው፥ ወይ ደግሞ አብረን ነው ያመጣነው ማለት አለባቸው::

የለውጥ ኃይሎች አይደሉም የተባለውም መሠረተ ቢስ ነው:: ሰው አሁን ነው ድምጹ መሰማት የጀመረው:: አሁን ሦስት አራት አምስት ወራት:: እኛ ከ2002 ጀምሮ "በከባድ ሁኔታ ችግር ላይ ነን፤ ድክመታችን በዝቷል፤ አገሪቱንም ወደ ቀውስ የሚያመሩ ነገሮች ተበራክተዋል፤ መሻሻል አለብን’ ብለን የለውጥ ሐሳቡን ያመጣነው እኛ ነን:: ለዚህም ከባድ ዋጋ ክፈለናል:: ያልከፈልነው ነገር የለም:: የለውጥ ኃይሎች አይደሉም የሚባለው፥ የለውጥ ጀማሪዎች ቀስቃሾች እኛ ነን:: ግን ወጥተን እንዲህ አድርገናል ማለት አልወደድንም::

ጥረትን በተመለከተ ለመነሻ የተሰጠን ገንዘብ 20 ሚሊዮን እና 31 ያረጁ ኤንትሬዎች ማርቼዲሶች ከጦርነቱ የተራረፉ ናቸው:: አሁን 11 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ 20 ኩባንያዎች ለአማራ ክልል አስረክበናል:: ከምስጋና ጋር ሊሸኙን ይገባ ነበር:: ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ አንዲሉ በወጉ እንኳ አላሰናበቱንም::

ኦዲትን ሪፖርት አለን:: ሁሉም ነገር አለን:: በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንዶውመንት ተብሎ የግብር ከፋይ ምሳሌ ይጠቀስ ቢባል ጥረትን ያክል ግብር ከፋይ ተምሳሌት የሆነ ድርጅት የለም:: ስለዚህ በዚህ ደረጃ ያነሱትም ነገር መሠረተ ቢስ ነው::” ቢቢሲ

## አት ታደሰ ካሳ ጥንቅሹም ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ይህንን ተናግረው ነበር

“የጥረት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነበርኩ:: ለዘጠኝ ዓመት ያህል አገልግለናል:: በዛ ቆይታ ጥረት ብዙ ለውጥ አምጥቷል:: እኔ አመራር ላይ እያለሁ በጣም አስደናቂ ለውጥ እያመጣ የነበረ ደርጅት ነው:: ሂደቱ የማይስማማቸው ሰዎች ይኖራሉ:: አንዳንድ የሚነሱ ነገሮች ነበሩ:: ችግር አለ ይባል ነበር:: እኛም በየጊዜው እየተማርን ነው ሥራውን ስንመራ የነበረው:: የቢዝነስ ሥራ ነው:: በ20 ሚሊየን ብር ተጀምሮ እኔ በምወጣበት ጊዜ ወደ 11 ቢሊየን ብር ካፒታል ያላቸው 20 ኩባንያዎችን ነው የፈጠርነው:: ጉድለት ነበር የሚለውን አስቀድመን ራሳችን ያየነውና እየገመገምን፣ መጨረሻም ሥር ነቀል የሆነ መፍትሄ ለማምጣት የሚችል ሥራ ስንሠራ ነው የነበረው:: ከዛ የጤንነትም የዕድሜም ጉዳይ ስላለ ከዚህ በኋላ «ጥረት» ላይ በቃኝ በሚል ሚያዝያ ወር ላይ በራሴ ለቅቄ ወጣሁ:: በራሴ ፈቃድ እንደወጣሁኝ ደብዳቤው በእጄ አለ:: በግልጽ ነግሬያቸው ነው…:: አሉ የምትሏቸውን ጉድለቶች ራሳችን የገመገምናቸው ናቸው:: ከዚ ውጪ ያባከንነው ገንዘብ የለም:: በግልም ደግሞ የሠራነው ጥፋት የለም:: ቢቢሲ

## በሁለቱ ከፍተኛ አመራሮች ላይ የቀረበው የክስ ጭብጥ

የአማራ ክልል ስነ- ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን በነ አቶ በረከት ስምኦን እና አቶ ታደሰ ካሳ የሙስና ምርመራ ዙሪያ መግለጫ ሰጥቷል:: የአማራ ክልል ስነ- ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ዝግአለ ገበየሁ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ጥረት ኮርፖሬት በ6 ካምፓኒዎች የአክስዮን ግዥ እና አንድ ካምፓኒ ሽያጭ በጥረት የቦርድ አመራሮችና በሌሎች ከፍተኛ አመራሮች የአመራር ጥሰት በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስላደረሱ በህግ እንዲጠየቁለት ኮሚሽኑን መጠየቃቸውን አስረድተዋል:: ኮሚሽኑም ይህንን ጥቆማ በመቀበል በኦዲት መረጋገጥ ያለባቸው ኦዲት እንዲደረጉ በማዘዝ የ5 ካምፓኒዎች የኦዲት ሪፖርት ይፋ አድርጓል:: 2 ካምፓኒዎች በኦዲት ምርመራ ላይ መሆናቸውንም ጠቁሟል::

### በኦዲት ምርመራ ወቅትም ፡-

1. የአዋጭነት /feasibility/ ጥናት እና የዳሰሳ ጥናት ሳያካሂዱ የአክስዮን ግዥ መፈፀም:
2. ከኮርፖሬቱ የፋይናንስ አሰራር ውጭ በፓርትነር በተመሰረቱ ካምፓኒዎች ያለምንም መያዣ ብድር በመስጠት ሃብት እንዲባክን ተደርጓል::
3. በባለሙያ ከተጠናው የዋጋ ግምት በላይ የአክስዮን ግዥ በመፈፀም ድርጅቱ ላይ ጉዳት ማድረስ::
4. ከውሉ ውጭ የፓርትነሩን የአክስዮን ድርሻ ጭምር ክፍያ መፈፀም በኋላም ያለምንም ምክንያት የጥረትን ድርሻ በዱቤ ክፍያ መሸጥ:: የታዩ ችግሮች መሆናቸውን ኮሚሽኑ ገልፃል:: በእነዚህ ምክንያቶች ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው ወደ ስራ ሳይገቡ የቀሩ ካምፓኒዎች መኖር በአብነት የቀረቡትም:-

1. ላፓልማ የተባለ ማዕድን ለማምረት ከተቋቋመ ድርጅት ምንም አይነት የካፒታል ዕድገት ባላሳየበት የአክስዮን ድርሻው 22በመቶ ማለትም ባለ1000 ዋጋ አክስዮን ብር 2200 ብር በመግባት 4 ሚሊየን 320 ሺህ ብር አላግባብ ተጠቃሚ አድርጓል:: የዚህ ካምፓኒ የቀድሞ ባለቤቶች ለመንግስት መክፈል የነበረባቸው የካፒታል ዕድገት ታክስ ባለመክፈል 1 ሚሊየን 296 ሺህ ብር ባለዕዳ ሆኗል:: ለዚህ ፋብሪካ ግንባታ ተከላ የተገባ 17 ሚሊየን 45 ሺህ 379 ብር ላይ ሳይውል ለብልሽት ተዳርጓል:: በዚህ ካምፓኒ ብቻ 22 ሚሊየን 661 ሺህ 379 ብር (ተመዝብሯል) ጉዳት ደርሷል::

2. በየዳ ሰስቲካል ኬሚካል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር • አንድ የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤት ግለሰብ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ባደረገው ስምምነት በ7000 እጣ በጥረት ስም የተመዘገበ 700 ሺህ ብር አክስዮን ገዝቷል:: ጥረት ግን የ1 ሺህ 400 እጣ ብር 1 ነጥብ 4 ሚሊየን ክፍያ ፈፅሟል:: በብድር ብር 564 ሺህ 298 ተከፍሏል:: በመጨረሻም የጥረት ድርሻ ያለምንም ምክንያት በዱቤ ሽያጭ በድርጅቱ ባለቤት የትዳር ጓደኛ ተሽጧል:: በዚህም 1 ሚሊየን 173 ሺህ 426 ብር ሳይመለስ ቀርቷል::

ቀጣዩን በገጽ 12 ይመልከቱ

# የኢሕአዴግ መስቀልያ መንገድ

ኢሕአዴግ ሌጣውን ያለምንም ተቀናቃኝ ሲዘውረው የነበረው የፓለቲካ ሥልጣን አሁን ሌላ መልክ ይዟል፡፡ኢሕአዴግ እንደ ፓርቲ መስቀልያ መንገድ ላይ እንደቆመ ከማንም የተሰወረ ሐቅ አይደለም፡፡ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ሀገሪቱን ቅርቃር ውስጥ ጨምሯት በኖረው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተዓለም ላይ እንኳን በአንድ ድምጽ መስማማት አልተቻለም፡፡አንድን ማኅበረሰብ ጠላት እና ወዳጅ ብሎ በመፈረጅ ፣አግላይ የትግል መስመርን በመከተል የሚታወቀውን አብዮታዊ ዴሞክራሲን አዴፓ እና ኦዴፓ እርግፍ አድርገው እንደተው ቢገልጹም በሕወሓት በኩል ያለው አቋም ግን ምንም አልተቀየረም፡፡ ኢሕአዴግ በርዕዮተዓለም ቅኝትም ሆነ ከሚታገልበት የፓለቲካ መስመር አኳያ ሲመዘን በተዛነፈ ሐዲድ ላይ እየነጎደ ነው፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሚመራው አዲሱ አስተዳደር የሕዝብ ወገንተኝነቱን እያጠናከረ በሄደ ቁጥር ኢሕአዴግ እንደ መርህ የቆመበት ድርጅታዊ ቀኖና እየተዳከመ መሄዱ የማይቀር ነው፡፡ይህ ደግሞ ለሰፊው ሕዝብ ብሥራት ነው፡፡የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተሰሚነትን የጨመረው በያዙት ተሰፍ ሰጪ ቁርጠኛ የፓለቲካ እርምጃዎች እንጂ እንደቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በማእከላዊ ዴሞክራሲ በተጠረነፈ አፋኝ ድርጅታዊ አሠራር አይደለም፡፡ ስለዚህ ኢሕአዴግ ሲወለድ ጀምሮ አጥብቆ የያዘው መሀላ ንፋስ እየገባው እንደሆነ ለመረዳት ፍጹም የማያፈናፍን አገዛዝን አንብሮ የቆየበት ፓለቲካዊ መርህ በአዲሱ የለውጥ አስተዳደር ቀስ በቀስ እየተሸረሸረ መሄዱን ስንታዘብ ነው፡፡

በቅርቡ የድርጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታዎችን በመገምገም አቅጣጫዎቹን ያስቀመጠበትን መግለጫ ስንመለከት ከላይ የተነሳው ነባራዊ ሁኔታ ውሃ የሚያነሳ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ድርጅቱ በመግለጫው ላይ አሁንም የጠራ አቋም እንዳላያዘ ብዙ ማሳያ የሚሆኑ ሐሰቦችን አንጸባርቋል፡፡የተገነኘውን የተስፋ ጭላንጭል ለማዳፈን ሌት ተቀን የሚባዝኑ ፀረ ለውጥ ኃይሎች በየአመራር እርከኑ ላይ እንደተሰገሰጉ ተገልጿል፡፡በርግጥ ኢሕአዴግ ባለፉት የጭቆና የአገዛዝ ዘመኑ ለመብት እና ነጻነት የሚታገሉትን ኃይሎች ማሸማቀቂያ ታፔላ በመለጠፍ ሰዶ ማሳደድ ውስጥ የመግባት ልማድ ነበረው፡፡ይኸኛው ፍረጃ ግን በዚህ ማእቀፍ ውስጥ ሊወድቅ እንደማይችል እስካሁን የተገኘውን አንጻራዊ ነጻነት ዋቢ ማድረግ ብቻ በቂ ይሆናል፡፡በርግጥ ፀረ ለውጥ ኃይል ተብሎ የተፈረጀው ቡድንን መታገል ከመንግሥት ወገን ብቻ የሚጠበቅ አይደለም፡፡ለውጡ እንዳይቀለበስ ሁሉም ወገን ሊረባረብ ይገባል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አመራር በፀረ ለውጥነት የተፈረጀቱን ኃይሎች ከማድበስበስ ይልቅ በይፋ ግልጽ በማውጣት፣ሰፊውን ማኅብረሰብ ከኋላው ደጀን አድርጎ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ይህ መለሳለስ ኋላ ላይ የበለጠ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል፡፡

ኢሕአዴግ ድርጅታዊው ጥንካሬው እንደከዳው ሌላው ማሳያ አዲሱን የለውጥ መንገድ የሚከተሉ በአንድ ጫፍ ይህንኑ አጥብቀው የሚቃወሙ በሌላ ጫፍ ሆነው እያካሄዱት ያለው ሹኩቻ ነው፡፡በአዴፓ እና በሕወሓት መካከል የተፈጠረው መካረር ገና በወጉ አልጠራም፡፡ሁለቱ ድርጅቶች ባለፈው ሳምንት በመካከላቸው ያለውን ቁርሾ ለሕዝብ ግንኙነት በሚመስል መልኩ ለጊዜው እንደፈቱት ገልጽው ነበር፡፡ይህ ግን ብዙም ሊያዛልቅ የሚችል አይደለም፡፡የቁርሾው ሰንኮፍ ገና አልተነቀለም፡፡

ኢሕአዴግ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ በውስጡ የሚፈጠረው ቀውስ ዳፋው ለመላው የሀገሪቱ ሕዝብ እንደሚተርፍ እሙን ነው፡፡ድርጅቱ በአባል ፓርቲዎች ደረጃ የመርህ እና የርዕዮተዓም ክለሳ ለማድረግ የተወሰነ ርቀት የሄደ ቢመስልም እንደ ፓርቲ ግን ወጥ የሆነ እርምጃ እስካሁን ሲወስድ ለማስተዋል አልቻልንም፡፡

ኢሕአዴግ በለውጡ መስመር የሚገቡትን አባል ፓርቲዎች እያቀፈ፣የሚያፈንግጡትን እያራገፈ ለመሄድ የፓለቲካ ቁርጠኝነትን መላበስ ካልቻለ ሀገሪቱ በቀላሉ ወደ ማትወጣበት ማጥ ወስጥ መግባቷ የማይቀር ይሆናል፡፡ስለዚህ ከመስቀልያው መንገድ አሻግሮ ማማተር ሊመጣ ከሚችለው ሀገራዊ አደጋ በጊዜ ለመጠበቅ ኹነኛ መፍትሔ ነው፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ደረጀ ይመር

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ተስፋዬ ሽብሩ
ሔማስ ታፈረ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
መስፍን ጌታቸው
አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(**ከአሜሪካ**)
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
ታምራት መርጊያ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን


**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ
ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# “የሁሉም የኢትዮጵያዊ ብሔሮች ደም አንድ መሆኑ በዲ.ኤን.ኤ ተረጋግጧል”

## “የቋንቋ ፓለቲካ ጠንቅ ነው”



## ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ

*ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ ከኢትዮጵያዊነት ጋር በተያያዘ በሚፅፏቸው መጣጥፎችና በሚያዘጋጇቸው የታሪክ መጻሕፍት ብሎም በገጣሚነታቸው ይታወቃሉ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የብሔርተኝነት ስሜት በመኮነን ኢትዮጵያዊ አንድነትን በማወደስ በርካታ ሥራዎችን የሠሩ ሲሆን በተለይም ከኦሮሞ ሕዝብ ማንነት ጋር በተያያዘ የብሔሩ ልሂቃን እና አክቲቪስት ነን ከሚሉ በተለየ መንገድ ታሪክን ከእውነታው ጋር በማዛመድ ትኩረት የሚሰቡ አነጋጋሪ ጉዳዮችን በማቀንቀን የሚታወቁት ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳን በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግረቸዋል፡፡*

**ግዮን፡- ፕ/ር ፍቅሬ ኢትዮጵያዊነትን እንዴት ይገልፁታል?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-**ኢትዮጵያዊነት የመልካም ነገር ሁሉ ልዕልና ነው:: ከዚህ ውጭ በዝርዝር እንየው ካልን፤ ኢትዮጵያዊነት ሰፊ ነው፣ እንዲህ በአጭሩ የምታስቀምጠው ነገር አይደለም:: የአማራ እና የኦሮሞ እውነተኛ የዘር ሐረግ በሚለው መጽሐፌ ውስጥ በተቻለኝ መጠን ኢትዮጵያዊነትን በዝርዝር ለመግለፅ ሞክሪያለሁ::

**ግዮን፡- ከሀገር ከወጡ ከረዥም ጊዜ በኋላ ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ሀገር ቤት መጥተው ነበር፤ አሁንም በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል:: የመጀመሪያው አመጣጥዎ እንዴትና ለምን ነበር?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** የዛን ጊዜው አመጣጤ ኢትዮጵያ ውስጥ ቁጥራቸው ሰባ በመቶ ይሆናሉ የሚባሉት የኦሮሞና የአማራን ግንኙነት ለማሻሻል ነበር፤እኔ ባደረግሁት የታሪክ ምርምር ደግሞ የአንድ አባትና የአንድ አያት ልጆች መሆናቸውን ስላረጋገጥኩ፤ ይህንን ለእነሱ በማብራራት እንዲግባቡ፣ ግጭት እንዲያቆሙ፣ ደም መፋሰስ እንዲቀር፣ ከመጣላት እንዲታቀቡ፤ ብሎም አብረው በሕብርና በፍቅር እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችል መልዕክት ለማስተላለፍ ነበር ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁት::

“ሁለት ዝሆኖች ሲራገጡ ወይም ሲጣሉ የሚጎዳው ሳሩ ነው” እንደሚባለው እነዚህ ሁለት ትልልቅ ጎሳዎች ታርቀው በሰላም ካልኖሩ፣ የትልልቆቹ ዳፋ ለሌሎችም ሊደርስ ስለሚችል፣ እነዛን ቀሪውን ሰላሳ በመቶ የሚሆኑትን ኢትዮጵያውያንን ለማዳን በተጨማሪም ፣በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ የፍቅር ተልዕኮ ይዤ ነበር የመጣሁት:: በእኔ ግምት ደግሞ ያ ተልዕኮዬ የተሳካልኝ ይመስለኛል::

**ግዮን፡- የአሁኑ የኢትዮጵያ አመጣጥዎና ተልዕኮዎስ ምን ነበር?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** በጠቅላላ ባደረግኩት ምርምር የሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ አባት ኢትዮጵ የተባለ የካህን ካህን፤ የንጉሥ ንጉሥ የሆነ፤እስከዛሬ ድረስም በስሙ ኢትዮጵያን የሚያስጠራ፤ አፍሪቃን በሞላ ኢትዮጵያ ያሰኘ፤ ዛሬ አትላንቲክ ውቅያኖስ የሚባለውን “ኢትዮጵያን ውቅያኖስ” ያስባለ ታላቅ ሰው ነው:: ለዚህ ደግሞ ማስረጃው በአዲሱ መጽሐፌ “የተሰወረውና ያልተነገረው የአይሁዳውያንና የኢትዮጵያውያን ታሪክ” የሚለው ታሪክ ውስጥ ካርታውን በግልፅ አስቀምጬዋለሁ::

መላው አፍሪካ “ላይኛው(አፐር) ኢትዮጵያ ታችኛው(ሎውር) ኢትዮጵያ” ይባል እንደነበር፣ እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ውቅያኖሶችም “የኢትዮጵያ ውቅያኖስ” ይባሉ እንደነበር በመጽሐፌ ውስጥ ገልጬዋለሁ:: የጥንት ባህረኞች ሲዞሩ ይዘውት ይንቀሳቀሱበት የነበረው የዓለም ካርታ ውስጥ ይሄ ማስረጃ አለ:: አሁንም ቢሆን የኢትዮጵ ትውልድ በሆኑ አፋሮች ስም ነው “ የአፍሪቃ” ስያሜ የተገኘው :: ያው ከእኛ አልወጣም ማለት ነው:: እስያ ከንግሥት ሳባ በፊት በነበረው በትልቁ ንጉሠ ነገሥት በአቴ ሲአኤል “እስያ” የሚለው ስያሜ እንደተሰጠው፤ ንጉሡም እስያ ሄዶ፣ ቅኝ ገዝቶ፣ ንጉሦች ሾሞ እስያን “እስያ” እንዳደረግ ትልልቅ የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ::

ስለዚህ ሁለተኛው ተልዕኮዬና የአሁኑ አመጣጤ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የአንድ እናትና አባት ልጅ መሆኑን አውቆ በሰላም፣ በፍቅር እንዲኖር ለመስበክ፣ ለማስረዳትና ሐቁን ለመናገር አስቤ ነው ወደ እናት ሀገሬ የመጣሁት::

**ግዮን፡- በቅርቡ “የኢትዮጵያውን ደም አንድ ነው፣ ዲ ኤን ኤውም ይህንን ያረጋግጣል” በማለት የደረሱበትን ጥናት በይፋ ገልፀዋል:: በአሁን ሰዐት በተቃራኒው ኢትዮጵያዊ ውስጥ የብሔር ልዩነት እየተስፋፋ ነው፤ ከዚህ በመነሳት የኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ ...... የሚባል የደም ልዩነት ሊኖር ይችላል?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** የደም ልዩነት የለም:: ያው የሁሉም ደም ቀይ ነው፤ ከዚህም በላይ ደግሞ ከኢትዮጵ የወረደ ነው:: ታሪክ እንደሚያስረግጥልን ከሆነ ኢትዮጵ ዐሥር ወንዶች ወልዶ እነዛ ተሰራጭተውና ቅርንጫፍ ሆነው ነው ሁላችንም የተገኘነው:: ከሶማሌ ዳር ድንበር ሳይቀር፤ ማሳይ ድረስ ይደርሳል የዘር ሐረጋችን፤ ከእኛ ነው የሄዱት::

ሁላችንም አንድ ነን:: አማራ ፣ኦሮሞ፣ትግሬ፣ ጋምቤላ፣ የደቡብ የኢትዮጵያ ጎሳዎች በጠቅላላ ከኢትዮጵ ዘር ነው የሚመዘዙ:: ይሄ እውነታ በመጽሐፍ በዘር ሀረግ ትንተና ተረጋግጧል:: ሁለተኛ በዲኤንኤ ወይም በሳይንስ ዘርፍ የሰውን ዘር የሚያጠኑ ሳይንቲስቶች ፤ ከ30 ዓመት በኋላ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የትግሬ እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ጎሳዎች በሙሉ አንድ አይነት ዲ ኤን ኤ እንዳላቸው በጥናታቸው ደርሰውበታል::

**ግዮን፡- የእዚህ ጥናት ውጤት በይፋ የተገለፀው መቼ ነው?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** ጥናቱ እንዳልኩት ረዥም ዓመት ወስዷል፤ ውጤቱ ይፋ የሆነው ግን አንድ ሶስትና አራት ዓመት ሆኖታል:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጎግል ላይ “ኢትዮጵያ ጄኔቲክስ” ወይም ደግሞ “ኢትዮጵያ ዲ ኤን ኤ ሪሌሽንሺፕስ” ብሎ ቢፈልግ የጥናቱ ውጤት በሳይንስ ተረጋግጦ መቀመጡን በግልፅ ይመለከታል::

ሳይንቲስቶች ከሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ሳምፐል ደም ወስደው ያጠኑት ጥናት ነው:: በጣም ተመሳሳይነትና አንድ አይነት እንደሆነ ነው የሚያረጋግጠው:: ስለዚህ በኢትዮጵያውያን መሀል የደም ልዩነት ጨርሶ እንደሌለ በሁለቱም መንገድ ይደገፋል ማለት ነው:: የኢትዮጵያውን ደምና ዘር አንድ መሆኑ በታሪክም ተረጋግጧል፤ በሳይንሳዊ ጥናት ►

ውጤትም ተረጋግጧል::

**ግዮን፡- የኢትዮጵያዊነት ጽንሰ ሐሳብ ምንድን ነው?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** የኢትዮጵያዊነት ጽንሰ ሐሳብ በጣም የተቀደሰና እጅግ ከፍተኛ የሆነ ነው:: ኢትዮጵያ የሚለው ቃል "የቢጫ ወርቅ ስጦታ ለእግዚአብሔር" ማለት ነው:: ዮጵ ከሚለው ቃል ነው የመጣው፤ ዮጵ ቢጫ ወርቅ ነው፤ ግዮን አካባቢ ይገኝ የነበረ ነው፤ ኢት ማለት በጥንት ሱባዊ ፊደልና ቋንቋ "ስጦታ" ማለት ነው:: ሱባዊ እውነተኛና በጣም የተጨበጠ ነገር ነው:: ግዕዝ የዛሬ ሶስት ሺህ ዓመት በፊት ነው ወደ ኢትዮጵያ የመጣው:: ከግዕዝ በፊት ሱባዊ ነው:: ይህ ቀደምት ቋንቋ እንደውም የአዳምና የሄዋን ቋንቋ ነው የሚመስለኝ::

ምክንያቱም አዳምና ሔዋን በግዕዝ ቢናገሩ ኖሮ የልጆቻቸው ስምም ግዕዝን የተመረኮዘ ይሆን ነበር:: ግን ሱባህ ስያሜ ነው:: የልጆቻቸው ስምም ሱባህ ላይ ትርጉም አለው፤ ስለዚህ የእነሱ ቋንቋ ነው ብለን እናስባለን:: ባቢሎንን ወደ ሰማይ በሚገነቡበት ሰዐት ያኔ ሱባህ ነበር የሚያወሩት፤ ግን በሰራነው ፎቅ እግዜር ድረስ እንድረስ የሚል ትዕቢት በመያዛቸው፣ እግዜር ተቆጥቶ ከፋፈላቸው፣ ቋንቋቸውን ቀያየጠው:: ያን ጊዜ ሌላ ቋንቋ መጣ፤ ሱባህ በቄሶች ዘንድ ተርፎ፣ በመጽሐፍ ብቻ ቀርቶ፣ በኢትዮጵ በኩል ወርዶ ወርዶ ይኸው ፊደሉ ተገኝቷል:: ሱባህ ከግዕዝ በፊት የነበረ የሰው ልጅ ቋንቋ ነው::

ግዕዝ አጋዚያን የሚባሉ ከእስራኤል የመጡ ሰዎች የሚናገሩት ቋንቋ ነበር:: ቀዳማዊ ምኒልክ እነሱን ይዞ ሲመጣ የእናቱና የሳባ ወገን እሱን ሲቃወሙት፣ እነ አዘቦ ራያና ሌሎች ኢትዮጵያውን "ይሄ ክልስ ከውጪ ሰው ይዞ መጣ" በሚል ተቃውመው ተዋግተውት ነበር:: ያኔ እናቱ አግዛው፣ እነዚህ አጋዚያንም ረድተውት ነጻ ስለወጣ "ነጻ አውጪ አጋዚ" በሚል የእናቱን ወገን ሳባን ትቶ፤ የአባቱን ሀገር የሰለሞንን (የእስራኤልን) ይዞ የሰለሞን ስርወ መንግሥትን መሠረተ፤ የመጨረሻው የኢትዮጵ ስርወ መንግሥት ተወካይ የሆነችው ሳባን (እናቱን) በመተው በመሠረተው ስርወ መንግሥት እስከ አፄ ኃይለስላሴ ድረስ ይህንን ስሜት ነበር የሚያንጸባርቀው፤ ከዛጉዌ በስተቀር:: ለነገሩ ዛጉዌም ራሱ የሰለሞን ዘር ነኝ ይል ነበረ::

ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ሊያጠፋ ፈለገና "ቋንቋችን ግዕዝ ነው፣ ሱባህ ታግዷል" አለ:: ሀገራችንም ብሔር አጋዚ ትባላለች የሚል አስቦ ነበር፤ ግን አልሆነለትም:: እግዜር የመረጠው "የቢጫ ወርቅ ስጦታ ለእግዚአብሔር" የሚል ስለሆነ ማንም ሰው ይቺን ቃል ሊያጠፋ አልቻለም:: መላው አፍሪካ ኢትዮጵያ ተብሎ የነበረው ቢጠፋ ቢያንስ አሁንም ድረስ የአባታችን የኢትጵና እርሱ ከመሰረተው ግዛት(ቴሪቶሪ) ትንሿን ይዘን ቁጭ ብለናል:: ስለዚህ ይሄ የኢትዮጵያዊነት ጽንሰ ሀሳብ መለኮታዊና ከእግዚአብሄር ጋር የተያያዘ ከፍተኛ ስም ነው::

**ግዮን፡- ኢትዮጵያውያን እሴቶቻችን የምንላቸው ምን ምን ናቸው?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** የኢትዮጵያውያን እሴቶች ድሮ የነበሩ፣ አሁን የጠፉ ናቸው:: ሀገራችንን ኮሚኒዝም ከመጎብኘቱ በፊት የእንቁ እሴቶች ባለቤት ነበርን:: ለአብነት ያህል አለመስረቅ፤ ሰውን ዝም ብሎ በግፍ አለመግደል፤ፈሪሃ እግዚአብሔር መኖር፤ እንግዳ መቀበልና መንከባከብ፤ ተካፍሎ መብላት፤ ታላቅን ማክበር፤የመሳሰሉት ከአባቶቻችን የወረስናቸው አኩሪ ባሕሎቻችን ነበሩ::

**ግዮን፡- እነዚህ የጠፉና እያጠፉ ያሉ እሴቶቻችንን ለማቆየትና ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብን?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ወቅት ማርክሲዝም የሚባል ጠንቀኛ ፍልስፍና በተማረው ኃይል አማካኝት ተስፋፍቶ ነበር:: ከዛ ወታደራዊው ደርግ ተቀብሎ "ማርክሲስት ነኝ" ብሎ ማስተጋባቱን ተያያዘው:: እነ መለስ ዜናዊም "የአልባኒያን ሶሻሊዝምን" አምላኪ ነበሩ::

ማርክሲዝምን ስታጠና ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር የለም ነው የምትለው:: "ሃይማኖት የሰው ልጆችን እንደ ዕጽ የሚያሰክር ነገር ነው፤ የድሃ አደንዛዥ ዕጽ ነው ሃይማኖት" ብሏል ማርክስ:: እኔ ደግሞ ሁሉን ነገር ከመረመርኩ በኋላ ፣ማርክሲዝም የድሃው አደንዛዥ ዕፅ ነው ብዬ ገለበጥኩት::አንድ መሪ አምላክ እንደሌለ ካመነ የበላይ የለውም ማለት ነው:: ስለዚህ ያ መሪ ቢዋሽ፣ ቢያስር፣ ቢገድል ቢዘርፍ ምንም አይሰቀጥጠውም፤ ከዚህን መሰሉ የከፋ ድርጊቱ የሚሰበስበው የለም:: ለምን የበላይ ጠያቂ የለበትምና::

ጉልበት ካለው አቅም ካለው፣ ጦር ሠራዊት ካለው፣ ገንዘብን ጨምሮ ሁሉ ነገር ካለው "ማን ይነካኛል" ብሎ ነው የሚያስበው:: ይሄ መሪ አስርቱ ትዕዛዛትን ለመፈፀም ግዴታ የለበትም:: አትግደል፣ አትስረቅ፣ አታመንዝር ፣የሰው ሀብት አትመኝ የሚሉትን ነገሮች በሙሉ አይቀበልም:: ፈጣሪ የለም ብሏልና :: በዚህ መሰረት ከላይ ያለው መሪ ሙስና ሲፈፅም፣ ከስር ያለውም እንዲሁ ያንን ድርጊት ይፈፅማል:: ከላይ ያለው መሪ በአደባባይ በቴሌቪዥን፣በሬድዮና በጋዜጣ ሲዋሽ ፤ሌላውም ሕዝብ እንደመሪው ስለሆነ ቀጣፊና ግብረገብነት የጎደለው ይሆናል::

**ግዮን፡-ይህ ነገር ለወጣቱ የውድቀት መንስኤ ነው ማለት ይቻላል?**

ፕ/ር ፍቅሬ፡-በትክክል የወጣቱ ውድቀት ከዛ ጊዜ ነው የሚጀምረው:: የዛሬ አርባ አምስት ዓመት በደርግ የሥልጣን ዘመን የጀመረው ውድቀት፣ በወያኔ የ27 ዓመት የሥልጣን ዘመን ደግሞ ተጠናክሮ ቀጠለ:: ተራማጆች ነን ከሚሉት ተማሪዎች ጀምሮ እግዜርን ሲክዱ፣ እነርሱም ጓዶቻቸውን ገድለው ሥልጣን ለመያዝ ወደ ኋላ አላሉም:: ስለዚህ ኢህአፓም እርስ በርስ በሥልጣንና አለመግባባት ጓደኛውን፣ ወንድሙን፣ እህቱን የገደለበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ማርክሲዝምን ስትከተል ትቀውሳለህ ፤የሚከብድህ የሚመልስህ ነገር የለም::

አሁን መደረግ ያለበት አንደኛ መፍትሔ ኢትዮጵያዊነትን መከተል ነው:: የኢትዮጵ ልጆች መሆናችንን ማመን:: ቀጥሎ ይሄን ቀውስ ያመጣው ከማርክሲዝም በተጨማሪ ጎሰኝነት ነው፣ በክልልና በቋንቋ የተካለለ ግዞት ነው ጎሰኝነት:: በቋንቋ ላይ ተመሥርቶ የገዛ ወገናችንን እንደ ባዕድ ማየት፣ ማባረርና ማፈናቀል ነው ሌላው ችግር:: በተለይ ታርጌት ሆኖ በዚህ መንገድ ሰለባ የሆነው አማራው ነው:: ሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች አማራውን የአንድነት ማስተባበሪያ ወይም አንድነትን አራማጅ አድርገውታል:: እነርሱ አንድ ሆነው በፖለቲካ አላማ እንደፈለጉ ለማድረግ፣ አማራውን በዝባዥ፣ ጨቋኝ እንደሆነ፣ ከዚህ በፊት እንደበደለና እንደረገጠ ተደርጎ ቀርቧል::

**ግዮን፡- ግን ይሄ አባባል ከታሪክ አኳያ እውነታነት አለው?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** እኔ እንደመረመርኩት በታሪክ ይሄ ነገር አማራው ላይ አልተገኘበትም:: አንድም ነገር:: እንደውም የኢትዮጵያዊያን ዳር ድንበር በማስከበር፣ ነፃነቱን በማስከበር፣ ሀይማኖቱን በማስጠበቅና ከውጭ ወራሪ በመከላከል፣ ከዚህም በላይ ደግሞ በሥነ-ፅሁፍ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስዕሎችን፣ ኪነ ጥበቦችን በማራመድ፣ ታሪካችንን በመጠበቅ፣ እፅዋትን መድኃኒት አድርጎ በማግኘትና በመጠቀም፣ መፃፍና ማንበብን በመጠበቅ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብዙ ነገር ነው ያደረገው አማራ ነው::

አሁን ወደ ተነሳንበት ዋና ነጥብ ስንመለስ ከጎሳና የዘረኝነት ስሜት መውጣት አለብን:: ጎሳ ማለት ቀጥተኛ ትርጉሙ ቋንቋ ማለት ነው:: የቋንቋ ትርጉምም ጎሳ ነው:: ጎስአ ከሚል የግዕዝ ቃል ነው የመጣው፤ ጎስአ ማለት ከውስጥ ተናገረ፤ አፈለቀ የሚለው የንግግር ክፍል ትርጓሜ ነው::

ሁሌ የማነሳው ምሳሌ አለ፤ እኔ ጀርመን ሀገር ሄጄ ጀርመንኛ የሚናገር ልጅ ብወልድ፣ እንግሊዝ ሄጄ እንግሊዘኛ የሚናገር ልጅ ብወልድ፣ ፈረንሳይ ሄጄ ፈረንሳይኛ የሚናገር ልጅ ብወልድ፤ የተለያየ ቋንቋ ልጆቼ ስለተናገሩ ወንድማማችነታቸው አይፋቅም:: በቋንቋ ምክንያት ወንድም መሆናቸው አይሰረዝም:: እኔም ከእነርሱ በተለየ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ስለተናገርኩ አባትነቴ አይፋቅም:: እኔና ልጆቼን ያዛመደን ቋንቋ ሳይሆን የእኔ ደም ዘር ነው :: ለዝምድና ወሳኙ ደም፣ ዘር እንጂ ቋንቋ አይደለም:: አንድ ሰው "እኔ ኦሮሞ ነኝ" ሲል ኦሮምኛ ከሚናሩ ሰዎች መሀል አንዱ አባል እኔ ነኝ ማለቱ ነው:: ወይም አንዱ "እኔ ተጋሩ ነኝ" ሲል ትግርኛ ከሚናገሩ ሰዎች አንዱ እኔ ነኝ ማለት ነው:: ሌላውም እንደዚሁ አማራ ነኝ ሲል አማርኛ ከሚናገሩ ሰዎች አባል ነኝ ማለቱ እንጂ የሚናገረው ስለ ቋንቋው እንጂ ስለ ዘሩ አይደለም:: ዘር የሚለውን ካየን ግን አማራውም ሌላውም የኢትዮጵ ዘር ነው:: አንድ ነው:: ጎሳህ ግን መጀመሪያ አፍ የምትፈታበት ቋንቋ ነው::

**ግዮን፡- ከሁለት ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚወለድ ልጅ የአፍ አፈታት ሁኔታስ እንዴት ይገለፃል?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** እናትና አባቱ ኦሮሞና አማራ ሆነው በሁለቱም እኩል አፍ ከፈታ "ልሳነ ክልኤ" ወይንም ባለ ሁለት ቋንቋ ትለዋለህ:: በቋንቋው ኦሮሞም፣ አማራም ነው ማለት ነው:: በደም ስትመጣ ግን ሁለቱም ወደ ኢትዮጵ ስለሚሄዱ በአጭሩ ልጁ ኢትዮጵያዊ ነው:: ኢትዮጵያዊነትን ከኢትዮጵ በላይ ልሂድ ካልክ አዳምና ሔዋን በሚለው ሐይማኖታዊ ታሪክ ካመንክ፣ የመጀመሪያ እናትና አባት ዘርህ አዳምና ሔዋን ይሆናሉ::

አይ እኔ የማምነው በእነ ሉሲ ነው ካልክ ደግሞ የአንተ ዘር በሉሲና ዘመዷቿ ነው የሚወሰነው:: ቋንቋህ የፈለገ ሊሆን ይችላል በዳርዊን ቲዮሪ ነው የማምነው፤ በፍሮይድ ነው የማምነው፣ በሳይንስ ነው የማምነው ስለዚህ አባቱ ዝንጀሮ ነው ካልክ፤ ዘርህ ዝንጀሮ ነው:: ቋንቋህ ግን አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ሱማልኛ፣ ኦሮምኛ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ አንድ ሰው "አማራ ነኝ" ማለት የለበትም፤ አማርኛ ተናጋሪ ነኝ ማለት ይችላል:: ነኝ የሚለው ቃል ማንነትን ነው የሚገልፀው::

ቀሪውን ቃለ ምልልስ በገጽ 25 ይመልከቱ

## ደራርቱ ቱሉ ታሪክ መሥራቷን ቀጥላለች




ፍልቅልቋ ደራርቱ ቱሉ የአድዋን ድል ለመዘከር በባዶ እግሯ 500 ሜትር ልትሮጥ ነው የሚል ዜና አነበብኩ።

ድሮም ታሪክ ሰሪ፣ ድሮም ድል አድራጊ ፣ ድሮም ፋና ወጊ፣ የአባት እናቱን ታሪክ ይዘክራል፣ ያለፈ አኩሪ ገድሉን ያከብራል፣ ያስከብራል።

ደራርቱዬ፣ የኔ ውብ አበባ...

የኔ ፊታውራሪ...

የኔ ፋና ወጊ....

በአኩሪ ምግባርሽ ከፍ ያደረግሻት ኢትዮጵያ ከዚህም ከፍ ታደርግሻለች....

ያከበርሻት ሰንደቅ መልሳ መላልሳ እጥፍ ድርብ አድርጋ ታስከብርሻለች...

ደራርቱዬ፣

የኔ ፊታውራራ...

የኔ ፋና ወጊ...

የኔ ውብ አበባ....

ከኢትዮጵያሽ ጋራ....ከፍ ብለሽ ብረሪ

ዝንትዓለም አብቢ ...

ሕይወት እምሻው

## ሌባ ጣት

መለስ ዜናዊ ታሞ አልጋ ላይ ተኝቶ ማንበብ ከመውደዱ የተነሳ መጥሀፍ የሚገልጥበት ሌባ ጣቱ በመላጡ ወረቀቱን የሚገልጥለት ባለ ሌባ ጣት ከጎን አስቀምጦ ነበር የሚያነበው ብለው የቀደዱልን ሰወች ዛሬ ትዝ አሉኝ። ለምን ብትሉ እኔም ዛሬ "እንኳን አብሮ አደረሰን" ብየ በመመለስ ሌባ ጣቴ ስለተላጠ ነው። ይሁንና ስልጣን ስለሌለኝ ሌባ ጣት የሚያውሰኝና፤ ከትህትናው አንጻር እንኳን አብሮ አደረሰን በማለት ለጦቢያ ሕዝብ ሲመልስ የሚጥፍበት ሌባ ጣቱ ተላጠ ብሎ የሚቀድልኝ ካድሬና ዘውጌ የለኝም። እንኳን ደረስን! እንኳን ደረሳችሁ!

ብሩክ አበጋዝ

## ኢትዮጵያ ገና ትኖራለች

ኢትዮጵያ ገና ትኖራለች ስልህ ከዚህ በከፋ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፏን በማስታወስ ነው አጎቴ... አዎ ኢትዮጵያ ገና ገና ወላዊ ብዙ ትኖራለች!!

ኢሕአፓ "ፓ" ብላ በመኢሶንና በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ደርግ ላይ ሙድ በመያዝ ነጭ ሽብርተኛ ነኝ ባለችበት ወቅት መኢሶንም የሕቡዕ ዳንሴ ይመቸኛል ብላ ከደርግ ጉያ ዘወር ስትል በምስራቅ የዚያድባሬ ውቃቤ ተክለፍልፎ ኢትዮጵያን ወረረ።

አስበው አድዋን አልፈናል

አስበው ማይጨውን አልፈናል... የነ ኢሕአፓ ታሪክ ጊዜ ምዕራቡ የዓለም ክፍል ምን አሚረተ መሰለህ? "ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከዓለም ካርታ ትጠፋለች!" ...

ዜያድባሬም ፈረጠጠ፡ ኢሕአፓም በቀይሽብር ተቀወጠ... እና ዛሬ የጁምዓ ሌሊት ነው ጓድ። ኢትዮጵያ ገና ገና ገና ብዙ ትሞሽራለች። የሚርተኛ ሚርት ጫፏን አይነካትም ስልህ ነቢ (ሰ.ዐ.ወ) በስም ስለጠሩልኝ መሸሻም ስላደረጓት ልቤ አይፈራም።

ይህን ስልህ ዓይኑ-ናስ እንዳለባት ሳልክድ ነው። የልጅ ጨዋታ የተመቸው በዝቷል። ጋሼ ዱዓ የማያደርገው ነገር የለውም። ሁሉም ይብሰል በልልኝ። ሶለዋት አለ ነቢ እያወረድክ በዝምታህ ውስጥ ተነጋገረው ሸጋው። ሀገሬማ ገና ገና ገና ትኖራለች!!!

ሱለይ አደም

## “ነዋሪ” እና “መጤ” ብሎ በመክፈል የሚታወቀው ፌዴራሊዝማችን !

በአገራችን ላለፉት 27 ዓመታት በሥራ ላይ የቆየውና ለአያሌ ዜጎች ሞትና መፈናቀል ምክንያት የሆነው ብሄርን/ጎሳን መሰረት ያደረገ ፌደራላዊ ሥርዓት ኢትዮጵያዊያንን “የክልል” እና “ከክልል ውጭ የመጡ” ብሎ ይመድባቸዋል:: በዚህ ክፍፍል መሠረት በአንድ ክልል ውስጥ ከሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን መካከል የክልሉ ባለቤቶችና ባለሙሉ መብት የሚሆኑት “የክልሉ ሰዎች” ሲሆኑ፣ “ክልል ውጭ የመጡት” በክልሉ ባለቤቶች መልካም ፈቃድና ችሮታ ላይ ተመሥርተው በጥገኝነተ መልክ የሚኖሩ ናቸው:: የክልሉ ባለቤት ነን የሚሉት ወገኖች ከክልሉ ውጭ የመጡ ተብለው የተመደቡትን ዜጎች በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ “ከክልላችን ውጡልን” የማለት መብት እንዳላቸው ይሰማቸዋል:: እየሆነ ያለውም ይኸው ነው:: በዚህ ጠንቀኛ አስተሳሰብ ምክንያት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው እንደ ባይተዋር እየተቆጠሩ በገፍ ሲፈናቀሉና በርካቶች ሲገደሉ ታዝበናል፤ እየታዘብንም ነው::

የአገራችን ሕገ መንግሥት ዜጎች በየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ እንደፈለገ ተዘዋውሮ ሠርቶ የመኖር መብት አለው እየተባለ ተደጋግሞ ሲነገር እንሰማለን:: ሆኖም ይኸው ሕገ መንግሥት የአገሪቱ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤቶች “ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች” ናቸው ብሎ በማያሻማ ሁኔታ እንደሚደነግግና ክልሎች፣ የብሔረሰብ ዞኖችና ወረዳዎች የተዋቀሩትም ይህንኑ የሕገ መንግሥቱን መርህ መነሻ በማድረግ በዘውጋዊ ማንነት ላይ ተመሥርተው በመሆኑ ይህ ሥርዓት በሥራ ላይ እስካለ ድረስ ዜጎች አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተብለው መከፈላቸውና በማንነታቸው ምክንያት መበደላቸው እንደሚቀጥል ጥርጥር የለውም::

ሚድል ፓዝ

## አርሶ አደሩ ፕሮፌሰር



ምንዳርአለው ሦስት ጊዜ አሸነፈ! በ1984 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ፕሮፌሰርነቱ ከ41 መምህራን ጋር ቀጥሎም ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች በተናጥል እየተከታተሉ ሲያባርሩት የአርሲ ገበሬ ሆኖ በጥላቻ የተሞሉትን አባራሪዎቹን አሸነፈ! ገበሬ ሆኖ በርካታ የፍልስፍና መጽሃፍትን በማሳተም ለሁለተኛ ጊዜ አሸነፈ! ዛሬ ደሞ ከ26 ዐመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አስተማሪነቱ ተመልሶ የአባራሪዎቹን ድውይነት፣ የግፈኛነት እና የእሱን አሸናፊነት ታሪክ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሲተርክ ሰማሁት። ምንዳርአለው ለሦስተኛ ጊዜ አሸነፈ! እነሆ! የገበሬው የፍልስፍና ፕሮፌሰር ታሪክ በአባራሪዎቹ መቃብር ላይ ጎመራ! ምንዳርአለው ሦስት ጊዜ አሸነፈ! (ማስታወሻ- ፕሮፌሰር ምንዳርአለው ዘውዴን ከ2 ዐመት በፊት ባጭሩ ካናገርኩት በኋላ መጽሃፎቹን ፌስቡክ ላይ ማስተዋወቄን አስታውሳለሁ።)

ጢሞቲዎስ ታደሰ

## አቶ አንዳርጋቸው በሚሊኒየም አዳራሽ ይህን ተናገርው ነበር

«የዓለምን ታሪክ ከቀየሩ ትልልቅ ኩነቶች መካከል የአድዋ ድል ዋናው ነው። አድዋ ለእኛ እና ለጥቁር ዘሮች ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለምም ኩራት ነው።አፍሪካውያን ምሁራን ለምን አልበለፀግንም ?ብለው በጠየቁበት ጊዜ « አፍሪካዊ የሆነ ፍልስፍና ስለሌለን እንሆነ በመግለጽ፤ ይህን ፍልስፍና “ኢትዮጲያዊነት” የሚል ስያሜ እንዲሰጠው ተነጋግረው ነበር። ለዚህም ምክንያቱ ይህ፦ «ኢትዮጲያ!» የሚለው ስም የአይበገሬነት እና በጋራ ቆሞ ችግርን የመፍታት ምሳሌ ስለሆነ ነው

«ዛሬ በእጃችሁ የምታውለበልቡትን ሰንደቅ አላማ 15 የአፍሪካ ሀገሮች ከነፃነት በኀላ ካውንስል አቁመው «ምን አይነት ሰንደቅ አላማ ይኑረን ?” ብለው ከመከሩ በኂላ “ የኢትዮጲያ ሰንደቅ አላማን መሰረት ያደረገ ይሑን!” ብለው የመረጡት ሰንደቅ አላማ ነው >>

ደረጀ ሀብተወልድ

# የነ በረከት . . .

*ከገጽ 7 የዞረ*

3. ባሕር ዳር ሞተርስ መገጣጠሚያ አክስዮን ማህበር የፖርትነር ውል ከመግባቱ በፊት ብር 4 ሚሊየን 90 ሺህ 63 ብር ብድር ተሰጥቷል:: በኂላም ጥረት በአማራ ዲዛይን ቁጥጥር ባለሙያዎች ያስጠናው የካፒታል ግምት ብር 10 ሚሊየን 417 ሺህ 16 ብር ሆኖ እያለ የብድሩን ገንዘብ ጨምሮ ብር 24 ሚሊየን 760 ሺህ 230 እንደገዛ ተደርጓል:: ይህ ፋብሪካ ግዥ ከፈፀመበት ህዳር 10 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ምንም እንቅስቃሴ የለውም::

4. ኢስታንቡል ጋዝ ማኒፋክቼሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የአክሲዮን ግዥው በ3 የቱርክ ባለሃብቶች ተቋቋመ የተባለ ድርጅት ነው:: ጥረት በዚህ ካምፓኒ 3 ሚሊየን 641 ሺህ 54 ብር የተከፈለ ካፒታል አለው:: ድርጅቱ ግን ፈርሷል:: በአሁኑ ወቅት ምንም ተጠያቂ አካል የለም:: ይህ ድርጅት ህጋዊ ድርጅት ስለመሆኑ በመጣራት ላይ ነው::

5. ደሴ መዳዶ ውሃ ፋብሪካ በአሁኑ መጠሪያው ጃሪ ውሃ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር 70 በመቶ የአክስዮን ድርሻ በብር 21 ሚሊየን ብር ግዥው በአዋጭነት ጥናት ላይ የተመሰረተ አይደለም:: ባለቤቱም የባንክ ዕዳ ለመመለስ ባለመቻሉ አበዳሪው ዳሽን ባንክ የኩባንያውን አጠቃላይ ሃብት 9 ሚሊየን እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ኮሚሽኑ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በ5 ካምፓኒዎች ዙሪያ የኦዲት መረጃዎችን አጠናቅሮ ክስ የመሰረተ ሲሆን በዳሽን ቢራ ፍብሪካ እና ጃቬንቱስ በተባሉት ሁለት ካምፓኒዎች ላይ የምርመራ ሂደቱ እንደቀጠለ መሆኑን ጠቁሟል:: በአጠቃላይ ጥረት ኮርፓሬት እየተመራ የነበረው በክልሉ ህዝብ ፍላጎት ሳይሆን በተወሰኑ ግለሰቦች እና ቡድኖች ፋላጎት መመራቱ ለጥፋት ዳርጎታል:: ከዚህ በተጨማሪም የኮርፖሬሽኑ አሰራር በውስጡ ላሉት ድርጅቶች ብድር የሚፈቅድበት አሰራር ቢኖርም ለሌሎች ካምፓኒዎችም ከመመሪያ ውጭ ብድር ይሰጥ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ:: ይህ እንዳለ ሆኖ በሁሉም ጉዳዮች ምርመራው ባይጠናቀቅም በተጠናቀቁት ጉዳዮች ክስ መመስረት የሚያስችል ማስረጃ በመኖሩ፤ አሁን በቁጥጥር ስር የዋሉት ተጠርጣሪዎች የድርጊቱ ሁሉ ዋና ፈፃሚና አስፈፃሚ በመሆናቸው እና ደፍሮ ቃለ መጠይቅ ማድረግ ባለመቻሉ፤ ጉዳዩ በተንተተ ቁጥር እንደ ሌሎች ባለስልጣናት ምሽግ አስኪያዘጋጁ መጠበቅ ጉዳት ስለሚያስከትል፤ እና በሌሎች መሰል ምክንያቶች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጓል::

## አቶ በረከት እና አና ጎሜዝ

የአውሮፓ ኅብረት የፓርላማ አባል እና የ1997 ሀገራዊ ምርጫ ላይ የኅብረቱ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ኃላፊ የነበሩት እና የኢትዮጵያን ፓለቲካዊ ጉዳዮች በቅርበት በመካታተል የሚታወቁት አና ጎሜዝ በቲውተር ገጻቸው ይህንን ጽፈዋል::

“በመጨረሻም ወንጀለኛው፣የአምባገነኑ መለሰ ዜናዊ አፈቀላጤ(ጆሴፍ ጎብልስ) በቁጥጥር ሥር ዋለ::በዚህም ብዘዎች ንጹሕ አየር መተንፈስ ይጀምራሉ ”

አና ጎሜዝ ከአቶ በረከት ስምኦን በ1997 ምርጫ ወቅት የነበረውን ውዝግብ አስመልክቶ ለቢቢሲ አማርኛው የዜና ክፍል ሐቁን እንዲህ ተንፍሰው ነበር፤

“ነገሩ በ 1997 ዓ.ም እኔ የአውሮፓ ምርጫ ታዛቢ ቡድንን መምራት በጀመርኩበት ጊዜ የሆነ ነው::እሱ ያኔ የመንግሥት ተወካይ ነበር::ከእኔና እኔ ከምመራው የምርጫ ታዛቢ ቡድን ጋር እሱ ነበር በየጊዜው የሚገናኘው::የፕሮፓጋንዳ ሚኒስትርም ነበር::በዚያ የታዛቢ ቡድን አማካኝነት እኔና የቡድኔ አባላት የተደረገውን ማጭበርበር ስላጋለጥን ነው በእኔ ላይ ቂም ይዞ የቆየው:: ከበረከት ሰምኦን ጋር በጁን 8 2005 የነበረንን ንግግር መቼም አልረሳውም::በመሀል አዲስ አበባ የተደረገውን ግድያ ስምቼና ሆስፒታሎችን ጎብኝቼ ወዲያውኑ አገኘሁት::የጎበኘኂቸው ነበር ::ባየሁት ጉዳይ ላይ መግለጫ እደምሰጥ በረከትን ነገርኩት::እርሱ በዚህ ውሳኔዬ ተበሳጨ::ይባስ ብሎ ለተፈጠረው ግድያ ተጠያቂው የአውሮፓ ኅብረት ነው አለኝ::ይህ ብሽ የሆነ ሐሳብ ነው::”

## በአቶ በረከት ስምኦን እና በቶ ታደሰ ጥንቅሹ እስር ታዋቂ ሰዎች ምን አሉ

*የሕወሓት ሥራ አስፋጻሚ አባል አቶ ጌታቸው ረዳ*

የሕወሓት ሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት አቶ ጌታቸው ረዳ በአቶ በረከት ስምኦን እና ታደሰ ጥንቅሹ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በሕግ ሥላ ሥር መዋላቸውን ተከትሎ ለቢቢሲ የአማርኛ ዜና አገልግሎት ሁለቱ ከፍተኛ አመራሮች በሙስናው ረገድ የሚታሙ አለመሆናቸውን በመግለጽ እስሩን ፓለቲካዊ አንድምታ እንዳለው ተናግረው ነበር፤

“እንደ ፓርቲው ከፍተኛ አመራር እርምጃው አስደንቆኛል::ከሙስና ጋር በተያያዘ ስማቸው የሚነሳ በርካታ ሰዎች አሉ፤መናገር የምፈልገው በረከትና ታደሰ ግን ከዚህ አንጻር በመጨረሻው ደረጃ ላይ ሊቀመጡ የሚችሉ ናቸው::ነገር ግን ስለማንም በርግጠኝነት መናገር አልችልም”ብለዋል

## የኢሕድን መሥራች የሆኑት አቶ ያሬድ ጥበቡ

የሚገርም ዜና ነው::የጥረት ቦርድ ሰብሳቢነት የሚያሳስር ከሆነ እማ ከእስር ማን ሊተርፍ ነው::ያውም ጥረት መንግሥታዊ ድርጅት አይደለም::የፓርቲ ቢዝነስ ነው የነበረው::ፍትሕ የፓለቲካ መሣሪያ ይደረግበት የነበረው የእነአቶ በረከት የአገዛዝ ዘመን እንዲያከትም ነበር ትግሉ::አሁን ተስፋ የማደርገው ያ አስከፊ አሠራር አልቀጠለም ብዬ ነው::ለሁሉም ፣ከሦስት ሳምንታት በኂላ ወደ ሸገር ስለማቀና፣እዚያው ደርሼ ሁሉንም አየዋለሁ::

## የቀድሞው የአዲስ ነገር ጋዜጣ ሥራ አስኪያጅ አቶ መስፍን ነጋሽ

ዘመኑ ባይቀር ኖሮ፣የበረከት ስምኦን መታሰር ከመለስ ሞት ያላነሰ ዜና ይሆን ነበር::ልዩነቱ፣መለስ ዕድለኛ ነው::ይኼኛው ቢያንስ ለጊዜው ዕድለ ቢስ ይመስላል::

ለብዙ ሰው ቁም ነገሩ በረከት የታሰረበት ምክንያት አይደለም::መታሰሩ ራሱ፣ለመታሰር መቻሉ ራሱ ነው ብርቁ::ሰውዬው ክፍ ፓለቲከኛ ነበር::አፈናንና ሰቆቃን እንደ ጥሩ የፓለቲካ መሣሪያዎች ቆጥሮ፣በአጠቃቀማቸው ላይ ለመራቀቅ የሞከረ ሰው አድርጌ እቆጥረዋለሁ::አፈናውን ያራቀቀው በመሰለው መጠን የሆነ የላቀ ተልእኮ እንዳሳካ በመቁጠር እየተደሰተ ሳይኖር አይቀርም::ይህን ሁሉ ሲያደርግም፣አገሩንና ሕዝቡን በቅንነት እያገለገለ እንደሆነ ለማስረዳት የሚሞክር ራሱን ጠይቆ የማያውቅ ሰው ይመስለኛል::ጋዜጠኞችንና ፓለቲከኞችን አድብቶ የሚከላ ሾተላይ ነበር::ዝርዝር ብዙ ነው::

እንዲያም ቢሆን፣አሁን ስለታሰረ ከሚደሰቱት ወገን አይደለሁም::በእስሩና በክስ ሒደቱም ሰብኣዊ ክብሩን የሚነካ ተግባር እንዳይፈጸምበት አጥብቆ ማሳሰብ ይገባል::ያለንበት የሽግግር ወቅት ለእውነተኛ ፍትሕና ርትእ ብዙ የተመቻቸ ባይሆንም፣የተጠርጣሪነት መብቱ ሙሉ ለሙሉ ተጠብቆለት፣ቢያንስ በፍርድ ቤቱ አደባባይ እንደንጹሕ የመቆጠር መብቱ ሳይፈፍ፣አካላዊ ጥቃት እንዳይደርስበት ጥበቃ ተደርጎለት የፍርድ ሒደቱ መካሄድ ይኖርበታል::ይህ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ተጠርጣሪዎች ሊጠበቅላቸው የሚገባ ነው::እነበረከት ለሌሎች የነፈጉትን መብት ልንነፍጋቸው አይገባም::ስሕተት፣ክፋትም በክፋት አይታረምም::

> **አፈናንና ሰቆቃን እንደ ጥሩ የፓለቲካ መሣሪያዎች ቆጥሮ፤በአጠቃቀማቸው ላይ ለመራቀቅ የሞከረ ሰው አድርጌ እቆጥረዋለሁ : :አፈናውን ያራቀቀው በመሰለው መጠን የሆነ የላቀ ተልእኮ እንዳሳካ በመቁጠር እየተደሰተ ሳይኖር አይቀርም**



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

# ዘመን በቃላዊ ግጥም ሲዘከር

‹‹ያ ወጣቱ ልጅ በደዌ ተይዞ፤
ተማሪ ቤት ታየ ሽመል ተመርኩዞ።››

ዘመናችንን እንዘክራለን። አዎ! በእለት ተእለት ወጋችን፤ በፍቅር ትርክታችን፤ በእንጉርጉሯችን፣ በሙሿችን፣ በቅብብሎሻችን፣ በተረታችን፣ በእንካ ሰላንትያችን፣ በበላ ልበልሃችን፣ በዘይቤያዊ አነጋገራችን ሁሉ ዘመናችንን እንዘክራለን። (ዛሬ የምናየው መንቶ ግጥሞችን ብቻ ቢሆንም)

እሱ፡-
‹‹መንደሩን ባቡሩ ከፈለው ለሁለት፤
አንቺ እንደሁ አይገባሽ እንደመር ማለት!››

እሷ፡-
‹‹አውጪው ሆያ ሆዬ ተቀባዩ ለምለም፤
እንደምን ተዳምረን፣ አንድ ሆነን እንክረም!?››

የዘመናችንን ምስል በአፋዊ ሥነጽሑፍ እናስቀምጣለን። አዎ! በእለት ተእለት ወጋችን፤ በፍቅር ትርክታችን፤ በእንጉርጉሯችን ውስጥ ሁሉ በዘይቤ በታሹ፣ ኅብር በለበሱ መንቶ ግጥሞች ዘመናችንን እንዲህ እንዘክራለን።

‹‹እምዬ ኢትዮጵያ አንቺ ቅድስት አገር፤
ልጆችሽ ወደቁ በመስቀሉ ፍቅር።››

‹‹ሥጋ በፍስለታ ሲበላ ተሰቅሎ፤
መካሪ ታጣ ወይ ‹አትግደፉ› ብሎ!?››

እንላለን። ኑሯችን እንዲህ ባለ ንፃሬ ተኩሎ ካልተበጀ፣ ተበጅቶም ካልተቀመጠ ነገ ስለዛሬ ምን ሊተርክልን ነው!? እንደምን ባለ ኪናዊ መንገድስ ዛሬያችንን ለነገ ሊያቀብልልን ነው!? …እንጃለቱ! ያዙ እንግዲህ፤

‹‹ይሄ ሁሉ ሥጋ ታርዶ እየተበላ፣
የምን ፍስለታ ነው የምንስ ቅበላ!?››

መለስ ብለን ደግሞ፤

‹‹በአዲሱ ሚንስትር በልበኛው ሹም፤
እባክሽ ነይልኝ የልቤ ሰላም።››

እንላለን። ‹‹ሰላም ማን ናት?›› ባይ ነገረኛ ቢመጣ እኛ ምን ግዳችን!? የሚጨነቅ ይጨነቅበት። ብቻ እንደ አውዱ፣ እንደ ጊዜውና ቦታው ዘመናችንን እንዲህ በኪነት አበጃጅተን እንሰንዳለን።

‹‹ሰላሜ ጉብሏ ዘንካንታዋ ቆንጆ፤
እንደምን ይፀናል ያላንቺማ ጎጆ።››

…በማለት ውዳሴ እናቀርባለን። …ከዚህም ዝቅ ስንል ደግሞ ሥጋትና ተስፋችንን በአንድ ሰፍተን እንዲህ እናሰናኛለን።

‹‹ከእንክርዳዱ መሀል ቢበቅል አንድ ስንዴ፤
ሊቀበል አልቻለም ጠረጠረው ሆዴ!››

…ዛሬ ላይ ሆነን፣ እንደ አስቴር አወቀ ዘመን "በሰባራ ፎሌ ውሃ አይጠለቅም" ብለን ግጥም አናበጃጅም። ሰባራ ፎሌ ምንድር ነው የተባልን ጊዜ መልሱ ሊጠፋን አይደለምን? ስለዚህ ለዘመናችን ቅርቡ ከፎሌ ይልቅ የቻይና ብርጭቆ ነውና ዘካሪ ግጥማችንን በጉብሏ አታክከን እንዲህ እናሰናኛለን።

‹‹የቻይና ኩባያ ተሰባሪ ነው፤
እመጣለሁ ብለሽ መቅረትሽ ምነው?››

‹‹ቻይና የሠራው እቃ ይሸጣል በጨኸት፤
በዜማ ስጠራሽ አትዪም ወይ አቤት!?››

ዘመናችንን እንዘክራለን። በእለት ተእለት ወጋችን፤ በፍቅር ትርክታችን፤ በእንጉርጉሯችን ውስጥ ሁሉ በዘይቤ በታሹ ግጥሞች ዘመናችንን እንዘክራለን።

‹‹ሽኩርምም ሽኩርምም ሽኩርምም በዪልኝ፤
ካንቺ ጋር መደመር እንደምን ያምርብኝ!?››

…እንላለን። አስተውሉ፤ የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ እና ዘመነኞቹ ዓላማ ነባር ቃላዊ ግጥሞችን መጠየፍ ወይም ማነወር አይደለም። ከእነሱ ጋር እየተገዳደሩም አይደለም፤ በጭራሽ! በነባሩ ቅርፅ እና አቀራረብ የራሳቸውን እየከተቡ እንጂ። ‹‹ትናንት እንደምን አለፈ? ምንስ ተባለ?›› ለሚል የነገ ጠያቂ ማስረጃ እየተዉ እንጂ።

ልብ እንበል፤ ቃላዊ ግጥም ስለከፍታ ብቻ የሚሰብክ የዘገባ አጀንዳ አይደለም፤ ይኸን በየሙዚቃው ሲዲና በየቴሌቪዥኑ ላይ አናጣውም። ይልቅስ ቃላዊ ግጥም የውድቀትንም ሰነድ አብሮ የሚይዝ ነው። እስኪ እኛ ዘመነኞቹ የወደቅንበትን ደዌ እንዲህ እንዘክረው፤

‹‹ብልህ ነው አዋቂ ሲባል ሰዉ ሁሉ፤
አባ-ለዘር ጣለው እንዲህ በቀላሉ።››

‹‹ተምሮ እንዲመጣ የተላከው ልጅ፤
ባለበትር ሆነ፤ ሽመገለ ጃጂ።››

ደግሞ እንመለስና በሥጋ ፈቃዳችን አስታከን ጊዜውን እንዲህ እንኳል።

‹‹በባቡሩ መንገድ እጥርጥር ባለው፤
ዐይንሽን ስፈልግ ጠፋብኝ ምነው!?››

…‹‹ቃላዊ ግጥሞች የተተረኩበትንና የተነገሩበትን ማኅበረሰብ ባህል፣ ሥነልቦና እና አኗኗር ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ የዘመን ስዕሎች ናቸው›› ይባል የለምን!? …ይኸው!

‹‹የካድሬዎች ሱሪ ያልቃል ወደ ቂጡ፤
ሺህ ቢሰበሰቡ መላ አያመጡ።››

‹ሥነ ቃል› እንፍጠር ብሎ መነሳት በራሱ ወፈፌነት ነው ብለው ሊቃውንት ሊያነውሩን ይችላሉ። ስለምን? ሥነቃልን ሥነቃል ካሰኙት ባሕርያት አንዱ አመንጪው ወይም ፈጣሪው በውል የሚታወቅ ባለመሆኑ። የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ እና ባልንጀሮቹ ግን እንዲህ ላለው ትችት ጀርባቸውን ሰጥተው፣ አሻራቸውን ለመተው ይታትራሉ፤ ነባር ቅርፁን በመዋስ የራሳቸውን እንዲህ ይፈጥራሉ።

‹‹ተቃዋሚ ፓርቲ ይበዛል ለምርጫ፤
ሁሉ ይስምሻል እንደ ሰፈር ዋንጫ።››

‹‹ምርጫ ምርጫ አትበል ምርጫ ያርግህና፤
አንተን መርጬ ነው የቀረሁ ጎዳና።››

አባቶች ብቻ የፈጠሯቸውን ተረቶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ቃላዊ ግጥሞች ብቻ እየመዘዝን መጠቀም አግባብ ነውን? በጭራሽ፤ ስለሆነም እንዲህ የዕለት ተዕለት ኑሯችንን በራሳችን አባባል፤ በዘመናችን ቋንቋ እንከትባለን።

‹‹እንደ ዘይት ጠፍተሽ፤ እንደ ስኳር ጠፍተሽ፤
እንደ ውሃ ጠፍተሽ፤ እንደ መብራት ጠፍተሽ፤
…አሳስበሽኛል፤
እንዳቺ ያለ ሂያጅ* ኧረ የት ይገኛል!?››

እኛ ዘመነኞቹ ‹‹ረዥም ግራር ላይ ይሰቀላል ቀፎ›› ብለን እንደ ድሮ አዝማሪ ግጥም አናበጅም። ረዥም ግራር ምንድን ነው? ቀፎስ? ተብለን ብንጠየቅ ለእኛም ሆነ ለእኛ ዘመነኛ መልሱ ጭንቅ ነው። ባይሆን አዝማሪው፤

‹‹ረዥም ግራር ላይ ይሰቀላል ቀፎ፤
ማን ይደርሳል ካንቺ ባጅሬ ላይ አልፎ።››

ብሎ ያንጎራጎረውን እንዲህ እንለው ይሆናል፤

‹‹ረዥም ሕንፃ ላይ ይሰቀላል ዲሽ፤
ከእጄ መውጣትሽ ነው ባለሹም ካየሽ።››

…ዘመናችንን እንዘክራለን። አዎ! በእለት ተእለት ወጋችን፤ በፍቅር ትርክታችን፤ በእንጉርጉሯችን ውስጥ ሁሉ በዘይቤ በታሹ፣ ኅብር በለበሱ መንቶ ግጥሞች ዘመናችንን እንዲህ እንዘክራለን።

‹‹ወጡ ሳይሠራ እንጀራው ሳይወጣ፤
ዋናው የሚያባላን እንግዳችን መጣ።››

እነሆ መቋጫ፤

‹‹ስንቆላ ስንታመስ፤
ስንታመስ ስንቆላ
ኖረን፣ ኖረን፣ ኖረን፤
የማንበስል ምን ጉዶች ነን!?››

…አለ ጭቁኑ ባቄላ የጋመ ምጣድ ላይ ሆኖ።

# “የወያኔ ትልቁ ክህደት ሀገሪቱን ወደብ አልባ ማድረጉ ነው”

## “አሰብን የቆረቆረው የእኔ አባት ነው”

## አቶ ነአምን ዘለቀ

*አቶ ነአምን ዘለቀ ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት በአሜሪካና በሌሎች የባህር ማዶ ሀገሮች አምባገነኑን የወያኔን ሥርዓት ለመቃወም በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሪ ተዋናይ በመሆን ስማቸው ይጠቀሳል፡፡ የአስራ ስድስት ዓመት ታዳጊ ወጣት እያሉ ከሀገር የተሰደዱት አቶ ነአምን ዘለቀ ለሠላሳ ሁለት ዓመታት በአሜካን ሀገር ቆይተው በ 2010 ዓ.ም ጳጉሜ ወር ላይ ወደ ሀገር ቤት ከገባው አርበኞች ግንቦት ሰባት አባላት ጋር በመሆን የናፈቋትን ሀገርና ወዳጆቻውን ለማግኘት በቅተዋል፡፡*

*የአርበኞች ግንቦት ሰባት ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑትና በፖለቲካው ዘርፍ ጉልህ ሥፍራ ያላቸው አቶ ነአምን ዘለቀ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ጉዞ ውስጥ የራሳቸውን አሻራ ማስቀመጥ የቻሉ የትግል ሰው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እኚህን የረዥም ዘመን የትግል ታሪክ ያላቸውን አንጋፋ የፓለቲካ ሰው፣ አቶ ነአምን ዘለቀን የግዮን ጋዜጠኞች ፍቃዱ ማ/ወርቅ እና ሮቤል ምትኩ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በሰፊው አነጋግረዋቸዋል፡፡ መልካም ቆይታ*

**ግዮን፡- የ16 ዓመት ልጅ ሆነህ ነበር ከአገር የወጣኸው፤ ለመሆኑ አጋጣሚውና ምክንያትህ ምን ነበር?**

**ነአምን፡-** ከሀገር የወጣሁበት አጋጣሚ የተፈጠረው በጊዜው ከነበረው ፖለቲካዊና ወታደራዊ እንቅስቃሴ አኳያ ነው:: አስራ አንደኛ ክፍል እያለሁ ብሔራዊ ውትድርና ስለነበር፤ ይሄ ነገር ቤተሰቦቼን በእጅጉ ስላስጨነቃቸው አሜሪካን ሀገር ያለ አጎቴ እኔና ወንድሜን ስፖንሰር አድርጎ ወደ እዛ ወሰደን:: የዛሬ ሰላሳ ሁለት ዓመት ነው ከሀገር የወጣሁት::

**ግዮን፡- ደርግ ከወደቀ በኋላ ወደ ሀገር ቤት ያልተመለስከው ለምንድን ነው?**

**ነአምን፡-** በደርግ ጊዜ አሜሪካን ሀገር ዩኒቨርስቲ ትምህርት ላይ ነበርኩ:: በተማሪ ቪዛ የሄድኩ በመሆኑ ወደ እዚህ መምጣቱ አስቸጋሪ ነው:: ከዚህ በሄድኩ በአምስተኛው ዓመት ወያኔ/ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ተቆጣጠረ፤ አባቴ በወቅቱ በኢትዮጵያ ባህር ኃይል ውስጥ ትልቅ ቦታ ስለነበረው ፤ እሱ በመታሰሩ ያልታሰበ ችግር ተፈጠረ ማለት ነው::

ለነገሩ በሙያው የሚያገለግልና የኢሠፓ አባል ስላልነበረ ከስድስት ወራት እስር በኋላ ተለቀቀ:: በኋላ እንደውም ጡረታውን ሁሉ አስከብሮ ነበር::

**ግዮን፡- አባትህ ኮማንደር ዘለቀ ከኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ የባህር ኃይል መኮንኖች መሀል አንዱ መሆናቸው ይነገራል:: እስኪ ስለ እርሳቸው እንዳንድ ነገሮችን አጫውተን?**

**ነአምን፡-** እዚህ ሀገር ባህር ኃይል በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ኦፊሰር መኮንኖችን በኖርዌጂያኖች አሰልጥኖ ሲያስመርቅ፣ ከአርባ በላይ ከሆኑት ምርጥ ሙያተኞች መሀል አንደኛ ሆኖ በመውጣት የንጉሰ ነገስቱን ሽልማት የተሸለመው የእኔ አባት ነው::

ባህር ኃይል ውስጥ የሎጀስቲክስ፣ የኢንጂነሪንግና ኤግዜኪውቲቭ አመራር የሚባሉ ሶስት ክፍሎች አሉ:: ከአመራሩም ውስጥም ሆነ ከአጠቃላይ ዘርፎቹ ውስጥ አንደኛ በመውጣቱ፣ ወደ ፊት የባህር ኃይሉ ዋና አመራር ይሆናሉ ተብለው ከሚገመቱት በጣም ጥቂት ሰዎች መሀል አንዱ ነበር:: ለውጡ መጥቶ ደርግ ስልጣን ላይ ሳይወጣ ወይም አብዮቱ ሳይፈነዳ መጨረሻ አካባቢ የባህር ኃይል የዘመቻና የመገናኛ ኃላፊ ሆኖ ነበር፤ ሶስተኛ ሰው ማለት ነው:: ዋናው የንጉሰ ነገስቱ ልጅ አድሚራል እስክንድር ናቸው::

ደርግ ሲመጣ ጄነራል አማን እያሉ ኮሞንዶር ጣሰው ደስታን የባሕር ኃይል አድርጎ ሾሙ:: ያኔ ደርግ ከባህር ኃይል፣ አየር ኃይል ከምድር ጦር የተማሩትን ኦፊሰሮች፣ ውጭ ሀገር ሄደው ከፍተኛ ትምህርት ያላቸውንና በደንብ የታወቁትን ሰዎች ከወታደራዊ ተቋሙ እያወጣ ሲቪል በሆኑ መ/ቤቶች ላይ ሚኒስትር ወይም ደግሞ የተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎች ኃላፊ እያደረጉ ይሾም ነበር:: አባቴም የባህር ማመላለሻ አስተዳደር ለሚባለው፣ ተጠሪነቱ ለአሰብና ለምፅዋ ለሆነው ለዚህ ተቋም ኃላፊ ሆኖ እንዲሰራ በመመረጡ በቦታው ረዘም ላሉ ዓመታት ሠርቷል::

**ግዮን፡- የአሰብና የምፅዋ ወደብ ጉዳይ ከተነሳ ከባህር ኃይሉና ከውሃ አስተዳደሩ ጋር በተያያዘ አባትህ ኮማንደር ዘለቀ እጅግ የገዘፈ የሥራ ታሪክ እንዳለችው በብዙዎች ዘንድ ይነገራል::በእርሳቸው ሥር ከነዚህ ወደቦች በተጨማሪ ሌሎች ታላላቅ ፕሮጀክቶችም እንደተከናወኑ ይታወቃል እስኪ እነርሱን በዝርዝር አስቀምጣቸው?**

**ነአምን፡-** እርሱ የተሾመበት የዛን ወቅቱ ኃላፊነት “የአሰብና የምፅዋ፣ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ውሃዎች” የሚባል ተቋም ነው:: በሀገር ውሃዎች ውስጥ እንግዲህ ጣና አለ፣ ባሮ አለ፣ ጎርጎራ አለ፣ አርባ ምንጭ የሚገኘው አባያና ጫሞ የተሰኙት ታላላቅ ፕሮጀክቶች ይገኛሉ::

**ግዮን፡- ይህንን ተቋም እስከ ደርግ ውደቀት ድረስ የመሩት እርሳቸው ነበሩ?**

**ነአምን፡-** አስራ ሰባት ዓመት ሙሉ ኃላፊነቱን የያዘው እርሱ ነው:: ደርግ ሥልጣን ላይ እንደወጣ ነበር የመረጠው፤ እሱም ከተመረጠ ከአንድ ዓመት በኋላ ጥናት አስጠንቶ፣ ያ አስተዳደር “የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ባለስልጣን” ተብሎ በአዋጅ እንዲቋቋም፣ እንደገና እንዲዋቀር ተደርጓል:: በዛ ተቋም ዋና አስተዳዳሪ በመሆን ወያኔ እስከገባበት የመጨረሻ ሰዐት ድረስም ሰርቷል::

አሁን እዚህ ከመጣሁ ከጥቂት ቀናት በፊት ባህር ዳር ሄጄ ነበር፤ ጣና ውሃው ጋር ሲወስዱኝ ልጆች ሆነን አባቴ ከውጭ ያስመጣት “ጣና ነሽ” የምትባል ትልቋ መርከብ አርጅታ፣ አሁንም እየሰራች ተመለከትኳት:: ካፕቴኑ ስጠታው አላምረው ይባላል፤ የእሱ አባት ከእኔ ▶



አባት ጋር ሠርተዋል:: አጋጣሚው በጣም ገርሞኝ የማስታወሻ ፎቶ አብረን ተነሳን:: እንግዲህ ወደኋላ መለስ ብለን ካየን የጎርጎራ፣ የጣና፣ የባሮ፣ የአኮቦ፣ የአርባ ምንጭ፣ አሰብና ምፅዋ ሁሉ በአባቴ አስተዳደር ስር ነበሩ ማለት ነው::

***ግዮን፡- ኮማንደር ዘለቀ በኃላፊነት ላይ በነበሩበት ሰዐት ከከፍተኛ የደርግ ባለስልጣናት ጋር ይጋጩ ነበር፤ ኃይለኛና እልኸኛ ሰውም ነበሩ ማለት ይቻላል?***

***ነአምን፡-*** ግጭቱ በስራ ስለሚያምን ነው፣ ፀቡ የሚፈጠረው:: ቀደም ሲል እንደገለፅኩት የኢሠፓ አባል አልነበረም:: ፈፅሞ ፖለቲካ ውስጥ አይገባም:: ከፕሬዝዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም ፣ ከካድሬዎችና ከብዙ የደርግ ሰዎች ጋር በአንዳንድ ጉዳዮች ይጋጭ ስለነበረና ኃይለኛም ስለሆነ ጓድ መንግሥቱ “ግድ የለም እርሱን ተውት” ብሎ ከለላ እያደረገለት የሚሰራ ሰው ነበር::

የሚገርመው በእርሱ ደረጃ ያሉ ሰዎች እንዳሉ የኢሰፓ አባል ናቸው፣ በእሱ ስር ያሉ ከሶስት መቶ በላይ ሰዎችም የኢሰፓ አባል ነበሩ:: እርሱ ግን የፖሊተካ ሰው መሆንን አልፈለገም:: ወያኔ ሲያስረው ስድስት ወር ብቻ የቆየበትም ምክንያት ይሄ ነው:: ሁሌም በስራ ነው የሚያምነው:: እንደ ሌሎች ኃላፊዎች አዲስ አበባ ቢሮ ውስጥ ሆኖ አልነበረም ትዕዛዝ የሚሰጠው፤ ረዥም ወራት ከእኛ ርቆ ሥራው ላይ ነው የሚያሳልፈው:: በአራትና አምስት ወር መሀል ብቅ እያለ ነበር ለአንድ ወር ብቻ አዲስ አበባ የሚቀመጠው::

ወያኔ ሥልጣን ይዞ ጡረታ ከወጣ በኋላ ወደ አሜሪካ ልንወስደው ሞክረን ነበር፤ እርሱ ግን አልፈለገም:: መጨረሻ ላይ በጣም ታምሞ የዛሬ አስር ዓመት አካባቢ መጣ፤ እኔ ቤት ሆኖ ለበርካታ ወራት ከወንድሜ ጋር አስታመምነው:: ግን ችግሮቹ የተደራረቡ ስለነበር ሕይወቱ አለፈ፤ አስከሬኑን ወደ እዚህ ልከን የተቀበረው ሀገር ቤት ነው::

***ግዮን፡- ከሀገር ከመውጣትህ በፊት ከአባትህ ጋር ወደ አሰብና ምፅዋ ወደቦች ሄደህ ታውቃለህ? በተለይ እርሳቸው ከአሰብ ከተማ መስፋፋት ጋር ይያዛሉና::***

***ነአምን፡-*** እኔና ወንድሜም አሰብን፣ ምፅዋን፣ አስመራን አባታችን በተገቢው ሁኔታ አሳይቶን ነው ወደ አሜሪካ የሄድነው:: በእዛን ጊዜ ትውስታዬ አሰብና ምፅዋ ግዙፍ፣ ትልልቅ የኢትዮጵያ ወደቦች ነበሩ፤ በጣም የሚያምሩ ሞቃት ቦታዎች ናቸው:: ባህር ኃይሉንም ምፅዋ ሄደን አይተናል::

እንዳልከው የእኔ አባት በብዛት የሚታወቀው ከአሰብ ጋር በተያዘ ነው:: አሰብን ከዜሮ አንስቶ ትልቅ ከተማ አድርጓታል:: ወደቡን ብቻ ሳይሆን ከተማውን ጭምር ለውጦታል:: በተጨማሪ ሃሌብ የሚባል ቦታ ላይ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ጀምሮ ነበር፤ እኛ የሄድን ጊዜ በጅምር ላይ ነበሩ:: በኋላ የጀልባ ፋብሪካ፣ የማሪታይም አካዳሚ እና ሶስተኛ ወደብ እዛ ቦታ ላይ እየተሰራ ሊያልቅ ሲል ነው ሻዕቢያና ወያኔ የገቡት:: ከበርካታ ዓመታት በኋላ በግንቦት ሰባት አባልነቴ ለትግል ኤርትራ በሄድሁበት ወቅት ቦታዎቹን ደግሜ ሳያቸው የነበሩት ትላልቅና መልካም ነገሮች በሙሉ እንዳልነበር ሆነዋል::

***ግዮን፡- በወጣትነትህ ያየሃቸው፣ የኢትዮጵያ የነበሩት የአሰብና የምፅዋ ወደቦች አሁን በሌላ ሀገር እጅ ገብተው ፣ ሀገሪቷ ወደብ አልባ ሆና ስትመለከተው ከድሮ ትዝታህ ጋር በተቆራኘ ምን ተሰማህ?***

**ነአምን፡-** ትልቁ የወያኔ ክህደት ይሄ ነው:: በወቅቱ ከሻዕቢያ ጋር ተደራድሮ ለኢትዮጵያ በሚጠቅም መልኩ፣ የአሰብን ወደብ ኢትዮጵያ ባለቤትም፣ ተጠቃሚም እንድትሆን ማድረግ ይቻል ነበር:: ይሄን እነ ኸርማን ኮህንም ገልፀውታል:: ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የቆመ መንግስት ቢኖር ኖሮ፤ ቢያንስ አሰብን ተደራድሮ ኢትዮጵያ በባለቤትነት እንድትይዘው ማድረግ ይቻል ነበር::

የባህር በርም ሆነ ባህር ኃይል ለአንድ ሀገር ወሳኝ ነው:: አሜሪካንን አሜሪካ ያደረጋት የባህር በሯ ነው:: የባህር ኃይሏ ዝም ብሎ ነገር ሳይሆን፤ ለዓለም ዓቀፍ ንግድም፣ የኢኮኖሚ ልማትም ሆነ ሌሎች ነገሮችን በሙሉ የሚቆጣጠሩት እነኚህ ባህር ኃይሎች ናቸው:: ዘጠና በመቶ የዓለም ንግድ የሚካሄደው በባህር ላይ ነው:: በዚህ ላይ አንድ ጥናት እያደረግሁ ነው፤ በቅርቡ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅቼ አሳትምዋለው::

የወያኔ ትልቁ ክህደትና በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመው አንዱ ደባ ሀገሪቷን ባህር አልባ ማድረጉ ነው:: ይሄ ጉዳይ ለእኔ ከኢትዮጵያዊነቴም በላይ ግላዊ በሆነ መልኩም ይሰማኛል:: አባቴ በእነዚህ ቦታዎች ላይ ብዙ ዕድሜውን፣ ዕውቀቱን፣ አጠቃላይ የሕይወት ሂደቱን በሙሉ ኢንቨስት አድርጎበታል:: ለዘመናት በርካታ ፕሮጀክቶችን ከመሬት አንስቶ ነው እላይ ያደረሳቸው:: ከሚገባው በላይ እንደደከመ አውቃሁ::

አሁን ሥልጣን ላይ ያለው የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ መንግስት የባህር ኃይል እናቋቁማለን ማለቱ ጥሩ ነው ፤ግን ይህ የባህር ኃይል በምን ወደብ ላይ ነው የሚመሰረተው:: ያለ ወደብ ባህር ኃይል ማቋቋም ከባድ ነው:: ጠ/ሚኒስትሩ የሚያቋቁሙት ባህር ኃይል በምን ወደብ ላይ እንደሚመሰረት ግልፅ አይደለም:: ይሄ ነገር መስተካከል አለበት፤ አሁን እንደሚገባኝ ከሆነ የኢትዮጵያ መንግስት ከኤርትራ ጋር የፈጠረው ኢዲስ የሰላም ስምምነት ይመስለኛል ወደ እዛ አይነት ሃሳብ እንዲያመራ ያደረገው:: ደርግም ሆነ ንጉሰነገስቱ፣ ፌዴሬሽኑም ጭምር የኤርትራን ህዝብ ገፍቶታል:: ከዛም አልፎ ተርፎ አንዳንድ የተፈፀሙ አላስፈላጊ ነገሮችና ስህተቶች የተነሳ ሻዕቢያዎች ወደያዙት አቅጣጫ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል::

መንግስቱ ኃ/ማርያም ከኤርትራ ጋር ውስጥ ውስጡን ብዙ ድርድሮች አድርጓል:: በአንድ ወቅት ሻዕቢያ በጣም በተዳከመበት ጊዜ የፌደሬሽንን ሀሳብ ተቀብለው ነበር፤ እነ መንግሥቱና አክራሪ አመራሮች ናቸው እምቢ ያሉት "አሰብን እንስጥና እንስማማ" ዓይነት ደረጃ ላይ ሁሉ ተደርሶ ነበር:: ያንንም አይሆንም በማለታቸው መጨረሻ ያው እንዳያችሁት ሁሉም ነገር ተጠቅልሎ ሄደ:: ይሄ ለኢትዮጵያ ትልቅ ጉዳት ነው::

**ግዮን፡- የአቶ ገብሩ አስራት መጽሐፍን ጨምሮ በርካታ የወያኔ ባለስልጣናት በተለያዩ አጋጣሚዎች "አሰብን ሻዕቢያ አሳልፎ የሰጠው መለስ ዜናዊ ነው፣ እጃችን የለበትም" ሲሉ ይሰማል:: በዚህ ጉዳይ በርግጥ መለስ ብቻ ነው ተጠያቂው?**

**ነአምን፡-** መለስ ዜናዊ ከሌሎቹ ወያኔዎች የበለጠ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያለውና ምንም አይነት የኢትዮጵያዊነት ስሜት ያልፈጠረበት ሰው ነበር:: ነገር ግን ያ ውሳኔ የመለስ ብቻ ነው ብዬ ለመቀበል በጣም እቸገራለሁ:: በወቅቱ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት ሳይመጣ ወያኔ በጋራ አመራሩ ነበር የሚታወቀው:: መለስ ዋና መሪ ቢሆንም ሕወሓት በጋራ ነበር የሚወስነው:: እንዲህ ዓይነት ትልቅ ውሳኔ በመለስ ብቻ የተደረገ ነው ብሎ መቀበል በጣም ያስቸግራል::

ስለዚህ እነ ገብሩ አስራትም ሆነ ሌሎችም የሚያውቁትና አብረው የሚወስኑት ነገር ነበር:: ኤርትራ ትገንጠል ብሎ የሻዕቢያን አቋምና ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ የመደገፍ ነገር የተጀመረው ገና በእንጭጩ፣ በትግል በርሃ በነበሩበት ጊዜ ነው:: ይህ ከሆነ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚል አሰብን ለመውሰድ ወያኔ የተደራደረበትን ሁኔታ አላውቅም:: የመስጠት አቋማቸው መጀመሪያ የነበረ፣ እስከ መጨረሻም የቀጠለና ሀገሪቱን ባህር አልባ ያደረገ የክህደት ውሳኔ፣ የወያኔ ጠቅላላ አመራር እንጂ የመለስ ብቻ አይደለም:: ሁሉም በጉዳዩ ተጠያቂ ናቸው::

ሕወሓቶች በግልፅ እንደምታውቁት የድርጅቱን ጥቅምና ፖለቲካ ለማስቀጠል እንደ እንሽላሊት ከለራቸውን እየቀያየሩ እንኳን አሰብን ሁሉንም ነገር ለመሸጥ ወደኋላ እንደማይሉ ነው ሪከርዳቸው የሚያስረዳው:: የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት ምንም የማይጨንቃቸው፣ ምንም ነገር ለመፈፀም ግድ የማይሰጣቸው ሰዎች እንደሆኑ የድርጅቱ ታሪክ ያረጋግጣል:: በዛ ቢባል ለትግራይ ጥቅም እንጂ ኢትዮጵያ ለምትባል ሀገር ፍቅርም፣ ክብርም እንደሌላቸው፣ ብሔራዊ ስሜትም እንዳልፈጠረባቸው ያየነው:: ይሄ ደግሞ የመለስ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ወያኔዎች እምነት ጭምር ነው::

**ግዮን፡- ገና በወጣትነትህ ወደ አሜሪካ ከመጓዝህ አኳያ በቀጥታ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ የጀመርከው መቼ ነው? የአባትህ የሀገር ፍቅር ስሜት ተፅዕኖ አድርጎብሃል?**

**ነአምን፡-** እሱ እንዳለ ሆኖ እ.ኤ.አ በ19 93 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሲገደሉ፤ ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ ኢ.ድ.ኃ.ቅ በሚባለው ድርጅት አማካይነት ተዘጋጅቶ ነበር:: ያኔ ሰልፍ ወጣሁ፣ ከዛን ጊዜ ጀምሮ በብዙ ድርጅቶች፣ መድረኮችና በበርካታ የትግል እንቅስቃሴዎች በሙሉ አቅምና ጊዜዬ ስንቀሳቀስ ነበር:: ለሀያ ስድስት ዓመት ንቁ የፖለቲካ ተሳታፊ ሆኛለሁ::

በወያኔ ላይ ከፍተኛ እልህና ቁጭት ነበረኝ:: ከጊዜ ወደ ጊዜ በአንድ ዘር ላይ የተመረኮዘ የበላይነት፣ ሌላውን ያገለለ፣ የገፋ እንቅስቃሴ በፖለቲካውም፣ በሚሊተሪውም፣ በኢኮኖሚውም ላይ መንፀባረቁ ስርዓቱ ለኢትዮጵያ የማይበጅ መሆኑና ይሄንንም መታገል እንዳለብኝ አሳይቶኛል:: በደኅንነቱ፣ በተለያዩ የስልጣን ዕርከኖችና የቢዝነስ ዘርፎች የአንድን ብሔር የበላይነት ብቻ አስጠብቆ ለመቆየት የመሰራቱ ነገር፤ በተጨማሪም የሚገደለው፣ ያለ አግባብ የሚታሰረው፣ ፍትህ ያጣውና አረመኔያዊ ተግባርና ግፍ የሚፈፀምበት ህዝብ ጉዳይ በራሱ ያሳዝነኝም፣ያበሳጨኝም ነበር:: ልጅ ሆኜ ሰዎች ሲደባደቡ ለተጠቃው አግዛለሁ፤ ወይም እገላግላለሁ:: ይሄ የሰዎችን ጥቃት የማይፈቅደው የተፈጥሮ ባህሪዬ የምችለውን ነገር በፖለቲካው ውስጥ እንዳደርግ፣ ጨካኙንና ዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ በይፋ እንድታገለው አስገድዶኛል::

**ግዮን፡- የመጀመሪያው የፖለቲካ ድርጅትህ ማን ነበር?**

**ነአምን፡-** በእነዚህ በጠቀስኩልህ ዓመታት በውጭ በተካሄዱ ትላልቅ ወያኔን በሚቃወሙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁሉ በዋና አደራጅነት እኔ አለሁ:: ከእነ ታማኝ በየነ፣ አበበ ገላውና በሚታወቁት አክቲቪስቶች የተቋቋመ እንቅስቃሴ ውስጥ ወይ እኔ አቋቁሜ እነሱ ናቸው የገቡበት፤ ወይም አብረን ነው ያቋቋምነው:: መጀመሪያ ኢትዮጵያን ሬጅስተር የሚባል መጽሔት ላይ ዋና አዘጋጅ ሆኜ ከእነ ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌና ከሌሎች ጋር ሆነን ከ1994 እስከ 2000 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ሰርተናል:: የመጽሔት ስራ ያው እንደምታውቁት ከባድና ፈታኝ ነው፤ ግን እሱን እየሰራሁ በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ወጣቶች እንቅስቃሴ መስራች አባል ነኝ::

በዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ ወጣቶች ማህበር በሰሜን አሜሪካ መስራች አባል ነኝ:: ብዙ ነገሮችን በተነሳሽነት መስርቻለሁ:: ከአምባሳደር ካሳ ከበደ ጋርም በኢትዮጵያ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሾርት ሬዲዮ ላይ ፕሮጀክት ኮርድኔት አደርግ ነበር:: በዋሽንግተን ዲሲ በተደረጉ ትላልቅ ኮንፍረንሶች፣ ሰልፎች፣ የግብረ ኃይል እንቅስቃሴ ላይ ለበርካታ ዓመታት ከተለያዩ የፖለቲካና ሲቪክ ድርጅቶች ጋር በመሆን የሚቋቋሙትን ግብረ ኃይሎች በማስተባበርና በመምራት ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጌያለሁ:: የምሁራን ኮንፍረንሶችን በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ለበርካታ ጊዜያት ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመሆን አዘጋጅተናል::

በፓርቲ ደረጃ እ.ኤ.አ 1994 ላይ ትግል በጀመርኩ ስድስት ወር አካባቢ የኮ/ጎሹ ወልዴ "የመድህን ፓርቲ" አባል ሆንኩኝ::ሰፊ እንቅስቃሴ ነበረኝ፤ በኂላ ወደ ኢትዮጵያ ሬጅስተር ስሄድ በመድህን አባልነት በይፋ አልንቀሳቀስም፤ የመጽሔት አዘጋጅ ስለሆንኩ:: ግን መድህንን እደግፍና እረዳ ነበር::

ብዙም ሳይቆይ ከኮ/ል ጎሹ ጋር አንዳንድ አለመግባባት ተፈጠረ፤ ጀነራል ኃይሌ መለስን ለመርዳት ስንሞክር ኮ/ል ጎሹ ፍቃደኛ አልሆነም:: በዚህም ምክንያት ከአመራር ጀምሮ፣ ሥራ አስፈፃሚ ውስጥ የነበሩ ሰዎችና ጉልህ ሚና የነበረን ሌሎች አባላቶች አንድ ላይ ሆነን ከዛ ተገንጥለን በመውጣት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት አርበኞች ግንባር የሚባል ድርጅት ጀነራል ኃይሌ የሚመሩት፣ ከእነቱሃትል እና ሌሎች የኢሰፓ ኦፊሰሮችና ወታደሮች የነበሩበት አምስት ድርጅት ተጣምሮ የፈጠረው እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ጀመርኩ::

የዕድል ጉዳይ ሆነና የሻዕቢያና የወያኔ ጦርነት ሲጀመር ጄነራል ኃይሌ ታሰሩ፤ ሌሎችም አመራሮች ታሰሩ:: የህዝቡም ትኩረት ወደ ጦርነቱ ተሳበና ውጭ ሀገር፣ ሀገር ውስጥም ያለው በሙሉ ሻዕቢያን ለመምታት በሚል የወያኔ ደጋፊ ሆነ:: በዛ ምክንያት ይሄ ድርጅት

ቀሪውን ቃለ ምልልስ በገጽ 18 ይመልከቱ

## አንደበት



"ሶማሌ ክልል ሕዝቡ ሲጨፈጨፍ ዝም ብለው ሲመለከቱ የነበሩ አመራሮች ናቸው፡፡ ሕዝቡን አስመትተውታል፡፡ ሰሜን ጎንደር ጭልጋ ላይ ሠራዊቱ ትርጉም ያለው ሥራ እየሠራ አይደለም፡፡ ሠራዊቱ ትርጉም ያለው ሥራ ባለመሥራቱ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ግጭቶች ይስተዋላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሠራዊቱ መሪዎች በአግባቡ ባለመሥራታቸው የመጣ ነው፡፡ እነዚህ የሠራዊቱ መሪዎች ሜቴክ ሲዘርፍ ፣አብረው ሲዘርፉ የነበሩ፤ ሜቴክ ጥሩ ሠርቷል ሲሉ የነበሩ ናቸው፡፡"

***ጀነራል ተፈራ ማሞ ዘመን መጽሔት ጥር 2011 ዓ.ም***

---



"ማክሰኞ እና ሐሙስ ጠዋት ከ12፡00 እስከ 2፡00 ሰዐት ድረስ 'ብሪፊንግ ሀወርስ' ነው፡፡ ፕሬዝዳንቱ ማልደው በመነሳት ቢሯቸው ይገባሉ፡፡ ቀድመው የሚደርሱት ዶ/ር አስማማው ቀለሙ ከብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮች ተነሥተው እስከ ዓለም-ዐቀፉ የ'ሴኩሪቲ' ሁኔታ ያሰባበሱትን መረጃ በትንተና አስደግፈው ሲያቀርቡ፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም በታላቅ ጥሞና ተውጠው የቀረበላቸውን ቡና እየጠጡ ያዳምጧቸዋል፤ አልፎ-አልፎም ማስታወሻ ይይዛሉ፡፡"

***ዶ/ር አስማማው ቀለሙ ፍትሕ መጽሔት ጥር 2011 ዓ.ም***

---



"የሽግግሩ ሒደት በእነዚህ ኹለት ተስፋና ሥጋት መካከል የተተከለ ነው፤ እነዚህን ኹለት ክስተቶችንም በእኩልነት ያስተናግዳል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት በጨቋኝ ወይም አምባገነን ሥርዓት ስር ታፍነው(ታምቀው) የቆዩ የሕዝብ አስተያየቶች በዚህ ወቅት ይፈነዳሉ፡፡ ሁሉም ሰው የፈለገውን ነገር ያወራል፣ የፈለገውን ይናገራል፤ በእውነትም በውሸትም ያመነባቸውን ነገሮች እውነት አድርጎ ይነሳል፡፡ የለውጥ ጊዜ ስለሆነ የተደራጀውም ቡድን ራሱን የተሻለ ሥልጣን ለማግኘት፣ በተሻለ ለመጥቀም የሚያደርገው ስትራቴጂካዊ እንቅስቃሴዎችም አሉ፡፡"

***ዶ/ር አወል ቃሲም አዲስ ማለዳ ጥር 11 ቀን 2011 ዓ.ም***

---



"ኦነግ በወለጋ ሕዝብ ዘንድ ድሮ ተቀባይነት ነበረው፡፡ አሁን ግን የአቶ ለማ መገርሳ ወገኖች ወለጋን በአስተሳሰብ አሸንፈዋል፡፡ ተቀባይነታቸውም ከኦነግ በተሻለ ጨምሯል፡፡ ኦነግ ሊያሸንፋቸው አይችልም፡፡ በወለጋ ኦነግ ተቀባይነት አለው በሚል የሚወራው ወሬ የድሮውን እውነታ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እኔ በቂ መረጃ አለኝ፡፡ አሁን እዚያ አከባቢ ኦነግ የበላይ አይደለም፡፡ የወለጋ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነቱን አጥብቆ የሚወድ ነው፡፡ እመነኝ፣ የወለጋ ሕዝብ አሁን የኦነግ አይደለም፡፡"

***አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ኢትዮጲስ ጥር 12 ቀን 2011 ዓ.ም***

## ተሞክሮ

በዚህ ዓለም ላይ ምንም ምስጢር የሚባል ነገር የለም፡፡ ለአንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰዎች እቅዴን አሳየኋቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ 900ዎቹ እቅዴን በፅኑ ተቃወሙት፡፡ 300ዎቹ ግን ቀና ምላሽ ሰጡኝ፡፡ ከ300ዎቹ ውስጥ 85ቱ ትልሜን ለማሳካት አንዱት ጋት ፈቀቅ ለማለት ተነሳሽነት ለማሳየት አልዳዱም ነበር፡፡ በጊዜ ሂደት ከ85ቱ ውስጥ 35ቶቹ ቁርጠኛ መሆን ቻሉ፡፡ ከ35ቱ ውስጥ ደግሞ 11ዱ ባለጠጋ አደረጉኝ፡፡

ቢልጌትስ

## አስደንጋጭ ዜና

እ.ኤ.አ በጃንዋሪ 17 2019 የወጣው ሪፖርት ይፋ እንዳደረገው ከሆነ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በየዓመቱ ከሩብ ሚሊየን በላይ ሰው ይህቺን ዓለም በሞት ይሰናበታል፡፡ከዚህ ቀደም በ2014 የዓለም ጤና ድርጅት ከ2030 እስከ 2050 ባሉት ጊዜያት ውስጥ በጭንቀት፣ በምግብ እጥረትና በወባ በየዓመቱ ሩብ ሚሊየን ሕዝብ እንደሚሞት ከተተነበየው ጋር የሚተካከል ነው፡፡ በአዲሱ ጥናት መሠረት እ..ኤ.አ 2030 ድረስ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ከ100 ሚሊየን ሕዝብ በላይ ከድህነት ወለል በታች ይወድቃል፡፡

| ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድኅን/1928-1998/ | | |
|---|---|---|
| ክራር ሲከር | ተውኔት | 1952 ዓ.ም |
| የእሾህ አክሊል | ተውኔት | 1952 ዓ.ም |
| በልግ | ተውኔት | 1954 ዓ.ም |
| አስቀያሚዋ ልጃገረድ | ተውኔት | 1955 ዓ.ም |
| እኔ ብዬ መጣሁ | ተውኔት | 1955 ዓ.ም |
| የከርሞ ሰው | ተውኔት | 1957 ዓ.ም |
| ጴጥሮስ ያቺን ሰዓት | ተውኔት | 1957 ዓ.ም |
| ሊስትሮው | ተውኔት | 1957 ዓ.ም |
| ሀሁ በስድስት ወር | ተውኔት | 1966 ዓ.ም |
| እናት ዓለም ጠኑ | ተውኔት | 1967 ዓ.ም |
| አቦጊዳ ቀይሶ | ተውኔት | 1968 ዓ.ም |
| ቴዎድሮስ | ተውኔት | 1970 ዓ.ም |
| መልዕክተ ወዛደር | ተውኔት | 1971 ዓ.ም |
| መቅድም | ተውኔት | 1972 ዓ.ም |
| ጋሞ ቴአትር | ተውኔት | 1973 ዓ.ም |
| ሀሁ ወይም ፐፑ | ተውኔት | 1985 ዓ.ም |
| እሳት ወይ አበባ | ሥነ ግጥም | 1966 ዓ.ም |
| ሐምሌት /ትርጉም/ | ተውኔት | 1953 ዓ.ም |
| ኦቴሎ /ትርጉም/ | ተውኔት | 1959 ዓ.ም |
| ማክቤዝ /ትርጉም/ | ተውኔት | 1960 ዓ.ም |
| ንጉሥ ሊር /ትርጉም/ | ተውኔት | 1972 ዓ.ም |

## አባባል

- ሳውዲ አረቢያ ግመልን ከአውስትራሊያ፣ አሸዋን ደግሞ ከቱኒዚያ በመግዛት ወደ አገርዋ ታስገባለች::
- የሌሊት ወፍ ጆሮዋ ከተደፈነ መብረር አትችልም::
- ፊታቸውን ወደ ኋላ ሳያዞሩ ከበስተጀርባቸው ያለውን ነገር ማየት የሚችሉት ጥንቸል እና በቀቀን ወፍ ናቸው::
- የዋልታ ድብ ለምሳው ወይም ለቁርሱ ብቻ 86 ፔንጉዊንስ ይመገባል::
- በጣም ትንሿ የወፍ ዝርያ ሃሚንግ በርድ ስትሆን ክብደቷ ከ "10 ሳንቲም" ክብደት ያንሳል::
- ዝሆን ከሞተም በኋላም እንደቆመ ይቀራል እንጂ ካልተገፋ በቀር አይወድቅም::

## ሸኙልን

እስኪ ወንበር ስጡኝ፣ የምቀመጥበት
መቆም ይሰለቻል፣ ብዙ ሰው ባለበት::
የተቀመጡትም...
ለባለተራዎች፣ መልቀቅ እንዳይረሱ
አውቆ አላዋቂውን፣ እንዲነሳ አስታውሱ
የተኛን ቀስቅሱ::
ምፅዓት እስኪመጣ፣ ጌታ እስኪፈርድልን
ቆመን የምንጠብቅ፣ እኛ ፃድቅ አይደለን::
እኝህን ፈራጅ ዳኛ፣
አርቁልን ከኛ፣
ከእውነት ዓለም ሸሽተው፣ ብዙ ሰው ሳይጎዱ
ከነወንበራቸው፣ ሸኟቸው ይሂዱ::
በዳኝነት ሰበብ፣ ፍርድ የሚያጎሉበት
ወንበሩን ሻሽጠው፣ አንድ ሀገር ይግዙበት::

*የወፍ ጎጆ ምህላ በኤፍሬም መኮንን 2011 ዓ.ም*

# የወያኔ ትልቁ ክህደት . . .

ከገጽ 16 የዞረ

ተዳከመ:: ጀነራሉንም ለማስፈታት ብዙ ትግል አደረግን፣ አንዳንድ ድርጅቶች እነ ኢህአፓም ተባብረውን ከእስር ከወጡ በኋላ ወደ ኒውዝላንድ እንዲሄዱ አደረግን:: ሰባት ዓመት የዘለቀው የፖለቲካ እንቅስቃሴያችን በዛ መልክ አለቀ ማለት ነው::

**ግዮን፡- በቀጣይስ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ገባህ?**

**ነአምን፡-** ከፖለቲካው አልወጣሁም:: በሲቪክ ድርጅቶች ተግባር ከእነ አምባሳደር እምሩ፣ ነፍሳቸውን ይማርና ጀነራል ቁምላቸው ደጀኔ፣ ኤልያስ ክፍሌና ሌሎች ወጣት አክቲቪስቶች አንድ ላይ በመሆን በጦርነቱ ጊዜ የፖለቲካ እስረኞች የነበሩት "እነ ፕ/ር አስራት ወ/ልደየስ፣ ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት፣ አበራ የማነአብ ካልተፈቱ በስተቀር ከወያኔ ጋር በፍፁም አንተባበርም" የሚል አቋም ይዘን፤ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ስናካሂድ ነበር:: ያኔ ነው እነ ገነነው አሰፋ እዚህ መጥተው እኛን "የሻዕቢያ ተላላኪዎች" ማለት የጀመሩት::

የኢሕአፓ አመራር ከነበሩት የፖለቲካ ሰዎች ጋር በጣም በቅርበት እሰራ ነበር፤ በነበራቸው አቋም የተነሳ አስራ አምስት አጠቃላይ ድርጅቶች ያካተተ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲዊ ኃይሎች ህብረትን ለማቋቋም እንቅስቃሴ ሲጀመር እኔም አንዱ አስተባባሪ በመሆን የቴክኒካል ኮሚቴው አባል ሆኜ ሥራዬን ጀመርኩ:: ከአንድ ዓመት በኋላ በ2003 (እ.ኤ.አ) በተካሄደው የ15 ድርጅቶች ጉባኤ ተደረገ:: ያ እንዲሆን ብዙ ሰሜን አሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያኖችን፣ የፖለቲካ ድርጅቶችንና ሲቪክ ድርጅቶችን የማስተባበር ሥራ ሰርቻለሁ:: የቴክኒካል ኮሚቴው ኃላፊ ሆኜ ጉባኤው ላይ ስገኝ ነው እነ ልደቱ አያሌውን ያየሁት፤ በጊዜው አቶ ኃይሉ ሻውል አልመጡም ነበር:: ግን ባለመምጣታቸውና በሌሉበት ሊ/መንበር ተደርገው ባለመመረጣቸው ቅሬታ ገባቸው:: ያ የህብረት ድርጅት ይፋ ሆኖ ሲመሰረት በዚህ የተነሳ ኃይሉ ሻውል፣ ልደቱ አያሌውና መኢአድ የማፈንገጥ ነገር ያሳዩት በዚህ ምክንያት ነው::

**ግዮን፡- በምርጫ 97 ወቅት ኢህአዴግ ከቅንጅትም በላይ ዶ/ር ነገደ ጎበዜን ነበር በጣም የሚፈራው፤ ያኔ እንደውም እርሳቸውም አንድ መጽሐፍ አውጥተው በረከት ስምኦን አስተያየት ሰጥቶበት ነበር:: ለምን ይመስልሃል?**

**ነአምን፡-**"ህገ መንግስትና ዴሞክራሲ" የሚል ነበር የዶ/ር ነገደ መጽሐፍ:: የህትመት ስራዎችን ስለምሰራና ድርጅትም ስለነበረኝ ይሄንን መጽሐፍ ያሳተምኩት እኔ ነኝ:: ወያኔ ነገደን የሚፈራው የሚያነሳው ሀሳብ በወቅቱ ገዢ ስለነበር ነው:: የተለያዩ የቀለም አብዮቶችን ተሞክሮ ባገናዘበ መልኩ እንዴት መደራጀት እንዳለበት፣ ህዝቡ ምን ዓይነት የመታገያ ዘዴዎችን መከተል እንዳለበት፣ ድርጅቶችም ሥርዓቱን ፕሮግራም ቀርፀው በምን ዓይነት መንገድ መታገል እንዳለባቸው፣ ስትራቴጂክ ምክሮችና አማራጮች የነበሩት ዶ/ር ነገደ ነው::

በኋላ ላይ የተደረጉትን የቅንጅቱንና የህብረቱን እንቅስቃሴዎች ካየህ ከእሱ ሀሳብ ጋር ይዛመዳሉ፣ ወያኔ ደግሞ ትንሽ ነገር ነው የሚያስበረግገው:: እነ በረከትም በሱ ሃሳብ በረገጉና የዚህ ሁሉ ትግል ስትራቴጂስት ነገደ ነው ብለው ደመደሙ:: ያቺ መጽሐፍ ደግሞ በጣም ታዋቂ ሆነች:: ከዛ አኳያ ነው በሁሉም ነገር ላይ "ነገደ ነገደ" ይሉ የነበረው::

ወያኔ ሁሌ ጭንቅ ሲገጥመው የተለያዩ ስሞችን ይጠቅሳል:: የዛሬ ሀያ ስድስት ዓመት ገደማ፣ እኔ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ስጀምር ሁለት ስሞች ወያኔን ያስበረግጉት ነበር:: አንዱ ኢህአፓ ነው፤ ሁለተኛው ካሳ ከበደ (አምባሳደር) ነው:: በረከት ስምኦንና በኋላ የተገፋው የወያኔ ባለስልጣን አለምሰገድ የሚባለው ሰው አሜሪካ መጥተው ኢንተርቪ ሲሰጡ "ካሳ ከበደና ኢህአፓ ነው ይሄን የሚያደርገው" ይሉ ነበር:: በየጊዜው የሚወቅሱትና የሚያብጠለጥሉት፣ የራሳቸውን ፍራቻና ችግር የሚያላክኩበት፣ የሚያደናግሩበት ሰው ይፈልጋሉ:: በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅትም ዶ/ር ነገደ ጎበዜን በዋነኝነት ይወነጅሉም ይፈሩም የነበረው ለእዛ ነው::

**ግዮን፡- በአሜሪካን ሀገር የነበረህ ድርጅት ምን ያህል ጊዜ ሰራ? የቆመበትስ ምክንያት ምንድን ነው?**

**ነአምን፡-** "ኤዞፕ ፐብሊሸርስ" ይባላል:: ስምንት መጽሐፎችን አሳትሜያለሁ:: የመጀመሪያው የዶ/ር ነገደ ጎበዜ ነው፤ በመቀጠል የሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስን ፣ ሰለሞን ገ/ስላሴ የሚባል የኢህአፓ አመራር፣ የዶ/ር ነገደን ሁለተኛ መጽሐፍ፣ የአቶ የሱፍ ያሲንን በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ የሚያተኩር መጽሐፍ ለህትመት አብቅቻለሁ:: ከነዚህ መጽሐፍት መሀል አንዳንዱን በራሴ ኢንቨስትመንት ነው ያሳተምኩት፤ አንዳንዱን ደግሞ እኔ ፕሮጀክት ማናጀር ሆኜ አሰራና እነሱ ለህትመቱ ይከፍላሉ፣ ሼር አድርገን ነበር ለገበያ የምናቀርበው::

የመጽሐፍና የመጽሔት ሕትመት ትልቁ ችግር ሥርጭት ነው:: ሲስተሙ በጣም የተደራጀና የተቀላጠፈ ስላልሆነ የግለሰቦች ጥገኛ ትሆናለህ:: እኔ በአለም ዙሪያ ሰፊ ኮንታክት ስላለኝ ለግለሰቦች ልኬ ፣እነሱ ሄደው በየሱቁ አከፋፍለው፣ እነዛ ሱቆች ደግሞ ኮሚሽናቸውን ወስደው ነው ገንዘቡ የሚደርስህ፤ በዛ መሀል ብዙ ሊኬጅ አለ:: ችግሩ ሰፊ ነው:: እ.ኤ.አ ከ2008 ጀምሮ እስከ 2014 ድረስ አሳታሚ ድርጅቱን ሰርቼበታለሁ:: የደረጀ ደምሴ "አባቴ ያቺን ሰዓት" እርሱ በጣም ተሸጧል:: የሻለቃ ዳዊትም መጽሐፍ ተሸጧል፣ የዶ/ር ነገደ የመጀመሪያው በደንብ ተሸጦ ነበር፣ ሁለተኛው ግን ጥሩ አልነበረም:: የህትመት ስራ ድካሙ፣ ወጪውና መጨረሻ ላይ የምታገኘው ነገር አይመጣጠንም::

**ግዮን፡- ወደ ፖለቲካ ትግል እንዴት ተመለስክ?**

**ነአምን፡-** ከህብረት ከወጣሁ በኋላ እቤት ቁጭ ብዬ መንጨርጨር ሆነ ስራዬ:: እንዴት የኢትዮጵያ ህዝብ ያለ ነፃነት፣ ያለ ፍትህ፣ ወያኔ እነዚህን ሁሉ በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች አስሮ፣ በአየደባባዩ ያን ሁሉ ሰው በጥይት ገድሎ፣ እንዴት አሁንም ስልጣን ላይ ይቀመጣል? በሚል ለአንድ ሰባት ወር ስብሰለስል ከቆየሁ በኋላ በአጋጣሚ ከሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ ጋር ተዋወቅን::


ከኢትዮጵያ የወጡ፣ የኢህአዴግ ሲነየር ኦፊሰሮችና የቀድሞ የኢሰፓ ውስጥ የነበሩ፣ የቀድሞ ጦር ውስጥ የነበሩ ኦፊሰሮች ኬንያ ናይሮቢ መጡ፤ ወደ እዛ ሄደን ካነጋገርናቸው በኋላ ወያኔን የሚቃወም፣ አስፈላጊውን የትጥቅ እንቅስቃሴ እናደርጋለን አሉ:: ያኔ በጣም ደስተኛ ሆኑኩኝ :: ምክንያቱን ከበፊትም ጀምሮ ወያኔ በሰላማዊ ትግል ብቻ አይወድቅም የሚል ዕምነት ስለነበረኝ::

በሻለቃ ዳዊት በኩል ሰዎች መጡ፣ እኔም አመጣሁ:: አቅም ያላቸው፣ ትግል ውስጥ የነበሩ ምሁሮች ወይም ፕሮፌሰሮችን ያካተተ አንድ ሀያ ሰዎች ያሉበት የህቡዕ ድርጅት አቋቋምን:: የእዛን ጊዜ ገንዘብ አሰባስበን እነዚህን ሰዎች ፈንድ እያደረግን፤ በአንድ በኩል የቀድሞ ሰራዊት ኦፊሰሮች በየቦታው፣ በየክ/ሀገሩ ኔትወርክ አለን ስላሉ እነሱን መርዳት እና ማጠናከር፣ የትጥቅ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ:: ሁለተኛው በወያኔ ውስጥ በሻምበል በምን ደረጃ ያሉ ሰዎች ስለሆኑ፣ እነሱ ደግሞ "የአድዋ ተወላጆቹ ከፍ እያሉ ነው፣ እኛ የሽሬና የሌሎች አከባቢ ተወላጆች ግን እየተገፋን ስለሆነ አንድ ነገር ማድረግ እንፈልጋለን" ስላሉ፤ እነሱን አንድ ዓመትና ሁለት ዓመት ያህል መሀል ሆነው እንዲረዱን ሞከርን፤ አንዳንድ ትናንሽ ነገር አደረጉ፣ ግን በምንፈልገው ደረጃ አልነበረም::

እንደውም በተወሰነ ደረጃ አጭበርባሪዎች ይመስሉኛል ወያኔዎቹ:: የደህንነት ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ነው በኋላ ላይ የገመትነው:: ያንን የህዕቡ ድርጅት ይዘን እየሞከርን ባለንበት ወቅት የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ግንቦት ሰባት ተመሰረተ:: ሰዎች ለብርሃኑ ስለእኔ ነገሩት፤ እኔም "አሁን ብርሃኑ በትክክል ከሰላማዊ ትግል ባሻገር ሌላም ትግል ለማድረግ ቆርጧል" ከሚል ውሳኔ ላይ ደረስኩ:: አስቀድሜ እሱን እከታተለው ስለ ነበር ተገናኘንና ተነጋገርን:: ከኤርትራውያቹ ጋር ያኔ እኛ በሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ አማካይነት ግንኙነት ፈጥረን ስለነበር ልንሰራ አስበን የነበረውንና አሁን ለእናንተ መግለፅ የማይገባኝን ነገር በሙሉ በዝርዝር ነገርኩት:: ዶ/ር ብርሃኑም "በጣም ጥሩ ነው፣ አብረን እንስራ " አለ፤ የህቡዕ ድርጅቱን ይዤ ተቀላቀልኩ፤ወደ ስራ ከገባን በኋላ ደግሞ በጣም መቀራረብ ጀመርን::

ከትግሉ ጋር በተያያዘ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች አሜሪካ ውስጥ ሰፊ ኔትወርክ ስላለኝ፣ ከብዙ ሰው ጋር እሱንም ሆነ ሌሎችን አመራሮች የማገናኘት ስራ ነበር የምሰራው:: የሰጠኝ ኃላፊነት በጣም ሰፊ ነው:: በኋላ ላይ እኔ ይዤው የቀረብኩት የህቡዕ ድርጅት፣ ግንቦት ሰባትና የአፋሮች ድርጅት "ጥምረት ለነፃነትና ለፍትህ" የሚል ግንባር ፈጠርን:: ያኔ ብርሃኑ ሊ/መንበር ነው፣ እኔ ዋና ፀሐፊ ነበርኩ፣ የአፋሩ ኦሎ የሚባል ሰው ደግሞ ም/ሊቀ መንበር ነበር:: በኋላ አንዳንዶቹን አፋሮች ወያኔ አስኮብልሎ በመውሰድ ገንዘብና ስልጣን ሲሰጣቸው፣ አፈነገጡና ዶ/ር ኮንቴ ብቻ ከእኛ ጋር ቀረ::

በአርበኞች ግንቦት ሰባት የበረሃ የትጥቅ ሕይወቱ፣ ስለ አንዳርጋቸው ጽጌ እስርና ስለነበራቸው ቅርበት፣ የትጥቅ ቡድኑን አስቀድሞ ኤርትራ በመግባት ስለመሰረተበት ጉዳዮችና አስገራሚ ስለሆነው የግል ሕይወቱ ያደረግነውን ሰፊ ቃለምልልስ በሚቀጥለው ይዘን እንቀርባለን::


ረ/ፕ ወንድማገኝ ታደሰ


ፕ/ር ፍሎሪያን ቢበር

# ኢትዮጵያ

## የዮጎዝላቪያን ውድቀት መድገም የለባትም

*ታዋቂው ፎረን ፓሊስ ድረገጽ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ጥናታዊ ጽሑፎችን፣መጣጥፎችን እና ዘገባዎችን በማቅረብ ይታወቃል፡፡ከሰሞኑ በዚሁ ድረገጽ ላይ የታሪክ ፕሮፌሰሩ ፍሎሪያን ቢበር እና ረዳት ፕሮፌሰር ወንድማገኝ ታደሰ የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፓለቲካ ትኩሳትን አስመልክተው የለቀቁትን ዘለግ ያለ ጽሑፍ የግዮን ጋዜጠኛው ደረጀ ይመር ለአንባቢ በሚመች መልኩ ወደ አማርኛ መልሶታል፡፡*

### መንደርደሪያ

በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሚመራው አስተዳደር የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብን ትኩረት የሚስቡ ፓለቲካዊ እርምጃዎችን መውሰዱ የሚታወስ ነው:: ለዘመናት ያጠላውን የሥጋት ደመና የሚገፍ የሰላም ሥምምነት ከኤርትራ ጋር መፈፀም ችሏል፤የአሸባሪነት ታፔላ የተለጠፈባቸው ግለሰቦች እና ተቋማት ነጻ መሆናቸው ተበስሮላቸዋል፤በሀገር ውስጥ እና በውጭ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎች ወደ ሰላም ማዕቀፍ ውስጥ መግባት እንዲችሉ ምህዳሩ ሰፍቶላቸዋል፤ ሚዲያዎች ያሻቸውን በነጻነት የሚዘግቡበት እድል ተመቻችቶላቸዋል፤ ገለልተኛነቱ ጥያቄ ውስጥ ይገባ የነበረው የሕግ ተርጓሚው ክፍል ተቋሚዊ ሪፎርም ማድረግ ጀምሯል፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ግማሽ ካቢኔ በአፍሪቃ ብዙም ባልተለመደ ሁኔታ በሴቶች ለመዋቀር በቅቷል::

ይህ ፈጣን የፖለቲካ ለውጥ ያላንዳች እንከን አልተከናወነም:: አገሪቱ አሁንም በአራቱም ማዕዘናት ሰላም እንደራቃት ነው:: ኢትዮጵያ 100 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ትልቅ ሀገር እንደሆነች ይታወቃል:: በዚች ከ80 በላይ የዘውግ ማኅበረሰብን ባቀፈች ባለብዝኃ ባህል እና ቋንቋ ሀገር ውስጥ የሚፈጠረው አዎንታዊ ለውጥ ለቀጠናው የሚያበረክተው ፋይዳ የላቀ እንደሚሆን እሙን ነው::

ነገር ግን ከለውጡ ጋር ተያይዞ የሚመጣ አደጋ ከወዲሁ ሊጤን ይገባል:: ለውጡን አጥብቀው የሚቃወሙት ኃይሎች በጎሳቸው መሀል መሽገው ማንነት ላይ ያነጣጠረ ግጭት ለመፍጠር ቀን ሌት መባተታቸው የማይቀር ነው::ይህ ግጭት እየተካረረ ከሄደ ደግሞ ሀገሪቱን ከለየለት ነውጥ ውስጥ ሊጨምራት እንደሚችል መገመት አያዳግትም::

የአሁኑ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ከ1982 ዓ.ም የዮጎዝላቪያ ፖለቲካ ትኩሳት ጋር ኩታገጠም ነው:: ልክ እንደቀድሞዋ ዮጎዝላቪያ ኢትዮጵያ በዘር ማንነት የተሸነሸኑ ዘጠኝ ክልሎችን ያቀፈች ፌዴራላዊ ሀገር ነች:: ትግራይ፣ አማራ እና ኦሮሚያ የሀገሪቱ 80 በመቶ የሚሆን ሕዝብ ይኖርባቸዋል:: ሁሉም የፌዴሬሽኑ አባላት መጠሪያ ስያሜያቸውን ያገኙት ክልሎቹ በርስትነት በተሰጠው የዘውግ ማኅበረሰብ ስም ነው::

ለዘውግ ማኅበረሰቦች አንድን ግዛት በርስትነት መስጠት በሁለት በኩል እንደተሳለ ቢለዋ ይቆጠራል:: በአንድ በኩል የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ዕድልን ሲያጎናፅፍ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ነባራዊ ሁኔታዎች ወደ ጎን ተገፍተው፣ የዘር ማንነት ብቻ እንዲጎላ እና ሁሉንም ወሳኝ ሚና እንዲጫወት ዕድል ከፍቶለታል:: በዚህም የተነሳ በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች ውስጥ በዘር ማንነት ላይ የተነጣጠረ ጥቃት በየጊዜው እንዲሰነዘር ምክንያት ሆኗል::

### የኢትዮጵያና የዮጎዝላቪያ ዝምድና

ዮጎዝላቪያን በ1980ዎቹ በአውራነት ሲመራት የነበረው የኮሚኒስት ፓርቲ ነበር:: በተመሳሳይም ኢትዮጵያን ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ ሌጣውን እያስተዳደራት ያለው ገዢ ፓርቲ ኢሕአዴግ እንደሆነ ይታወቃል:: ከወራቶች በፊት ኤሕአዴግን በመሠረቱት በዘውግ ፓርቲዎች መካከል ያለው ግንኙነት የአውራ እና የጭፍራ ነበር:: የለውጡ ሒደት ግን ይህንን የተዛባ ግንኙነት ገለባብጦታል::

> **የኢትዮጵያ ወቅታዊ የፓለቲካ ትኩሳት ታሪክን የኋሊት ተጉዘን የ1970ዎቹ መባቻ ላይ የነበረውን የቀድሞዋን ዮጎዝላቪያ ምስቅልቅል የፓለቲካ ገጽታን እንድናስታውስ ያስገድደናል፡፡ የአሁኗ ኢትዮጵያ እንደ ቀድሞዋ ዮጎዝላቪያ በዘውግ ፖለቲካ ወጀብ እየተመታች ነው**

የኢትዮጵያ ወቅታዊ የፓለቲካ ትኩሳት ታሪክን የኋሊት ተጉዘን የ1970ዎቹ መባቻ ላይ የነበረውን የቀድሞዋን ዮጎዝላቪያ ምስቅልቅል የፓለቲካ ገጽታን እንድናስታውስ ያስገድደናል:: የአሁኗ ኢትዮጵያ እንደ ቀድሞዋ ዮጎዝላቪያ በዘውግ ፖለቲካ ወጀብ እየተመታች ነው::በዮጎዝላቪያ ሰርቦች የነበራቸው የወታደራዊ እና የደህንነት ልዕልና አደጋ ውስጥ እንደወደቀው ሁሉ ሕወሓትም በለውጡ ሂደት ለሃያ ሰባት ዓመታት በፊታውራሪነት ሲዘውረው ከነበረው የወታደራዊ እና የደህንነት ተቋማት ሚናው ተነጥቆ ወደ ዳር ለመገፋት ተገዷል::

ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዐት መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆማለች:: ሀገር ለመበተን ላይ ታች በሚሉ እና የሀገር አንድነትን ለማጽናት በሚተጉ ኃይሎች መካከል ያለው መካረር ገና መልስ አላገኘም ::በርግጥ ከሶማሌ ክልል የሚነሳው የመገንጠል እንቅስቃሴ አሁን የረገበ ይመስላል:: ትግራይ ግን ለማእከላዊው መንግሥት ያልተጠበቀ ረስምታት ሆና ብቅ ብላለች:: በማንኛውም ሰዐት ሀገሪቱን የሚያናውጥ ቀውስ ከዚሁ ክልል ሊፈነዳ ይችላል:: ይህንን አደጋ አንዳንድ ታዛቢዎች ግን እንደ ቅዠት ነው የሚቆጥሩት:: ነገር ግን አሁን ሕወሓት ያለተቀናቃኝ ሌጣውን የሚያስተዳድረው የትግራይ ክልል ለማዕከላዊ መንግሥት ሳንካ እየሆነ እንደመጣ ማሳያ የሚሆኑን ገሀድ እውነታዎችን እያስተዋልን ነው:: ክልሉ በሽብርና በወንጀል ለተጠረጠሩ ግለሰቦች ጥሩ መሸሸጊያ (safe heaven) ሆኗል::

የቀድሞዋ ዮጎዝላቪያ ፈላጭ ቆራጭ መሪ ፊልድ ማርሻል ቲት ሕለፈተ ሞታቸውን ተከትሎ የፖለቲካ ምስቅልቅሉ ተባብሶ ነበር:: የኮሚኒስት ሊግ የሚባለው ገዢው ፓርቲም በቲቶ ዘመነ መንግሥት የነበረውን ሽምቀቆ በማላላት የፖለቲካ ምህዳሩን በእጅጉ ማስፋት ጀመረ:: የሚዲያ ነጻነት፣ የመሰብሰብ እና የመደራጀት መብትን የፈቀደ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የብሔርተኝነቱ እንቅስቃሴ እየጎመራ ሊሄድ ችሏል::

ገዢ ፓርቲው ከዚህ ቀደም የነበረውን የኃይል አማራጭ በመቀየሩ የተነሳ ብሔርተኞች እንደልባቸው የሚፈነጩበት አጋጣሚ አገኙ:: በሰሜኖቹ ባለጠጎች እና በደሀዎች ደቡቦች ፖለቲከኞች መካከል የነበረው መካረር ቀስ በቀስ እየተባባሰ ሄደ:: ►

በቲቶ የአገዛዝ ዘመን ደርሶ የነበረው የሰብኣዊ መብት ጥሰት የብሔርተኝነቱን እንቅስቃሴ የበለጠ ለማፋፋም እንደ ነዳጅ ሆኖ አገልግሏል:: የተለያዩ የብሔር ድርጅቶች ጭቆናን ከፍ አድርገው በማዜም፣ ደጋፊዎቻቸውን ለማበራከት ላይ ታች ማለታቸውን አጠናከሩ:: እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች በሀገሪቱ የተዘረጋውን የብሔር ፌዴራሊዝምን በመመርኮዝ በቀላሉ ኃይላቸውን እያሰባሰቡ ለመሄድ አልተቸገሩም ነበር:: የዮጎዝላቪያ ፌዴሬሽን በራሳቸው የቆሙ ሪፐብሊኮች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮችን ያቀፈ ሲሆን ፌዴሬሽኑን የመሠረቱት ክልሎች ግን ዋንኛ መለኪያ ብሔር ነበር::

በዚህ መሠረት በሪፐብሊኮቹ ውስጥ ብቅ ብቅ ያሉት ብሔርተኞች የመገንጠል አጀንዳቸውን እውን ለማድረግ የሚያስችል አቅምን እያጎለበቱ ለመሄድ አልተቸገሩም:: የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ የሚለግሰውን ድጋፍ ለዮጎዝላቪያ ፌዴራል መንግሥት መንፈጉ ደግሞ የዳር ኃይሎችን በማጠናከር በምትኩ ማእከላዊውን መንግሥት በእጅጉ ሊያዳክመው ችሏል:: በተለይ ግዙፎቹ የገንዘብ ተቋማት አይኤም ኤፍ እና ወርልድ ባንክ በሀገሪቱ ውስጥ የተከሰተውን ቀውስ የሚያባብስ እርምጃን ወሰዱ:: በዚህም ምክንያት ሥራዓጥነት ተበራከተ፣ ዮጎዝላቪያ እንደ ሀገር መቀጠሏ የማይዋጥላቸው ኃይሎች ተጨማሪ ማሳመኛ ምክንያት አገኙ:: የአንድነት ምልክት የሆኑ ሐሳቦች እና ተቋማት ከል ለበሱ:: የዘውግ አቀንቃኝ ፖለቲከኞችም ይህንን ቀውስ ለሚፈልጉት ዓላማ በመጠቀም የዮጎዝላቪያን ውድቀት ሊያፋጥኑት ችለዋል::

## ኢትዮጵያን ከዮጎዝላቪያ ምን ይለያታል?

የዮጎዝላቪያ ውድቀት በኢትዮጵያ እንደማይደገም ምንም መተማመኛ የለም:: የፖለቲካ ምህዳሩ በሚሰፋበት ጊዜ በዘውግ ማንነት ላይ የተቀለሰው ፌዴራል ሥርዓት በቀላሉ ሊፈነዳ የሚችል ቦንብን መፍጠሩ የማይቀር ነው::በለውጡ ሂደት ሀገሪቱን በአራቱም ማዕዘናት የሚለበልብ እሳት ሊከሰት ይቻላል:: ምንአልባትም ከዮጎዝላቪያ ጋር ሲነፃፀር ኢትዮጵያን በተሻለ ደረጃ ሊያስቀምጧት የሚችሉ ነባራዊ እውነታዎች አሉ::

በቅድሚያ በኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት ውስጥ በአባልነት የተቃፉት ክልሎች ከዚህ ቀደም ልክ እንደ የጎዝላቪያ የፌዴሬሽን አባላት በታሪክ ሂደት ውስጥ በራሳቸው የቆሙ ሉአላዊ ሀገሮች አልነበሩም::ሁለተኛው አዎንታዊ ገጽታ :አብዛኛው የዘውግ ማኅበረሰቦች ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል ያላቸው እምነት ጽኑ ነው::

ሦስተኛ፡ በዘውግ ማኅበረሰቦች መካከል ያለው ትስስር በጣም ጠንካራ ነው:: ለምሳሌ ሁሉም ብሔሮች ከ80 ዓመት በፊት በነበረው በጣሊያን ወረራ ወቅት የተደረገውን የተጋድሎ ታሪክ በእኩል ደረጃ ይጋሩታል:: በአንጻሩ ዮጎዝላቪዊያን በአንድነት የሚያስተሳስራቸው ምንም ዓይነት የጋራ ታሪክ አልነበራቸውም::

ስለዚህ ከየጎዝላቪያ አንጻር ኢትዮጵያን መበታተን ተምኔታዊ ሊመስል ይችላል:: ለአብነት ያህል ትልቁን የኦሮሞ ዘውግ እንውሰድ፤ ኦሮሚያ በራሱ ሀገር የሚሆንበት መልካምድራዊ አቀማመጥ የለውም:: የዮጎዝላቪያን ተሞክሮ ስንወስድ ግን ሁሉም የፌዴሬሽኑ አካል የነበሩት ክልሎች ከሌላ ሉአላዊ ሀገር ጋር ኩታገጠም ነበሩ::

የዮጎዝላቪያ ገዢ የነበረው የሰርቢያን ሊግ ኮሚኒስት ፓርቲ በ1970ዎቹ እና 80ዎቹ በኃይል ጭምር ማእከላዊነት ለማጠናከር በሚሞክርበት ጊዜ በስሎቬኒያ እና በክሮሺያ የነበሩት ፓርቲዎች መገንጠልን አጥብቀው ያቀነቅኑ ነበር::በኢትዮጵያ ግን የፖለቲካው አቅጣጫ ሶስት መቶ ስልሳ ዲግሪ ተቀይሯል::አንዳንድ ኃይሎች በሕገ መንግሥቱ ላይ የተቀመጠውን የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል አጀንዳን በመተው የአንድነት አቀንቃኝ መሆን ጀመረዋል::

በኢሕአዴግ ውስጥ ያሉት አዴፓ እና ኦዴፓ፣ የሀገሪቱን ከ70% ፐርሰንት በላይ የሚሸፍኑትን የአማራን እና ኦሮሚያ ሕዝቦችን የሚወክሉት ፓርቲዎች በዚህ ማእቀፍ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው:: ከሀገሪቱ የሕዝብ ብዛት 20 እጅ የሚሸፍኑትም የደቡብ ብሔረሰቦች የአንድነት አቀንቃኝ ሆነው ብቅ ብለዋል::

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ እንደ ዮጎዝላቪያ የመበታተኑን ሂደት የሚከላከሉ መጠበቂያ ግንቦች እንዳሉ ቢታወቁም አደጋው የለም ብሎ አፍን ሞልቶ መደምደም ግን አይቻልም:: ልክ በቀድሞዋ ዮጎዝላቪያ እንደነበሩት የክሮዋት እና የስሎቪንስ ገንጣይ ቡድኖች በትግራይ ክልል የተሰባሰቡት ኃይሎች የማእከላዊ መንግሥቱን እየተፈታተኑት ነው:: ላለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ሀገሪቱን በበላይነት ሲዘውራት የነበረው ሕወሓት መልሶ የሚያንሰራራበት፣ ከተቻለም ወደ ቤተመንግሥት የሚመለስበት ድብቅ ሴራ ከመንደፍ ወደኋላ እንዳማይል ይናገራል:: ይህ ሕዳጣን ቡድን የሀገሪቱን 10 በመቶ እንኳን የማይሞላን ሕዝብ ወክሎ ሚዛናዊ ባልሆነ መልክ የሥልጣን መንበሩን ጨብጦ መቆየቱ ለብዙዎች ግራ ነበር ::

የሕወሓት ቅያሜን ያባባሰው በቀድሞ አባላቱ ላይ የተወሰደው እርምጃ ነው:: በዘረፋ እና ሰብኣዊ መብት ጥሰት የተጠረጠሩ የድርጅቱ ቱባ ሹማምንት ላይ የእስር ዋራንት መቆረጡ ከማእከላዊ መንግሥቱ ጋር ቁርሾ ውስጥ አስገብቶታል:: ከዚህም በተጨማሪ የድርጅቱ አባላት ከክልል እና ከፌዴራል አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ ቀስ በቀስ መገለላቸው ድርጅቱ በበጎ አልተቀበለውም::

በዘር ማንነት ላይ ተንጠላጥሎ ማዶ ለማዶ በተከፋፈለ ማኅበረሰብ ውስጥ የፖለቲካውን ምህዳር በድንገት ማስፋት አደጋው የበዛ ነው:: የሸምቀቆውን መላላት ተከትሎ ብሶትን እና ቅያሜን ከፍ አድርገው በማዜም ለፖለቲካ ትርፍ የሚታትሩ የፖለቲካ ነጋዴዎች ከየሰርጡ ብቅ ብቅ ማለታቸው አይቀርም:: በዚህ ውዥንብር ወቅት ላይ ሰፊው ማኅበረሰብ ፍሬውን ከገለባው የሚለይበት ምንም ዓይነት አጋጣሚ አይኖረውም::

የእነዚህን ግለሰቦች እኩይ ተግባር እርቃን የሚያስቀር መዋቅር ወይም ተቋም እንዳይገነባ ያለፈው የ27 ዓመታት አምባገነናዊ አገዛዝ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የዘር ፌዴራሊዝም ሥርዓት በተዘረጋባቸው ሀገሮች ፓርቲዎች በአብዛኛው የሚመሠረቱት በዘውግ ማንነት መሰመር እንደሆነ የአደባባይ እውነታ ነው:: እነዚህ የዘውግ ፓርቲዎች ደግሞ ጠንካራ ድጋፍ ለማሰባሰብ ከአማካኝ የፓለቲካ አቋም ይልቅ ከሌሎች የዘውግ ማኅበረሰቦች ጋር የሚያቃቅርን ልዩነት ማራገብ መለያ ባሕሪያቸው ነው::ከአምክንዮ ይልቅ ለስሜት ነው የሚባትቱት::ተቀባይነትን ለማግኘት ሕዝባቸውን ከበባ ሥነልቦና(Siege Mentality) ቅርቃር ውስጥ ይጨምሩታል::ከሚወክሉት ዘውግ ባሻገር ሌላ የዘውግ ማኅበረሰብን የዓላማቸው ተከታይ ለማድረግ የተብራራ ፐሮግራም ስለሚያስፈልግ ቀላሉን ፍርሃት እና ሥጋትን በመስበክ ድጋፍን ማሰባሰብ ይመርጣሉ::

## መደምደሚያ

ከዮጎዝላቪያ በተለየ በኢትዮጵያ የተካሄደው ለውጥ የአብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል በአውንታዊ ነው የተቀበለው:: ሁሉም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀገራት በኢትዮጵያ በተከሰተው አዲስ የለውጥ ሥርዓት ድጋፋቸውን ከመለገስ ወደ ኂላ አላሉም:: አሜሪካ፣ የአውሮጳ ኅብረትም ሆነ ቻይና ለአዲሱ የለውጥ አስተዳደር ያሳዩት ድጋፍ ከፍተኛ ነው::

ዐቢይ አሕመድ በኢትዮጵያ የቅርብ ታሪክ ውስጥ ለንጽጽር እንኳን የማያበቃ ከፍተኛ ድጋፍ ከዳር እስከ ዳር ማግኘት ችለዋል:: ምንም እንኳን ከብሔር ድርጅት ተወክለው ሥልጣን ላይ ቢወጡም፣ ሀገራዊ አርበኝነትን በብርቱ በማቀንቀን፣ ኢትዮጵያ የሁሉም ብሔሮች ሀገር መሆኗን በመሳጭ ንግግሮቻቸው አጽኖት በመስጠት የአብዛኛውን ሕዝብ ልብ መግዛት ችለዋል::

ነገር ግን የዐቢይ አሕመድ የቤት ሥራ ገና አልተገባደደም:: ኢትዮጵያ ውስጣዊ ሰላም ከራቃት ሰንብቷል:: ግድያው፣ ዘረፋው እና መፈናቀሉ ከግዜ ወደ ግዜ እየተበራከተ ነው:: ከቤተ መንግሥት የተባረረው ሕወሓት እና ግብረአበሮቹ በለኮሱት እሳት ምክንያት ከሁለት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ሊፈናቀሉ ችለዋል:: በተጨማሪም በጋብቻ፣ በንግድ እና በሥራ ከቀዬአቸው ርቀው ኑሯቸውን በሌላ ክልል ባደረጉ የዘውጌ ማኅበረሰቦች ላይ የሚደርሰው አድሎ ሌላው የአዲሱ መንግሥት ራስ ምታት ነው:: ይህንን አድሎ የሚያስቀሩበት ተቋማዊ አሰራር አዲሱ አስተዳደር እንደሌለው ይታወቃል::

በዮጎዝላቪያ ላይ የደረሰውን ውድቀት ላለመድገም የኢትዮጵያ መሪዎች በዘውግ ማኅበረሰቦች መካከል የሚፈጠረውን መካረር ማለዘብ አለባቸው:: ልክ እንደ ቀድሞው ዮጎዝላቪያ፣ እንደ አዲስ በተፈጠረው በለውጥ አስተዳደር ላይ የተከፉት ቡድኖች ብሔራቸውን እንደ ምሽግ በመጠቀም ፍርሃትን እና ሽብርን በመንዛት ማንገራገራቸው የማይቀር ነው:: ይህን መሰሉ ግጭት በሚፈጠር ጊዜ ማእከላዊ መንግሥት ከማንም ሳይወግን ፍትሐዊ አሸማጋይ ሚናን መያዝ ይኖርበታል:: በተጨማሪም የሽግግሩን ፕሮጀክት ሰፊው ሕዝብ በባለቤትነት እንዲይዘው ማድረግ በዘውግ ማኅበረሰብ መካከል የሚፈጠረውን ግጭት ሊያለዝብ ይችላል::

በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ፍትሐዊ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ሥርዓትን ማስፈን ከማእከሉ የመነጠል አዝማሚያ የሚያሳይቱን ኃይሎች አጀንዳ የሚያሳጣ እና የሀገሪቱን አንድነት የሚያጠናክር ነው::

በቀድሞዋ ዮጎዝላቪያ የተከሰተው ዘርን መሠረት ያደረገ እልቂት ለኢትዮጵያ የማስጠንቀቂያ ደውል ሊሆን ይችላል:: በርግጥ የኢትዮጵያ የለውጥ ሽግግር ከዮጎዝላቪያ ጋር ሲነጻጸር ብዙ ጠንካራ ጎኖች አሉት:: ነገር ግን ይህንን ጠንካራ ጎን ለማጎልበት በዮጎዝላቪያ የሽግግር ወቅት የተከሰተውን ውጣ ውረድ መለስ ብሎ በማጤን የለውጡን ሂደት ማፋጠን ለነገ የሚባል ሥራ አይደለም::



ኃይሉ አሰለፍ ገብሬ

# የአልጋ ቁራኛ የሆነው ኢኮኖሚያችን

በዚህ ጽሑፍ የምንዳስሰው አጠቃላይ የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ዕጣ ፈንታ (ትሩፋቱንም ችጋሩንም) እንዴት ወደ ዜጎች የዕለት ከዕለት ኑሮ እንደሚመነዘር ነው:: "የምስኪኗን አንድ ሃገር ወስን ሃብቶችም ሆነ በመጠናቸው እጅግ አነስተኛ የሆኑ ምርቶች (Products, goods and services) ዜጎች ባለቤት የሚሆኑት እንዴት ነው ? ዜጎችን በጥረታቸውና በድካማቸው ልክ በሚሸልም፣ ሁሉንም አሳታፊ፣ ፍትሐዊ፣ ወቅታዊ በሆነ ለአንድ ሃገር ኢኮኖሚ ዘለቄታዊ ፋይዳ ያለው ኢኮኖሚያዊ አመንክዮን (Economic Logic and Reasoning ) ባገናዘበ ሥርዓት ዜጎችን የሃብቶቻችንንና ምርቶቻችንን ባለቤት ማድረግ ጀምረናል ?" ወይስ "የዜጎች ተጨባጭ ኑሮ በሀገራችን እንደሚነፍሰው የንፋስ ዓይነት አቅጣጫውን የሚቀያይር ቢሆንም ንፋስ የሚጥለው (Wind Fall) ክስተት፣ ሁኖ ቀጥሏል ? " የሚሉ ጥያቄዎችን ከንፋሶች ዓይነትና መልክ ጋር ለመፈተሽ እንሞክራለን::

ቀደም ብሎም ይሁን ዛሬ የአንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕጣ ፈንታ ድህነትና ኋላቀርነት እንደነበረ፣ አሁንም የሀገራችን ዕጣ ፈንታ በተመሳሳይ መልኩ እንደቀጠለ መስማማት የሚቻል ይመስለኛል::

> በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ የሚፅፉ ግለሰብ ሁልጊዜ እንደሚገልፁት በአስተሳሰባችን፣ በባህላችን ፣ በሥርዓታችን፣ በፖሊሲዎቻችን ለእያንዳንዱ ዜጋና ቤተሰብ ጥረት፣ ኑሮና ስኬት ዋጋ አንሰጥም፡፡ ባለን ሃብትና ጥቂት በሆነችው ምርትና ዋጋዋ ዜጎችን በጥረታቸው፣ በድካማቸው ልክ የሚሸልም፣ የበለጠ እንዲሰሩ የሚያበረታታ ሥርዓት ገና አልጀመርንም

በኋላቀርነትና በድህነት ዕጣ ፈንታ ውስጥ ግን ምንም የለም ማለት አይደለም:: አጠቃላይ ቁሳዊ የሆነው ሀገራዊ ኋላቀርነትና ድህነት ምክንያት ልናመርት የምንችልበት ሃብት ቢኖረንም እነዚህን ተጠቅመን የሠራነው፣ ውጤቱ፣ ያመረትነውና በእጃችን ያለው ምርት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት ነው::

እጅግ አነስተኛ የሆነው ሀገራዊ ምርት የሀገራችንን አጠቃላይ ዕጣ ፈንታ ይወስናል:: ሃብቶቻችንን (የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሃብቶች) በጋራ የምንጠቀምበት ፣ ያመረትነውን ጥቂት ምርት፣ ዋጋውን (Real Value) እና በእጥረቱ ምክንያት ያለውን ድህነትና ችጋር የምንከፋፈልበት ባህልና አስተሳሰብ፤ ሥርዓት፣ ሕግ፣ መመሪያ፣ ደግሞ እጅግ በጣም ኋላቀር ስለሆነ በአንድ ሀገር ውስጥ ያለን ዜጎችን ዕጣ ፈንታ ሰማይና ምድር እንዳደረገው ቀጥለናል:: ይህ ተጨባጭ ሁኔታ እጅግ አነስተኛ ለሆነው ሀገራዊ ምርትና ለሀገራችን ዕጣ ፈንታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲኖረው ጦሱ እየዞረ ከኢኮኖሚው አልፎ ለፖለቲካ ግብ ግብ ከዚህም አልፎ ኢሰብኣዊ ለሆኑ ቀውሶች አድርሶናል::

የአንድ ሀገር ዜጎች የኑሮ ልዩነት ችግር የነጩ ካፒታሊዝም (ኮምኒስቶቻችን መሬት ላይ ቁጭ ብለው ኒዮ ሊበራሊዝም ሲሉ የሚወርፉት) አስተሳሰብና ሥርዓት ማኅበራዊ ችግር እንደሆነ ይነገራል:: ከፍ ቢል እጅግ ብዙ ምርት ባመረቱና ከፍተኛ ሰው ሠራሽ ሀብት ባከማቹ ካፒታሊስት ሀገሮች ያውም አሁን አሁን ኢኮኖሚያዊ ችግር እየሆነ ቢመጣ ነው::

በእኛ ሀገር ግን የፊውዳሊዝም፣ የሶሻሊዝምና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ንፋሶች ቢነፍሱም፣ በነበሩት ሥርዓቶቻችን ውስጥ ልዩነቱና ችግሩ ከፍተኛ ሁኖ ቀጥሏል :: በዚህ ረገድ ሰማይ ጠቀስ ለሆነ ችግር የበቃነው በሃያ ሰባት ዓመታት ውስጥ ሲሆን ለብዙኃኑ አንድ ሺህ በጣት ለሚቆጠሩትም ቢሆን መቶ ሺህ ብርቅ ከነበረበት ሁኔታ ተነስተን ነው:: ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዘገብን ብንልም አጠቃላይ ሀገራዊ ምርታችንም ሆነ ምርቱ ከሕዝብ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር የዓለም መጨረሻ ደረጃ ላይ ባለበት ሁኔታ ነው:: በእነዚህ ዓመታት ለብዙኃኑ ጭቁኖች ተብለን፤ ባለሃብቶች፣ የገበያ አክራሪዎችና ጥቂቶች እንደፈለጉ ብዙኃኑን በዝብዘው ሰማይ መድረስ እንዳይችሉ፣ ለሁሉም ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና ዘላቂ ዕድገት ተብሎ ሲለፈፍ፣ ሲሞገትና ሲመከት የነበረው ርዕዮተዓለም አብዮታዊ ዴሞክራሲ መሆኑን ስናስብ እና ዛሬ ውጤቱን ስንመለከት አብዮተኞቻችንን በመታዘብ ብቻ ማለፍ ያለብን አይመስለኝም::

በአንድ ሀገር ውስጥ ያለ ሃብት የተመረተ ምርት፣ ዋጋውና ጥቅሙ በፖለቲካ ብቻ እየተዘወሩ በሥልጣን አካፋ እየታፈሱ፣ በሙስና እየተመዘበሩ፣ ለዜጎች ሁሉ ፍትሐዊና አሳታፊ ባልሆኑ ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ለጥቂቶች ብቻ እየታቆሩ፣ ከታቆረው ለሚፈለጉትና ለጥቂቶች እየተንጠፈጠፉ ቀጥለናል:: የፖለቲካና የሥልጣን ንፋሶች ናቸው:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁሉም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሥልጣን ለመያዝ የሞት ሽረት ትግል ቢያደርግ፣ የተያዘን ሥልጣንና ጥቅም ለማስጠበቅ፣ በሂደት የተሠራና የተጠራቀመ ጉድ፣ ምዝበራ እንዳይገለጥ ኢሰብኣዊ በሆኑ ጭካኔዎች ጭምር ከእንስሳት የወረደ ተግባር ቢፈፅም ተገቢ እንጅ ሊደንቅ የሚገባ አይሆንም:: ►

ያለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ምዝበራዎች፣ የሰማናቸው የጭካኔ ድርጊቶች፣ ከግል ዘመናዊ የኢኮኖሚ የማምረቻና የሥራ ተቋማት በላይ የሆነው የግለሰብና የቡድን የፖለቲካ ድርጅቶቻችን ቁጥር፣ አሳፋሪ የፖለቲካ አሻጥሮቻችንና ሽኩቻዎቻችን የተያያዙ እና ከላይ የተገለፁት ሁኔታዎች ውጤት ናቸው::

ከእነዚህ የሚቀጥሉ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው እውነታዎች በሀገራችን ብርቅ አይደሉም:: ሌሎች ንፋሶች ማለት እንችላለን:: ስለዚህ ከአጠቃላይ ሁኔታዎች የምንረዳው የጥቂቶችን ችግር ብቻ ሳይሆን ሁላችንም በዚህ ረገድ ሃገርንና ሥርዓትን ገና እንዳልጨበጥናቸው ይመስለኛል::

በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ የሚፅፉ ግለሰብ ሁልጊዜ እንደሚገልፁት በአስተሳሰባችን፣ በባህላችን ፣ በሥርዓታችን፣ በፖሊሲዎቻችን ለእያንዳንዱ ዜጋና ቤተሰብ ጥረት፣ ኑሮና ስኬት ዋጋ አንሰጥም:: ባለን ሃብትና ጥቂት በሆነችው ምርትና ዋጋዋ ዜጎችን በጥረታቸው፣ በድካማቸው ልክ የሚሸልም፣ የበለጠ እንዲሰሩ የሚያበረታታ ሥርዓት ገና አልጀመርንም::

ጸሐፊው እንደሚሉት አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴን ጨምሮ የአትሌቶቻችንን የግለሰብ ስኬት የስኬቶቻቸውን ዋጋ ፣ ያስገኙትን ገቢ፣ የሚሠሩትን ሥራ፣ በሥራዎቻቸው ለዜጎች የፈጠሩትን የሥራ ዕድል፣ ሀገር የምትመለከተው ከአበበች ጎበናና ከሜቆዶንያ የበጎ ምግባር ሥራና ፋይዳቸው አሳንሳ ነው:: በስኬቱም ይሁን በችግሮቹ የመንግሥት ትኩረትን የሳበ የሚዲያ ሽፋን የሚያገኝ የሥራ ተቋም አናስታውስም፣ የዜጎችን ችግሮች ለጊዜው ቢያቃልሉም ብዙ ዓሉታዊ የጎንዮሽ ጉዳት ያላቸው የበጎ አድራጎት፣ የእርዳታ፣ የሥጦታ፣ የሎተሪ፣ የዕጣ፣ የሽልማት ፕሮጀክቶች የሁሉም ሚደያዎች፣ ተቋማትና የመንግሥት ጭምር አጀንዳዎች ናቸው:: ያውም በአደባባይና በግልፅ::

አንድ ቀን ድሬደዋ፣ ታይዋን በተሰኘው የገበያ ስፍራ አቅራቢያ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ቁመን ለሸመታ ወደ ገበያ አዳራሹ የገቡ ጓደኞቻችንን እየጠበቅን ነበር:: አንድ ስምንት ዓመት የሚሆናት ሕጻን ጥቂት ማስቲካዎች ይዛ እንድንገዛት ጠየቀችን:: ሁለታችንም አልመለስንላትም:: ሕፃኗ ከእኛ ሳትርቅ ሁለት በዕድሜያቸው የገፉ፣ በኑሯቸው የተጎሳቆሉ፣ እኛ የማንረዳውን ቋንቋ የሚናገሩ እናቶች በቋንቋቸው እየተናገሩ እጃቸውን ለምፅዋት ወደ እኛ ዘረጉ:: እናቶቹ አንጀት ይበላሉ፤ እኔ ወደ ኪሴ ገባሁ፣ በኪሴ ያገኘሁት ብር ባለ ዐሥር ብር ኖቶች ብቻ ነበር:: እነዚህ እናቶች አጅ እጄን ዕያዩ ስለነበር ዝርዝር አልፈለኩም፣ ወይም ልነሳቸው አልቻልኩም፣ ለእያንዳንዳቸው ዐሥር ዐሥር ብር ሰጠኋቸው::

እኔ ልብ ባልልም ይህን ያየችው ሕጻን አንድ እጇን ዘረጋችልኝ:: በአንድ እጇ ማስቲካዎችን ይዛለች:: ደነገጥኩ:: አንች እኮ ጎበዝ ልጅ ነሽ፣ እየሠራሽ ነው ስለዚህ መለመን የለብሽም ብዮ የፈሰሰውንና የማይታፈሰውን ለማፈስ ወሸከትኩ:: ከዚህ በኋላ አንጀቴ ባይችልም በአደባባይ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎቻችን ሁሉ ተመሳሳይ ነገሮችን ስመለከት ሀገር እያፈሰሰች እንደሆነ ይሰማኛል:: የምናፈሰው ደግሞ በቀላሉ የሚታፈስ አይደመስልም:: ቀጣይ የሕግና ፖሊሲ ንፋሶችንና ውጤታቸውን እንመልከት::

ግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተከትለን ላለፉት ዓመታት የግብርና ምርት ዕድገት ተመዝግቧል:: በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በግብርና ምርቶች ባለቤት በገጠር የተመለከትናቸው አዎንታዊ ለውጦች ግን አነስተኛ ናቸው:: ውስን በሆነው ሀገራዊ ምርት ሃገር ድሃ ብትሆንም ይህ ድህነትና ችግር በአንፃራዊነት የማይነካካቸው ባለጊዜዎች፣ መሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ የአገልግሎት ተቋማት፣ የከተማ ኗሪዎችን ነው:: የ ሀገራዊ ምርት ባለቤቶች፣ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ግን የችግሮች ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሾች ሁነው ለብዙ ዘመናት ቀጥለዋል:: እስካሁን ድረስ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ በእጁ ባለ፣ በባንክ ቁጠባ ሂሳቡ በተቀመጠ ገንዘብና ጥሪቱ በሀገራችን ግብርና ላይ የሚፈጠርን የአንድ ዓመት ቀውስ እንኳ (ለምሳሌ ድርቅ) መቋቋም አይችልም:: በከተሞች ግን ተመሳሳይ ነው ማለት አይቻልም:: ጥቂት ቢሆኑም ንግድ ፍቃድ አውጥተው ከውጭ ሸቀጦችን ስላስመጡ የግብርና ምርት ወደ ውጭ ስለላኩ፣ እንደንፋሱ ቢቀያየሩም ጥቂት ዓመታት ሠርተው ለልጅ ልጅ ሚሆን ጥሪት አከማችተዋል:: ፎርብስ ዘርዝሯቸዋል::

ሰፊ መሬት ባለበት ሀገር የከተማ መኖርያ ቦታና መሬት፣ የመንግሥት የንግድ ቦታና ሱቅ ብቻ የዜጎችን ዕጣ ፈንታ የሚቀይሩ በመሆናቸው ለሹሞቻችንም የፈተና ምንጭ ሁነዋል:: እነዚህን ሃብቶች መንግሥት የሚያስተዳድረው ከሃያና ሰላሳ ዓመታት በላይ በያዘው ውልና፣ ወረፋ ነው:: በዚህ ምክንያት ባለው የጥቅም ሰልፍና ሽሚያ ምክንያት መንግሥት የመኖርያ ቦታና ቤት ፈላጊዎችን የሚመርጠው በሊዝ ዋጋ ጨረታና በዕድል ዕጣ ብቻ ነው::

ሁሉንም ዜጎች እኩል ተመልክቶ የዜጎቹን የተለያየ ፋይዳ የማይመዝን፣ ያልተጋባ የጥቅመኝነትን ባሕሪን እና እውነተኛ የዜጎችን ፍላጎት በየወቅቱ ለመለየት የማይችል ሰነፍ መንግሥት፣ ከደርግ የመጀመርያ ዘመን ጀምሮ ከዐሥር ብር በታች የሚከራዩ የቀበሌ ቤቶችን ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ከማስተዳደር፣ እያወቀም ይሁን ሳያውቅ የዜጎችን መሠረታዊ የመኖርያ ቤትና ቦታ ፍላጎት ላይ ከጥቅመኞች ጋር አብሮ ከመነገድ፣ እንደ ብሔራዊ ሎተሪ ዕጣ መቶ ለአንዱ ከመሸለም ውጭ አማራጭ ሊኖረው አልቻለም::

የቀበሌና የመንግሥት ቤቶች ቁልፍ ስንት ጊዜ በምን ያህል ገንዘብ እንደተሸጡ፣ የከተማ ቦታና ቤት፣ የጋራ መኖርያ ቤቶች በማን እጅ እንደገቡ፣ የኪራይና የሽያጭ ዋጋቸው በአጭር ጊዜ ስንት እንደደረሰ ሁላችንም እናውቃለን:: በዚህ ሁኔታ የኪሳራ አደጋ በሌላቸው፣ ከፍተኛ የኪራይ ገቢና የሽያጭ ትርፍ በሚገኝባቸው፣ ንግድ ፈቃድና ግብር በሌለባቸው የከተማ ቦታና ቤት ባለቤትነት፣ ኪራይና ሽያጭ ሥራ ላይ የቻሉት ሁሉ ተቀናጅተው እንደሚረባረቡ ግልፅ ነው:: ቤቱንና ቦታውን ባይፈልገው፣ ቤት ለመሥራትና ለመግዛት አቅም ባይኖረው በዕድሉ የደረሰውን፣ ከግለሰብ ወይም ከመንግሥት ገዝቶ በመሸጥ፣ በዕዳ ዕገዳ በማስያዝና በማስተላለፍ በቀላሉ ለመጠቀም ሁሉም እንደሥራ ዕድሉን እየሞከረ ነው:: ለብዙዎች የተሳካ ሥራ ነው:: በመንግሥት ወቅታዊ፣ ዝርዝርና ትክክለኛ መረጃ በየወቅቱ መሬትና ቢያንስ መኖርያ ቤትና መሥርያ ቦታ ለዜጎች እውነተኛ ፍላጎት ካልቀረበ መሬትና ቤት ገዝቶ መሸጥ፣ ማከራየት፣ መደለልና ማሻሻጥ ሁነኛ ስራ ሁነው ይቀጥላሉ:: አሁንም መንግሥት የማያውቃቸው፣ ገቢ የማያገኝባቸው፣ ከፍተኛ ገንዘብ የሚንቀሳቀስባቸው መሸጦ ሥራዎች ናቸው::

ሕጋዊ የምንለው፣ ቀድሞ የዐሥር ሺህዎች ሄክታር መሬት ባለቤት የሆኑበት የሪል ስቴት ቢዝነስ ለተመሳሳይ ሥራም ሆነ፣ ከዚያ ውጭ ለሆኑ በማኅበርና በተናጠል ለዜጎች በሚኖር ወቅታዊ የመሬት አቅርቦት አማራጮች ካልታጀበ፣ ትክክለኛ አገልግሎት እንዲሰጥ መጠበቅ ሞኝነት ብቻ ነው:: ኩባንያዎች በማስታወቂያዎቻቸው ከእነሱ ቤት የገዙ ሰዎች ሲሸጡት ምን ያህል እንዳተረፉ እየገለፁ ሲሆን ወደፊት የተመሳሳይ ትርፍ ባለቤት የሚሆኑ የቤት ነጋዴዎችን በማማለል ላይ ናቸው:: ከትላንት ተነስቶ ዛሬን ያየውና የወደፊቱን በተመሳሳይ የጠበቀ አንዱ ቀደምት ኩባንያ ደግሞ "ከነገ ዛሬ ይሻላል!" የሚል ተስፋ አልባ የሆነ ማስታወቂያ ይጠቀም ነበር::

በዚህ ዙሪያ አሁን ባለንበት ሁኔታ የሚደረግ ማንኛውም ግብይት ትክክለኛ ገቢ የሚገኝበት ሥራ ሳይሆን መሸጦ ጥቅም የሚታፈስበት የጥገኝነት አካሄድ ነው:: የበለጠ የሚገርመው ሁኔታውን ከማስተካከል መንግሥትም በቁጥጥሩ ሥር ያዋለውን የዜጎች ሃብት እየሰፈረ፣ በየዓመቱ ጣራ ከሚነካ የመኖርያ ቦታ ሊዝ ሽያጭ እንኳ መሸጦ ጥቅምን እንደገቢ መሰብሰቡና ለዜጎቹ አርዓያ መሆኑ ነው::

ሽልማትና ዕድል ሌሎች ንፋሶች ሁነው ብቅ ብለዋል:: ብሔራዊ ሎቶሪ አለ፣ ሥራው የራሱ ቢሆንም አሉታዊ እንድምታዎቻቸውን ሳይመዝን ሥራውን ለሁሉም ይፈቅዳል::ቅርንጫፍ እንደመክፈት፣ ገቢውን እንደ ማሳደግ ብቻ ሳይቆጥረው አይቀርም:: በዚህ ረገድ የሥራና የስኬት አስተሳሰብ ፊታውራሪ መሆን የነበረባቸው ሁሉም ባንኮቻችን ዕጣ መተው በአደባባይ፣ በሚዲያ እየገለፁ የሚሸልሙ ናቸው:: ቢራ ፋብሪካዎች ይጠጡና በዕድልዎ ሕይወተዎን ይቀይሩ ይላሉ፤ የተለያየ ሸቀጥ ቸርቻሪ ሱፐር ማርኬቶች የዕድል ዕጣዎች ነበሯቸው፣ሜቅዶንያም ለምንዱባን ገቢ ሲሰበስብ ለዜጎች በዕጣ የሚለግሰው አላጣም:: በተንቀሳቃሽ ስልካችን አጭር የፅሁፍ መልዕክትን ተጠቀምንበት ካልን ለበጎ አድራጎትና ለሎቶሪ ነው ማለት ይቻላል:: በርግጥ አልፎ አልፎ በየአውዳመቱ የበዓል እንኳን አደረሳችሁ መልዕክቶች፣ የአንዱ ዓመታዊ ቀን ሲከበርም የግንዛቤ ማስጨበጫ መልዕክቶች ይደርሱናል:: ሙሉ ለሙሉ የሉም ባልልም ተመሳሳይ የሥራና የቢዝነስ መልዕክቶች ፣ የምርትና አገልግሎት ማስታወቂያዎች.. ወዘተ ከሽህ አንድ አይሆኑም::

ስለዚህ የሀገራችንን ዜጎች ተጨባጭ ኑሮ የሚወስኑት የምጣኔ ሃብት ፅንሰ ሐሳቦች ላይ የተመሠረቱ ፍትሐዊ የሆኑ ፖሊሰዎች ፣ ከእነዚህ የሚመነጩ ወቅታዊ የግለሰብ ሥራና ጥረት ናቸው ማለት አንችልም:: ፖለቲካ፣ ሥልጣን፣ እድሜ (ቀድሞ መገኘት ) ዕድልና አጋጣሚዎች የበለጠ ድርሻ ይዘው ቀጥለዋል:: በዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ከፖለቲካው ለውጥ ከኢኮኖሚያችን ዕድገት መጠበቅ ከባድ ይሆናል:: አመሰግናለሁ::



ተስፋዬ ሽብሩ

# ኢሕአዴግ ያከሰረው የዲፕሎማሲው ዓለም

“አምባሳደሮች ሲሾሙ ድግስ ነው:: የሚመደቡበትን ሲያውቁ ግን ፀብና ጭቅጭቅ ይመጣል:: ይህም የሆነው አምባሳደርነት የጡረታ የመዝናኛ ጥቅም የማግኛና የመጨረሻ አድርጎ ስለሚወስድ ነው:: አምባሳደር የሚሄደው ለግሉ ሳይሆን ለአገር ጉዳይ ነው:: ኢትዮጵያን ትርፋማ ለማድረግ ነው:: የግል ምቾትና ጥቅም ሁለተኛ አድርጎ መውሰድ አለበት:: ምን ያህል ባላሀብት አገር ቤት አምጥቶ ልማት ላይ እንዲሳተፉና በሌሎች ሥራዎች ውጤት ነው የሚለካው::” በማለት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለዲፕሎማቶች ትኩረት የሚስብ ንግግር ማድረጋቸው ይታወሳል::

## አዳዲስ አምባሳደሮችን ብቻ መመደብ

መንግሥት የመዋቅር ማሻሻያ በማድረግ አዳዲስ አምባሳደሮችን በመመደብ በዲፕሎማሲው መስክ ያለውን ክፍተት ለማስተካከል ጥረት ማድረጉ በጎ ጅምር ቢሆንም የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲው ክፍተት ስለማይታይበት ማሻሻያ ሳይደረግበት መቆየቱ ራሱን የቻለ ችግር ፈጣ መሆኑ ይታወቃል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ከመዋቅር ማሻሻያው በተጨማሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲው ክፍተት ስለማይታይበት ማሻሻያ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል:: ከጎረቤት አገራት ጋር ስላለው ድንበር በግልጽ የተቀመጠ ነገር እንደሌለም የጠቀሱት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ፣ ኢትዮጵያ የአፍሪቃ ኅብረት መቀመጫነቷ ለኢትዮጵያ አቅጣጫ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ አገራትም የተዘነጉ እንዳሉ በማንሳት ፖሊሲው ማሻሻያ እንደሚያስፈልገው የተወሰኑትን ክፍተቶች ለመጠቆም ምክረዋል::

የዘርፉ ምሁራንም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የተቀራረበ ሀሳብ ይሰጣሉ:: የቀድሞው የውጭ ጉይና የደህንነት ፖሊሲ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣምና ማሻሻያ በማድረግ ለውጥ ማምጣት ካልተቻለ አምባሳደሮችን ብቻ በመመደብ ከቀድሞው የተለየ ውጤት መጠበቅ ትርጉም የለሽ ድካም ነው በማለት ፖሊሲው በጥልቀት መፈተሽና ማስተካከያ መውሰድ እንዳለበት ያስገነዝባሉ::

በ1995 ዓ.ም የተዘጋጀው የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ የውስጥ ኃይል ከተጠናከረ የውጭ ተፅዕኖ መቋቋም ይቻላል:: ፖሊሲው የአገሪቱ ደህንነት ለከፋ አደጋ የሚጋለጠው፣ ለእልቂትና ለብተና የምንዳረገው፣ ልማትና ዴሞክራሲ እውን ሳይሆኑ ሲቀሩ እንደሆነ ያትታል::ይህንን መሰረት ያደረገው ፖሊሲ በአገራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ መጠነኛ ሥራ ቢሠራም በዴሞክራሲና አገራዊ አንድነት በማስፈኑ ረገድ ጉድለት አለበት:: ፖሊሲው ከተቀረፀ ረዘም ያለ ጊዜ ከመሆኑ ጋር ተደምሮ በተለይ የጎረቤት አገራት የምሥራቅ አፍሪቃም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች መቀየራቸው ፖሊሲው እንዲሻሻል ገፊ ምክንያት ይሆናል::

ባለፉት ዓመታት በጠላትነት የተፈረጁት እንደ ኤርትራ ያሉ አገራት እንዲሁም ወዳጅም ጠላትም ያልነበሩ የመካከለኛው ምሥራቅ አገራት የወዳጅነት ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት ተጀምሯል::

የጎረቤት አገራትም ሆነ የሌሎች አገራት ተፅዕኖ ቀድሞ ከነበረው በላቀ ደረጃ ተጠናክሮ መቀጠሉ የውጭ ጉዳይ ደህንነት ፖሊሲው ያለበት ክፍተትን ለመፈተሽ ጊዜው አሁን ነው በማለት አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ::

በአገር ውስጥ ፖሊሲ መነሻነት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተተንትኖ በግልፅ አቅጣጫ ተቀምጦ መንግሥት ወደ ሥራ በአፋጣኝ መግባት እንዳለበት ያስረዳሉ:: ከዚህ ውጪ አምባሳደሮችን መመደብ ብቻ ብዙም የተለየ ሥራ እንዳልሆነና ምደባና መዋቅር ማስተካከል ብቻ ቀድሞም የነበረ አሰራር መሆኑን ያነጋገርናቸው ባለሙያዎች ይጠቁማሉ::

## የአፈጻጸም ችግር

የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲው መሰረታዊ ችግሩ የፖሊስ አይደለም የሚሉም አስተያየት ሰጪዎች አልታጡም:: በርግጥ ፖሊሲው ላይ አንዳንድ አነስተኛ ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ቢያምኑም ዋናው የውጭ ጉዳይ እና ደህንነት ፖሊሲው ያጋጠመው የአፈፃፀም ችግር ነው በማለት በአገሪቱ ላለፉት 27 ዓመታት የተፈጠረውን የዲፕሎማሲ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ ችግሮችን ያስረዳሉ::

ይህንን አባባላቸውን ለማስረዳት ሕወሓት መራሹ መንግሥት አምባሳደሮችን ዲፕሎማቶችን የሚመድበው በብሔር ተዋፅኦ መሠረት ያደረገ መሆኑን ይጠቅሳሉ:: እነዚህ ባሙያዎች ያልሰለጠኑ የፖለቲካ ሹመኞች መሆናቸው፣ አገሪቱ ለገጠማት የውጭ ጉዳይ እና የደህንነት እንዲሁም የዲፕሎማሲ ቀውስ ያስረዳል::

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት በውጭ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር የፈጠረው መልካም ግንኙነት አዎንታዊ ጎን እንዳለው ይጠቀሳል:: የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም በእውቀታቸው የሚያገለግሉ ብቁ ባለሙያዎችን በመመደቡ ኢትዮጵያ የተሻለ ትርፍ እንድታገኝ ማድረግ ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግልፅ እንዳስቀመጡት አምባሳደሮች አገሪቱ ውስጥ በኢኮኖሚ፣በፖለቲካ በማኅበራዊ ዘርፍ ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ኢትዮጵያ ያላትን አማራጭ ለዓለም ገበያ በመሸጥ ቦታ እንዲኖራት ማድረግ መሆኑን አስገንዝበዋል::የአገሪቱን ትክክለኛ ገጽታ የሚያቀርብ አምባሳደር ከሌላት በዓለም ገበያ ቦታ አይኖራትም፤ በመሆኑም የአገሪቱን ፍላጎት ለዓለም ገበያ መሸጥ የሚያስችል ብቃት በመያዝ ለአገራቸው አስተዋፅዖ ማድረግ እንዳለባቸው ማስገንዘባቸው ያለፉትን ደካማ የአፈፃፀምና የፖሊሲ ክፍተቶች ጠልቀው በመረዳታቸው እንደሆነ የማይካድ ሐቅ ነው::

## የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ

ኢትዮጵያ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ዕውቅና ያላትን ያህል በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ መሆን ያልቻለች አገር ነች:: በፖለቲካው ያላትን ዕውቅና በኢኮኖሚው ዘርፍ ለመድገም አሁን የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ መጠቀም ይገባል::

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዓቀፉ ኅብረተሰቡ ያገኘውን ተቀባይነት በመጠቀም ኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲ የሚያስገኘውን ጥቅም አሟጦ መጠቀም ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ መልካም አጋጣሚ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ::

በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው የተመደቡት አቶ ፍፁም አረጋም ይህንን ሀሳብ ይጋራሉ:: አዲስ በተመደቡበት የዲፕሎማትነት ቦታ ያልተሞከሩ ዕድሎችን በመፈተሽ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ልታበረክት የምትችለውን የላቀ ሚና ለማሳደግ እንደሚሰሩ ተናግረዋል:: አሁን የተጀመረው ለውጥ ከአሜሪካ ጋር የበለጠ የሚያቀራርብ በኢኮኖሚውም ሆነ በሌሎች ግንኙነቶች የላቀ ሥራ ለመስራት ዕድል እንደሚፈጥር ጠቁመዋል::

ሰሞኑን ለአምስት ቀናት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሊካሄድ በነበረው የአምባሳደሮች ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲና ለቀጠናዊ ውህደት የሚጠበቅባትን ሚና በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የዲፕሎማሲያዊ ተቋማት ▶

መገንባትና ስትራቴጂካዊ አጋሮች ማፍራት ዋናው ተልዕኮ መሆኑ ተጠቅሷል:: የተያዘውን የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ዕቅድ ለማሳካት ከባለድርሻ አካላት ጋር ሊኖር ስለሚገባው ትብብር ትኩረት ተሰጥቶት ውይይት መደረጉም ታውቋል::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ አገሪቱ በሚቀያየር የዓለም ፖለቲካ ውስጥ ጥቅሟን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማስጠበቅ በምትከተለው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ረገድ ያሉትን ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶች አንስተው ማብራሪያ ሰጥተዋል:: የውጭ ጉዳይን ሚኒስቴርን ተቋማዊ ለውጥ ለማሻሻል መስሪያ ቤቱ የሚያደርገው መዋቅራዊ ለውጥ በአገር ዓቀፍ ደረጃ ከሚዳረገው ለውጥ የሚታይ መሆኑንም ዶ/ር ወርቅነህ አንስተዋል::

የዲፕሎማሲ ተልዕኮውንም ለማሳካት አገሪቱ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች 46 ኤምባሲዎችና 14 ቆንስላ ጽ/ቤቶችን በመክፈት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት ላይ ትገኛለች ብለዋል::

ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ ያስቀመጠችው ግብ እንዲሳካ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው የራሱን ወሳኝ ድርሻ ሊወጣ እንደሚችል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ገልጿል:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ማርቆስ ተክሌ በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ እና የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል::

የዓለም አቀፍ ግንኙነትና በዲፕሎማሲ ዘርፍ እውቅ ፀሐፊ የሆነው ሄድሌድ ቡል “Anarchical society፡ A Study of order in Politics” በተሰኘ መጽሐፍ የዲፕሎማሲን ዋና ዋና ተግባራት ይዘረዝራል::በአገራት መሪዎች ታላላቅ ዲፕሎማቶች እና በሌሎች የዘርፉ ተዋናዮች (Actors) መካከል የሚደረውን ድርድር ውይይት ዋነኛው ጉዳይ መሆኑን ሄድሌይ ይጠቅስና ከዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ውጪ ዓለም ዐቀፉ ማኅበረሰቡም ሆነ ዓለምዓቀፉ ሥርዓት (System) ሊኖርና ሊሠራ አይችልም በማለት የዲፕሎማሲውን ዓለም ዋነኛ ተግባር ይጠቁማል::

**ሌላው የዲፕሎማሲ ተግባር የአገሮችን የደህንነት መረጃዎች በማነፍነት ለራስ ጥቅም ለአገር ጥቅም እንዲውል የማድረግ የስለላ ዘዴንም እንደሚጨምር ሄድ ሌይ ይጠቁምና የዲፕሎማሲ ተግባር ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ መሆኑን ያስረዳል**

በሁለተኛ ደረጃ የዲፕሎማሲው ተግባር ውስብስብ የሆኑ ድርድሮችን በማድረግ ስምምነት ላይ እንዲዳረስ እና ለችግሮቹ መውጫውን መንገድ መፈለግ መሆኑን ይጠቅሳል:: በድርድሮች ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ባይችል እንኳን ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች መሥራታቸው መቀጠሉ አይቀርም የሚለው ሄድ ሌድ ድርደሩና ወደ ስምምነት የሚኬድበት መንገድ እየጠበበና ድርድሩ የሚቋረጥ ከሆነ በአገራት መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ዕድሜያቸው አጭርና አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል:: ስለዚህ ዲፕሎማሲ ተግባሩ ይህንን አስቸጋ ሁኔታ በመቀልበስ ስምምነቶች ተግባር ላይ እንዲውሉ አዎንታዊ ሚናውን ይወጣል በማለት የዲፕሎማሲውን ዓለም አስፈላጊነት ይተነትናል::

ሌላው የዲፕሎማሲ ተግባር የአገሮችን የደህንነት መረጃዎች በማነፍነት ለራስ ጥቅም ለአገር ጥቅም እንዲውል የማድረግ የስለላ ዘዴንም እንደሚጨምር ሄድ ሌይ ይጠቁምና የዲፕሎማሲ ተግባር ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ መሆኑን ያስረዳል::

## ዲፕሎማቱ ማን ነው

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንደተናገሩት አምባሳደርነት ጡረታ የመውጫ የማረፊያ ቦታ አይደለም:: የራስ ጥቅም ማስኬጃ ሀብት ማጋበሻም ሊሆን አይገባም:: የማይፈለገውን ግለሰብ ከፖለቲካ ማግለያም አይደለም::

አምባሳደሩ ወይም ዲፕሎማቱ ዘርፈ ብዙ የሆነ ዕውቀት ችሎታ ሊኖረው ይገባል:: ተናግሮ የማሳመን፣ የትንተና ብቃት፣ የአስተዳደር ችሎታ ሊኖረው ይገባል:: በሚያደርገው ድርድር እና ውይይት አሻሚ የሆኑ ሀሳቦችን በመስጠትና ነገሮችን ሸፋፍኖ የማለፍ ጥበብና ብቃትን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊጠቀምበት ይችላል::

አምባሳደሩ የውጭ ቋንቋ ዕውቀት የአገሮችን ባህል አኗኗር ከሞላ ጎደል ማወቅና ዝግጁ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል:: በአምሳደርነት የሚያገለግልበት አገር መንግሥትን ሀሳቦች የፍላጎት ቀድሞ በማወቅ የራሱ አገር ከዛ ተጠቃሚ የምትሆንብት መስመር ሊተልም ይገባል:: አምባሳደሩ የአገሩ መንግስት ፖሊሲዎች በፖለቲካው በኢኮኖሚው ዙሪያ ያለውን እንቅስቃሴና አሰራር በጥልቀት ሊረዳ ግድ ይለዋል:: የአገሪቱን ሕጎች የቢሮክሲውን ሂደት መረዳትም ለሚሠራው ሥራ ይበጀዋል:: ከደህንነት እና ወታደራዊ ተቋማት ጋር ለጋራ ዓላማና ለአገር ደህንነት ተቀራርበው መስራት እንዳለባቸው የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ::

ዲፕሎማት ሰባት ባህሪያትን መላበስ እንዳለበት ሀሮልድ ኒኮልስን የተባሉ እንግሊዛዊ ዲፕሎማት ይናገራሉ::እውነተኛት ፣ ትክክለኛት፣ የተረጋጋ፣ ስሜቱን የሚቆጣጠር፣ ትዕግስተኛ፣ ትሁት እና ታማኝነት ናቸው::

የአገራት ግንኙነት ሰላማዊ መሆነ መንገድ ላይ ካለ በጣም ጠቃሚው የዲፕሎማሲ አገልግሎት ይዘነጋል:: ዲፕሎማቱ ቦታ አይኖረውም ወደ ኋላ ይገፋል:: ነገር ግን ዲፕሎማሲ በሰላሙም ጊዜ አገራትን ለጋራ ጥቅም በማሰለፍ ኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማቱ ከሚያገለግሉበት አገር በኢኮኖሚ በፖለቲካው በሌሎችም ዘርፎች ያሉ እድሎችን አሟጦ በመጠቀም ለአገሩ መስራት ካልቻለ የአምባሳደርነት ተግባሩን በብቃት አልተወጣም ሊባል ይችላል:: እንዲሁም በተመደቡበት አገር የሚኖሩትን ዜጎቹን ኢትዮጵያውያንን መብት በማስከበር ኢትዮጵያዊነት ክብር መሆኑን ማሳየት እንደሚገባና ኤምባሲዎችም ለዜጎች በደስታ በሀዘን በንግድ ሥራ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ክፍት በማድረግ እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተናገሩ ሀሳብ ተሿሚዎቹም ሆኑ የቀድሞዎች አምባሰደሮች ልብ ሊሉት ይገባል::

## የአዲስ ተሿሚዎች አምባሳደሮች ድምጽ

አምባሳደሮችና እና ዲፕሎማቶች ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ ውጤታማ ሥራ እንደሚያከናውኑ ጠንካራ ክትትል የሚደረግ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጠቅሶ አምባሳደሮች እና ዲፕሎማቶች የሚያከናውኑትን ሥራ በየጊዜው ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የሚገመግም መሆኑን የሚኒስትሩ ቃል አቀባይ አቶ ነብያት ጌታቸው አስታውቀዋል::

በቅርቡ ኢትዮጵያን በውጭ አገራት የሚወክሉ አምባሳደሮች ምሁራን እና ታዋቂ ግለሰቦች የተካተቱበት የአምባሳደሮች ሹመት መካሄዱ የሚታወስ ሲሆን በአሜሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር የሆኑት አቶ ፍፁም አረጋ አሁን ላይ የተፈጠረው ለውጥ ከአሜሪካ ጋር ያለንን ግንኙነት ይበልጥ እንዲጠናከር ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል:: ይህንን ዕድል ተጠቅመው ከኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ጋር በመሆን የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ለመስራት ማቀዳቸውን ተናግረዋል፡፧

በአዲሱ ሹመት በጀርመን የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሙሉ ሰለሞን ከአሁን በፊት በንግድ ሥራ ላይ ያላቸውን ልምድ በመጠቀም አገራቸውም ለመጥቀም ማቀዳቸውን ጠቁመዋል:: አምባሳደር ሙሉ ጀርመናዊያን ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በስፋት እንዲመጡ በማድረግ አሁን በአገሪቱ ያለውን የለውጥ እንቅስቃሴ በተገቢው ደረጃ ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን በማናገር አዲስ የተሾሙት የአምባሳደር ቦታ ይዞት የሚመጣውን ከፍ ያለ አገራዊ ኃላፊነት ለማስረዳት ሞክረዋል::

በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሆነው የተሾሙት አምባሳደር ሄኖክ ተፈራም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቅ የአፍሪካን ድምጽ በማሰማት ኃላፊነታቸውን ለመወጣጥ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኂላ የመጣው ለውጥ አገር አቀፍ ብቻ ሳይሆን ቀጠናዊ ለውጥም ያመጣ ነው ፧ያሉት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ታዬ አፅቀ ሥላሴ ፣በአዲሱ አስተዳደር የዲፕሎማሲውን ሥራ ከመከላከል ወደ ትብብር ዲፕሎማሲ መቀየሩ ጠቁመዋል::

# የሁሉም የኢትዮጵያዊ . . .

ከገጽ 10 የዞረ

ስለዚህ በአንድነታችን ተማምነን ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ እንደሚለው ወደ ፊት መራመድ ነው ያለብን::

**ግዮን፡- የአሁኑ ትውልድና ኢትዮጵያዊነት በደንብ ተቆራኝተዋል ማለት ይቻላል?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** እስካሁን ድረስ ይህ ትውልድ ጎሰኝነቱ ነው የተነገረውና "እኔ ጎሳዬን ነኝ" ሲል ከርሟል:: ከእንግዲህ በኋላ ይሄ ጠፍቶ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለትን ማዳበር አለበት:: ከዚህ በተጨማሪ ባለፈ የአባቶቹና አያቶቹ ታሪክ እኔ እንዲህ ዓይነት ጀግና ነኝ ብሎ እያወራ ብቻ መኖር የለበትም:: ያንን እውነትና ምሳሌ ከተረዳ እኔም እንደ እነሱ እሆናሁ ብሎ የአባቶቹን ታሪክ የትምህርትና የጥበብ መስፈንጠሪያ አድርጎ ወደ ፊት በመሄድ አዲስ ታሪክ ለመጻፍ መጣር ይኖርበታል::ዋናው መቻሉን፣ ለራሱ ማሳመን ነው ያለበት:: ትልቁ ነገር መሰረቱን ማወቅ፣ ቋንቋው ላይ አለማተኮር፣ ኢትዮጵያዊነቱን ማስቀደም ከቻለ በሚፈለገውና በሚገባው መጠን ከኢትዮጵያዊነቱ ጋር ሊቆራኝ ይችላል::

**ግዮን፡- የኢትዮጵያዊነት ስሜትና ድንበር ልዩነታቸው እንዴት ይገለፃል?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-**ሀገራችን እስከዛሬ ያተረፈችውንና ኢትዮጵያ ያሰኟትን እሴቶች መቀበልና ባለበት ሁኔታ ወደ ፊት ማራመድ ነው የሚያስፈልገው እንጂ በክልላዊነት መጥበብ መጥፎ ነው:: ለ27 ዓመት ባየነው ተሞክሮ ሰው በቋንቋ ተከልሎ የመቆየቱ ውጤት መጠላላትና መተላለቅ ነው የሆነው:: ያንን መተው፤ ግን ደግሞ እስካሁን ድረስ ያለንና የተረፈችዋን ዳር ድንበር ከጠላት ማስከበር፣ በእዛ አንድ ሆኖ መቆም፣ ሀገሪቷን ማፍቀር መውደድ ይሄ መልካምነት ነው::

**ግዮን፡- ከ27 ዓመት በኋላ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በሕወሓት/ኢህአዴግ ከነበረው የጎሰኝነት ስሜት በፀዳ መልኩ ኢትዮጵያዊነትን እያስቀደሙ ይገኛሉ አስተሳሰባቸውንም ሆነ እርሳቸውን እንዴት አገኟቸው?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** ባለፉት አርባ አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በሚለው ዙሪያ ሁለት ነገሮችን አልሰማንም:: በርግጥ እነ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ኢትዮጵያ ይሉ ነበር፤ እሱን የደርግ ጊዜን እንተወው:: በ27 ዓመታት ውስጥ ግን ኢትዮጵያ የሚለውን ስም መጠየፍና እንደ እርም ማየት ተጀምሯል፤ ከአቶ መለስ ዜናዊ እነ ጠ/ሚ ዐቢይ ወደ ሥልጣን ከመምጣታቸው በፊት የነበሩት መሪዎች ሁሉም ኢትዮጵያ ሀገራችን ናት ብለው አያውቁም::

አሁን ግን ሁለት ነገሮች መጥተዋል:: የመጀመሪያው እግዚአብሔን መፍራት ተጀመረ፤ በእነዛ ዓመታት ተረስቶና ወድቆ የነበረውን ኢትዮጵያዊነት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አነሳው:: ከንጉሡ አፄ ኃይለሥላሴ በኋላ "እግዚአብሔር ይረዳናል፣ ወይም እግዚአብሔር ሀገራችንን ይጠብቅልን" የሚሉ የሀገር መሪዎች አልነበሩንም::

በጠ/ሚ ዐቢይ ላይ ሁለት ነገር ነው የተከሰተው፤ አንደኛው ፈሪሃ እግዝአብሔር ያላቸው መሪ መሆናቸው ሲሆን ሁለተኛው



ለኢትዮጵያዊነት ስሜት ያላቸው ጽኑ እምነት ነው፤"ስንኖር ኢትዮጵያዊ፣ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ ነን" የሚል አባባል አምጥተው ብዙዎቻችንን በደስታ አፍነክንከውናል::ይሄ በጣም ትልቅ ለውጥና የሚደገፍ እርምጃ ነው::ባለፉት 30 ዓመታት ያደረግኩትን ተጋድሎና የሄድኩበትን መንገድ ነው አሁን እየሆነ ያለው:: ለበርካታ ዘመናት የተለያዩ መጽሔቶች ላይ ኢትዮጵያን ሪቪውን ጨምሮ ኢትዮጵያውያን አንድ ዘር እንደሆኑ የሚገልጹ መጣጥፎችን በአንግሊዘኛ ስጽፍ ቆይቻለሁ:: እነዚህን ታሪኮች ወደ መጽሐፍ የቀየርኩት መጨረሻ ላይ ነው::

**ግዮን፡- ወደ እዚህ ከመጡ በኋላ ጠ/ሚ/ር ዐቢይን አግኝተዋቸዋል?**

**ፕ/ር ፍቅሬ-** አላገኘኋቸውም:: እኔ ያተኮርኩት ሥራዬ ላይ ነው፤ እነሱን ሳላውቃቸው በፊት የዛሬ ሰላሳ አንድ ዓመት ነው፤ የኢትዮጵያውያንን አንድነት ማራመድ የጀመርኩት:: መጀመሪያ ላይ እንደውም ኢትዮጵያዊ ነኝ በሚል ግጥም ነው የገለፅኩት፤ "ይህቺ ናት የእኔ ምድር" የሚል ነበር:: ሠላሳ አንድ ዓመት ሙሉ በጀርመን ሬድዮ ይደገም እየተባለ የተላለፈ ነው:: አሁን እንደውም በድምፄ ተቀርጬ በካሴት አውጥቼዋለሁ፤ በመጽሐፍ መልክም ለገበያ ቀርቧል:: የኢትዮጵያን ትልቅነት በከፍተኛ የግጥም አፃፃፍ የሚገልፅ ረዥም ግጥም ነው::

የአማርኛን ሥነ ግጥም ለሦስት ከፍዬዋለሁ፤ አጭሯ ከሁለት ስንኝ እስከ አስራሁለት፤ ረዘምዛሜ ከሁለት ገፅ እስከ አራት ገፅ፤ ከዛ በላይ ረዥም የሆነው ረዥሜ ተብሏል:: የእኔ ግጥም ሳነበው አንድ ሰዐት ከዐሥር ደቂቃ ነው የሚወስደው:: ምናልባት በአማርኛ ታሪክ ረዥሙ አንድ ወጥ ግጥም የእኔ ነው የሚመስለኝ::

**ግዮን፡- ከበርካታ ዓመታት በኋላ አሁን ያለው የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲህ ጎልቶ ሲወጣ ሲያዩ ምን ተሰማዎት?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** እጅግ በጣም ማመን ነው ያቃተኝ:: አቶ ለማ መገርሳም ሆነ ጠ/ሚ ዐቢይ በዚህን ያህል ደረጃ ጥልቅ የሆነ የሀገር ፍቅር ስሜት ይዘው ሲመጡ ማመን ነው ያቃተኝ:: "ጣናን ኬኛ" ብለው ባህርዳር በመሄድ "ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው" የሚለውን ንግግር ሲያደርጉ ከሚገባው በላይ በጣም ነው ደስ ያለኝ:: በህልሜ ነው በእውኔ የሚል ጭንቀት ውስጥ ነው የከተተኝ:: በእኔ ዕድሜ ይሄ ይሆናል ብዬ አላስብም ነበር::በዚህ ዘመን በኢትዮጵያዊነት ላይ ማመን ብቻ ነው የሚያስፈልገው፤ ኢትዮጵያችን የሁላችንም ናት::

የቋንቋ ፖለቲካ አይጠቅምም:: ጎሰኝነትን ወይንም ቋንቋን ከተከተልን ይበታትነናል እንጂ አንድነታችንን ሊያጠናክርልን አይችልም:: እንዲያውም የጨረባ ተስካር ነው የሚሆነው::

ሁላችንም የተስማማንበት ቋንቋ አለ፤ይኸውም በዝግመተ ለውጥ ለዘመናት እየጎለበተ የሄደው አማርኛ ነው:: ከዛ ቀጥሎ ደግሞ በብዛት ሰው የሚናገርበት ቋንቋ ኦሮምኛ ነው፤ ሁለቱን በተጓዳኝ ወይም በእኩልነት የኢትዮጵያ መንግሥት የመግባቢያ ቋንቋ ቢሆኑና ቢፀድቁ ጥሩ ይሆናል::

**ግዮን፡- ትምህርቱ በምን ዓይነት መንገድ ነው መሰጠት ያለበት?**

**ፕ/ር ፍቅሬ፡-** በኢትዮጵያ ፊደል ብቻ:: ምክንያቱም የኢትዮጵያን ሁኔታ በደንብ የሚገልፀው የራሳችን ፊደል ብቻ ነው:: እንደ `ጨ`፣ `ቀ` 'ጠ' ዓይነት ድምፆችን የሚገልፁት የኢትዮጵያ ፊደሎች ናቸው:: በነገራችን ላይ ይሄ ፊደል የሁላችንም አባቶች የመሠረቱት እንጂ የአንድ ጎሳ ወይም የአማራ ወይም የትግሬም አይደለም:: የእነሱ ብቻ አደርጎ ማሰብ ከባድ ስህተት ነው::

የእነርሱ እንኳን ቢሆን የማናውቃቸውን ፈረንጆች ላቲንስ ጋር ሄዶ ከማምጣትና ባዕድ ከመሆን የምናውቀውንና አባቶቻችን የኖሩበትን ብንጠቀም ነው የሚሻለው:: አሁን ያለው የኦሮሞ ቋንቋ መማሪያ ላቲን ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ለሚጠቀምበት ጎሳ ራሱ ባዕድ ነው:: በጣም የሚገርመው መጽሐፌ ላይም አሳይቻለሁ አራት ገፅ በላቲን ቋንቋ የሚፃፈው ኦሮሞኛ፣ በኢትዮጵያ ፊደል አንድ ገፅ ከግማሽ ብቻ ነው የሚፈጀው:: ከእጥፍ በላይ ነው የባዕድ ፊደሉ ያመጣው ልዩነት::

የዛሬ መቶ ሰላሳ ዓመት መጽሐፍ ውስጥ በኦሮምኛ ተፅፏል፤ በግዕዝ ፊደል ማለት ነው:: አናሲሞስ ነሲብ የሚባሉ ስዊድን ሀገር የተማሩ ኢትዮጵያዊ ፓስተር፣ እርሳቸው ፊደሉን በደንብ ቀርፀው ጽፈውታል:: አሁንም አንዳንድ የኦሮምኛ ድምፆች በአማርኛ ፊደል ውስጥ የሉም የሚባለው ሀሰት ነው:: ዶ/ር አበራ ሞላ የተባለ ሊቅ ለኦሮሞም፣ ለሀዲያም ለከምባታም የሚስማማ የኢትዮጵያ ድምፆችን በሶፍትዌር አስገብቷል:: ቀና መንፈስ ካለ እነሱን መጠቀም እንችላለን:: በኢትዮጵያ ፊደል መግለፅ የማይቻል ምንም የኦሮምኛ ድምፅ የለም:: አሁን ያለፈው አልፏል፤ ለአንዲት ኢትዮጵያ ሁላችንም በጋራ በፍቅር ከሠራን፣ ዘራችን ደማችን አንድ መሆኑን ካመንን፣ እንደ ጥንቱ ትልቅ የማንሆንበት ምክንያት የለም::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**



ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

# ፖለቲካና ሕግ ይራራቁ

የሕግ የበላይነት ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ ሁሉም ዜጎች ከሕግ በታች መሆናቸውንና በሕግ ፊት ሁሉም እኩል መሆናቸውን የሚያመላክት ጽንሰ ሐሳብ ነው። ይህን ሥርዓት መገንባት ዜጎች በኃይለኞች በተለይ ከምንም በላይ ኃይል ባለው መንግሥት እንዳይጠቁ ዋስትና የሚሰጥ ነው:: ፖለቲካና ሕግን እያፋራረቁ መጓዝ ዘመናዊ የመንግሥት ሥርዓት ሊገነባ አይችልም። የሕግ የበላይነት ከሌለ ዘመናዊ መንግሥት ጨርሶ ሊኖር አይችልም:: በየትኛውም ሀገር መንግሥት በሕግ ካልተገደበ ትልቅ አደጋ ነው:: አንድ መንግሥት ፈላጭ ቆራጭ እንዲሆን ምንጩም ይሄው ነው። ስለዚህ የሕግ የበላይነት ማለት ሁሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን እንጂ ከፖለቲካ ጋር እያደባለቁ የሕግ የበላይነትን እንዲጣስ ማድረግ ማለት አይደለም:: ዛሬ ግን በሀገራችን ሕግ ያስከብራል የተባለው የሕግ አካል ፖለቲካው ልቆበት፤ ሕግ ማስከበር አቅቶት፣ ዜጎች ከሕግ ውጪ በጠራራ ፀሐይ ግፍ ሲፈፀምባቸው ዝም ብሎ መመልከት የተለመደ የዘወትር ተግባር ከሆነ ከረመ:: ለሀገራችን ይህ ድርጊት አሳዛኝም አሳፋሪም ነው::

> የሚመላለሱ ያሉትን ያህል፣ ክሳቸው ተቋርጦ በነጻ የሚሰናበቱ ስንቶች በብዛት ታይተዋል፤ ፡ ‘አንድ ንፁህ ሰው ያላግባብ ከሚታሰር ይልቅ አንድ ሺህ ወንጀለኞች ቢለቀቁ ይሻላል’ የሚለው የሕግ መርህ እየተጣሰ በርካታ በደሎች የደረሱባቸው አሉ፡፡ በጉልበተኞች ንብረታቸውን የተቀሙ፣ ሰብዓዊ ክብራቸው የተደፈረ፣ በተከበሩበት አገር የተዋረዱ፣ ያለጥፋታቸው የመከራ ገፈት እንዲቀምሱ የተደረጉ፣ ወዘተ በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ከጥርጣሬ አልፎ ጥላቻ ቢፈጠርባቸው ምን ይገርማል

ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ መንግሥት የማይተካ ሚና ይኑረው እንጂ ኅብረተሰቡ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ያለው አስተዋፅኦም ከፍተኛ ነው። የሕግ የበላይነት ለሰላም መረጋገጥ የመጀመሪያውና ትልቁ መስፈርት ነው። አገር እንደ አገር ልትቀጥል የምትችለው በተመሳሳይ መንግሥትም እንደ መንግሥት ሊከበርና አገር ሊያስተዳድር የሚችለው የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ሰዐት የሕግ የበላይነትና ፖለቲካ ከዘፈቀደ ውሳኔና ከማንአለብኝነት ጋር እየተያያዘ ነው:: በአገራችን አንዳንድ የክልል መንግሥታት ውስጥ በየደረጃው ሥልጣን የተቆናጠጡ ሰዎች በሆነ አጋጣሚ ሲታሰሩ፣ ሲከሰሱና ፍትሕ ደጃፍ ቀርበው ሲከራከሩ የፍትሕ ጉዳይን አንገብጋቢነት ሲመሰክሩ በተደጋጋሚ በአደባባይ ተሰምተዋል:: ቀድሞ ሥልጣን ላይ እያሉ ትዝ ያላላቸው ፍትሕ እስር ቤት ውስጥ ሆነው ስለ ፍትህ መዛባት ብዙ ተናግረውለታል:: እነሱ በሥልጣን ላይ ሳሉ የረባ የፍትሕ ሥርዓት መገንባት ባለመቻላቸው ምክንያት ሲያዝኑም ተሰምቷል:: የሚያሳዝነው ግን ሁሉ በእጃቸው ሁሉ በደጃቸው በነበረ ጊዜ ፍትሕን ከፖለቲካ ጋር እንዲደበላለቅ ግንባር ቀደም ሆነው የሠሩ፤ እነሱ ሲታሰሩና ፍትሕ ሲጓደልባቸው ቢጮሁ ምንም የሚገርም ጉዳይ አይሆንም:: በሁሉም መንግሥታት ጊዜ ሕግና ሕገ መንግሥት ቢኖሩም የዜጎች የሕግ የበላይነት ደምቀው ቢጻፉም፣ በተግባር ሥራ ላይ መዋል እያቃታቸው ሕግና ፖለቲካን እያደባለቁ ዜጎችን ደም እንባ አስለቅሰዋል::

ከወረቀት ጌጥነት ያላለፉ የሚያምሩ የሕግ የበላይነት የመብት አንቀጾች በፖለቲካ ወገንተኝነት ምክንያት እየተዳጡ ስንቶች ያለ ኃጢያታቸው በእስር ማቀዋል:: ከሀገር ተሰደዋል:: ዛሬም የምናየው ይህ ሕግንና ፖለቲካን እያደባለቁ ማስኬድ የአገርን ህመም እንጂ ጤና አያሳይም:: ይልቁንም ፖለቲካንና ሕግን አደባልቆ መሥራት የአገርን ፅኑ ሕመም ላይ መሆኗን ዛሬም በግላጭ በደንብ እያሳየን ነው:: አሁንም በሕግ የሚፈለግን ግለሰብ ከፖለቲካ አመለካከትና ከብሔር ጋር በማያያዝ ለሕግ እንዲቀርብ አለማድረግ፤ሕግንና ፖለቲካን ማደባለቅ ነው::

ሕግ ሁሉንም ዜጋ እኩል ያያል እስከተባለ ድረስ ደግሞ እንደ ሀገር ሁሉም አጥፊ እኩል በሕግ ፊት እንዲታይ ማድረግ እንጂ፤ በፖለቲካና በብሔር ሽፋን አንደኛው ተጠያቂ ሌላው የሚተው ሊሆን አይገባም:: የታየው ችግር እንደ ሥርዓት ችግር መኖሩን መግባባት ላይ ከተደረሰ ሁሉም በሀገሪቱ ሕግ እኩል ሊዳኙ ይገባል:: ክልሎች በሕግ የሚፈለግን አካል አሳልፌ አልሰጥም ማለት የሕግ በላይነትን አለማክበር ነው:: ወንጀሉን ፍርድ ቤት የሚዳኘው ጉዳይ ቢሆንም ማንም ኢትዮጵያዊ በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጪም እየታደነ ለሕግ ሲቀርብ ተመልክተናል:: እነዚያ አገሮች ወንጀለኛውን አሳልፈው የሰጡት በሕግ የበላይነት ስለሚያምኑ ብቻ ነው:: ለሕግ የሚፈልግ ግለሰብ ሆነ የሕግ አካል ሥራው ሁሉ ሕግ ሕግ ብቻ ሊሸት ይገባል:: በሕግ ሽፋን የፖለቲካ ሊሠራ አይገባውም::

ዛሬም እንደትላንቱ ሕግና ፖለቲካ በመደባለቁ ምክንያት በክልሎች መካከል መቃቃር እየበረከተ ነው:: በጠቅላይ አቃቢ ሕግ እና በትግራይ ብሔራዊ ክልል መካከል አቶ ጌታቸው አሰፋን አስረክቡ አናስረክብም ክርክር የመጣው ሕግና ፖለቲካ በመደበላለቁ ምክንያት ነው ይላሉ አንዳንድ ፖለቲከኞች:: እንዲህ አይነት ፖለቲካና ሕግን ማደባለቅ ለዘለቄታው የሚያስኬድ ጉዳይ አይሆንም:: ምንጊዜም ሕግ የሁሉም የበላይ በመሆኑ ሁሉም ለሕግ ሊገዛ እንጂ ለብሔሩ ወገንተኝነቱን ሊያሳይ አይገባም:: ይህ ለአንድነታችን፣ለሰላማችን እና ለዴሞክራሲያችን መልካም አይሆንም:: እንደ አገር የሕግ በላይነትን ለማክበር አንድ ከሆንን ፀንተን እንቆማለን፣ በሕግ የበላይነት ላይ ከተከፋፈልን ማሳረጊያችን ውድቀት ይሆናል:: ስለዚህ ሕግን ማክበር ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ የሚታወቀውም በፖለቲካ አስተሳሰብ ቢለያይም ሕግን አክብሮ በመኖሩ ነው:: ይህ በደምና በአጥንት የተለሰነ የአገር ፍቅር ስሜት የአንድነቱ አንፀባራቂ ህያው ምስክር ዝም ብሎ የተገኘ ሳይሆን በየወቅቱ ለነበሩት መንግሥታት በሕግና በሕግ ብቻ በመመራቱ ነው::

አገር ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተቀባበለች እዚህ የደረሰችውም ለፊውዳሉም ይሁን ለአምባገነን መንግሥታት ሕግና ሥርዓት ተገዢ እየሆነ በመኖሩ ነው:: ጨዋውና አስተዋዩ ሕዝብ ከምንም በላይ ሕግ አክባሪ ነው:: ከዚህ ቀደም ከሳሽና ተከሳሽ ያለ ፖሊስ ነጠላቸው ብቻ ተቋጥሮላቸው በጋራ ወደ ሕግ አካል የሚሄዱበት መልካም የሕግ እሴት የነበረን ሕዝቦች ነን:: በተለያዩ ዘመናት ይህ ምሥጉን ሕግን በተግባር ማሳየቱና በማስቀጠሉም አሁን ያለንበት ዘመን ላይ

◀ እንድንደርስ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል:: ይህ አርቆ አሳቢ ሕዝብ በደግም ሆነ በክፉ ጊዜያት ከፖለቲካ በላይ ሕግን በማክበር አንድ የሚያደርጉት በርካታ የጋራ ጉዳዮች ስለነበሩ አገሩን ለዚህ ትውልድ አስረክቧል:: ይህ ትውልድም ከምንም ነገር በላይ ይህንን ሕግን የማስከበር አኩሪ እሴት የማስጠበቅ ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት::

በአገራችን በአሁኑ ሰዐት በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ከፈጠሩ ችግሮች አንዱ የፍትሕ ሥርዓቱ ተጠቃሽ ነው:: ዓቃቤ ሕግ መከሰስ ያለበትን አይከስም:: መከሰስ የሌለበትን ግን ፍርድ ቤት ገትሮ መከራ ያሳየዋል:: ያላግባብ ተከሰው ፍርድ ቤት የሚመላለሱ ያሉትን ያህል፣ ክሳቸው ተቋርጦ በነጻ የሚሰናበቱ ስንቶች በብዛት ታይተዋል:: 'አንድ ንፁህ ሰው ያላግባብ ከሚታሰር ይልቅ አንድ ሺህ ወንጀለኞች ቢለቀቁ ይሻላል' የሚለው የሕግ መርህ እየተጣሰ በርካታ በደሎች የደረሱባቸው አሉ:: በጉልበተኞች ንብረታቸውን የተቀሙ፣ ሰብዓዊ ክብራቸው የተደፈረ፣ በተከበሩበት አገር የተዋረዱ፣ ያለጥፋታቸው የመከራ ገፈት እንዲቀምሱ የተደረጉ፣ ወዘተ በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ ከጥርጣሬ አልፎ ጥላቻ ቢፈጠርባቸው ምን ይገርማል?

ሁሉም ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ አመለካከት ቢለያዩም በሕግና በእኩልነት የሚኖሩባት አገር ለመገንባት መነሳት እንጂ፣ ብሔር ላይ እየተለጠፉ፤በብሔር ስም ከጥፋታቸው ነጻ ለመውጣት ራስን መከላከልም ሆነ ቢጤዎችን ከፍትሕ ለማሸሽ መሞከር በሕግ ከማስጠየቅ አያርቅም::

የሀገሪቱ ችግሮች የሚመነጩት በሀገራችን የሕግ የበላይነት ባለመኖሩ ብቻ ነው:: የሕግ የበላይነት የለም ማለት ደግሞ ፍትሕ የለም ማለት ነው:: እስከዛሬ ድረስ ይቺን ሀገር ያስተዳደሩና የገዙ መንግሥታት አንዱ ትልቁ ችግራቸውና ድክመታቸው እንዲሁም ሊወቀሡበት የሚገባቸው ከፓርቲና ከመንግሥት ተፅዕኖ ነጻ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን አለመፍጠራቸው ነው:: አሁንም እነዚህ የሉም። ምናልባት ሙከራዎች ሊደረጉ ይችላሉ እንጂ ነጻ ተቋማት ዛሬም የሉም:: ወደፊትም በሥልጣን ላይ የሚቀመጡ ሰዎች ይህንን ልብ ሊሉት ይገባል:: ‹‹እኛ›› እና ‹‹እነሱ›› እየተባባሉ ከሕግ ያለፈ የፖለቲካ ድብብቆሽ በሕዝብና በሕግ ላይ መጫወት ሕገ ወጥነት ነው:: ማኅበራዊ ፍትሕ የነገሠባት አገር ለመገንባት መነሳት እንጂ፣ የብሔር ፖለቲካ ካርታ እየመዘዙ መቆመር ለዛሬው ትውልድ አያዋጣም:: የሕግ የበላይነት እንዲከበር እንጂ፣ ሕግ እንዲጣስ ማደፋፈር የከፋ ሕገወጥነት ነው:: የተጠያቂነት ዳር ድንበር በግልጽ ይሰመር የሚባለው ለዚህ ነው!

ዛሬ በሀገራችን በአንዳንድ ክልሎች እንደምናየው የሕግ የበላይነት ካልተረጋገጠ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይቅሩና ሰብአዊ መብቶች በጠራራ ፀሐይ ሊጣሱ ይችላሉ:: በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ሰዎች በዘራቸው ብቻ ከመኖሪያ ቤታቸው እየተጎተቱ ተገድለዋል፤ መኖሪያቸውና ቤተ ዕምነቶቻቸው ተቃጥለዋል፤ በርካታ ዜጎች ያለሃጢያታቸው ተደብድበዋል፤ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፤ ንብረታቸውን ተዘርፏል። ሀገሩ የእኛ ብቻ ነው ብለው ያሰቡ ወይም እንደዚያ የተነገራቸው አካሎች በዘር ወይም በቋንቋ ወይም በአስተሳሰብ ተለይተውናል ፣እኛን አይመስሉም ያሏቸውን አናሳ ወገኖች እንደፈለጉ ሲያጠቁ ሲዘርፉና ሲያዘርፉ ተመልክተናል። ለዜጎች ደህንነት የመጀመሪያው ተጠያቂ መንግሥት ይሁን እንጂ ኅብረተሰቡም ኃላፊነት ሊሰማው ይገባል።

የሕግ የበላይነት መከበር ለሀገር ሰላምና መረጋጋት ብሎም ልማትን ለማሳለጥ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የሕግ የበላይነት ከሌለ ሰላም የሚባልን ነገር ማሰብ አይቻልም። ሰላም ከጠፋ ደግሞ ስለ ልማትና ዴሞክራሲ ማሰብ አይቻልም። ፀረ ልማታዊነትና ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ቦታውን ይረከባሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ እንደ እኛ ሰላምን፣ ልማትንና ዴሞክራሲን የኅልውናው ጉዳይ ላደረገ ሀገር አሜኬላ እሾህ መሆኑ አያጠያይቅም።

የሕግ የበላይነት ሲረጋገጥ ሰላምን እንጎናፀፋለን። ሰላምን ስንጎናፀፍ ደግሞ የምንመኛቸውን የልማትና የዴሞክራሲ ሥራዎችን ዕውን እናደርጋለን። ሕጎች ለአንዱ የሚሰሩ ለሌላው ደግሞ የማይሠሩ ሊሆኑ አይችሉም። ሁላችንም በሕግ ፊት እኩል እንስተናገዳለን። የሕግ የበላይነት ሲኖር ሁላችንም ከሚገኘው ሀገራዊ ጥቅም እኩል ተካፋዩች እንሆናለን። እናም እንደ ማንኛውም ዴሞክራሲን የሚከተል አገር የሕግ የበላይነትን ማክበር እንጂ ሕግንና ፖለቲካን እያደባለቁ ሕግና ሥርዓት እንዲጣስ ማድረግ፤ የማያዋጣ መንገድ እንደሆነ ታውቆ ሕግንና ፖለቲካን አራርቆ ማስቀመጥ ይገባል እንላለን።

ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር

# የሞራል...

ከገጽ 28 የዞረ

አይኖረውም። ይህ ከሆነ ዘንዳ የርሱ ፍላጎት ቅቡል እንዲሆን የሌላውን ፍላጎት ሳያወላዳ የመቀበል ግዴታ እንዳለበት ያምናል ማለት ነው። በመሆኑም እንደ ማኅበረሰብ አሁን ላለንበት ተጨባጭ ፍላጎታችን ምን እንደሆነ እንኳን ጥርት ባለ መልኩ ባለማወቃችን አለያም ሚዛን አልባ በሆነ ፍላጎት በባዶ ሜዳ የመዋለል ስሜት እንደሆነ ይጠቁማል።

## ብስለት /Intelligence/

እንደ ሥነልቦና ባለሙያዎች ገለጻ ብስለት በሁለት ዋናዋና ክፍሎች ይጠቃለላል። የአዕምሮ ብልህነት(IQ) እና የስሜት ወይም ግንዛቤ ብልህነት( Emotional Intelligence)። የአእምሮ ብስለት እውቀትን የማከማቸት አቅም ማደግ ሲያሳይ የግንዛቤ ብስለት ደግሞ አንድም እውቀቱን እንዴት እንደሚጠቀመው አለያም ካወቀው በመነሳት አዲስ ነገር እንዴት መፍጠር እንደሚችል ማሰብ መቻል ነው። በመሆኑም እውቀቱን አከማችቶ ግንዛቤ/ ማስተዋል ከሌለው ሰውነቱ ጎደሎ በመሆኑ የሌሎችን ፍላጎት በማድመጥና በማክበር የራሱን ፍላጎት የሚያስፈጽምበትን ስልት በብስለት ከመቀየስ ይልቅ በመግቢያው እንደገለጽኩት በቁሳዊ ማንነቱ በመተማመን ብቻ በደመነፍሳዊ ምሪት ሰብኣዊነት የጎደለው ውጤት ያስከትላል። በመሆኑም ማኅበረሰባችን አሁን ላለበት የእርስበርስ እልቂትና ትንቅንቅ የማስተዋል ብስለቱ መውረድ መሆኑን ያመላክታል።

## ሀብት/ Resource/

ይህኛው ከመጀመሪያው ምክንያት ጋር በከፊል የሚገናኝ ሲሆን የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጉትን ቁሳዊ ግብአቶች ያሳያል። እንደ ምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች የሰው ልጅ ፍላጎት ማለቂያ የሌለው ሲሆን የተፈጥሮ ሀብት ደግሞ የተገደበ ነው። በመሆኑም ሁሉንም ፍላጎቶቹን የሚያሟላ የተፈጥሮ ሀብት ባለመኖሩ ያለውን ይቀራመታል። በዚህ ሽሚያም የፍላጎት ግጭት ይፈጠራል። ይህን ግን ሊያስታርቀው የሚችለው የማስተዋል ብስለት /Emotional Intelligence/ ነው። ይህም የሰው ልጅ የተሰጠውን ግድብ ሀብትን በብልሀት የመጠቀም አስተውሎትን በማዳበር በሚዛናዊ ፍላጎት ያልተገደበ ሀብት በመፍጠር በትንሽ ከባቢ ሰፊ ዓለም እንደመፍጠር ማለት ነው።

በዚህ ጽንሰሐሳብ ማኅበረሰባችን ያለችውን ሀገር ከማሳደግ ይልቅ ወደማፍረስ ለመሄዱ የተሻለ ማስተዋልና አርቆ የማሰብ ክህሎት ማጣቱ እንደሆነ ያሳያል።

## ከባቢ፣ ባህል እና ቋንቋ

ይህ የሰው ልጅ እራሱን ከሚገልጽባቸው መንገዶች አንደኛው ሲሆን በአስተዳደጉ ሂደት ተጽእኖ ያሳደሩበትና የገነቡት ንጥረ ነገሮች/ግብአቶች ተደርገው ይወሰዳሉ።

እንደ ማኅበረሰብ ሥራ ባለሙያዎች ገለጻ የሰው ልጆች ተፈጥሯዊም ማኅበራዊም ስሪትም እንደሆነ ይገልጻሉ . ይህም ተፈጥሯዊው ስሪታቸው ተጽእኖ እንደሚኖረው ሁሉ ማህበራዊ ስሪታቸውም ተጽእኖ ይኖረዋል እንደማለት ነው።

በመሆኑም ሰካራም፣ ቁማርተኛ፣ ዝሙተኛና ቀማኛ አካባቢ የሚያድግ ልጅ ባብዛኛው አካባቢውን የሚመስል እንደመሆኑ በእውቀትና በስራ የተከበበ አካባቢ ውስጥ የሚያድግም በመሰሉ ባህሪ እንደሚቀረጽ እሙን ነው።

አስተዳደጋችንን እንደ ምሳሌ ብንወስድ "ልጅ እንቁላል አይበላም" "ሴትና ልጅ ወደ ማጀት?" በሚል ባህላዊ ትውፊት ተከበን፣ ቤተሰቦቻችንም የሚሹትን እንድንፈጽም ከምክንያት ይልቅ ቁርጥ ባለ ትእዛዝና ዱላ ያደግን በመሆኑ በልጅነት የሀሳብ ነጻነት መነፈጋችን ማሳያ ነው። ይህም ዛሬ ትልቅ ሆነን ሀሳባችንን በግልጽና ቀጥተኛ በሆነ መልኩ እንዳንገልጽ አለያም ልሳናችን አንዴ ከተፈታም ከዴሞክረቲክ ነጻ የሀሳብ ሽያጭ ይልቅ እንደ አስተዳደጋችን አፋኝና ጨቋኝ የመሆናችንን በዚሁም አሁን ላለንበት ተጨባጭ እንዳበቃን ማሳያ ነው።

በመጨረሻም ባህላችን ብዙ መልካም መገለጫዎች ያሉት በመሆኑ ጎጂ ባህሎችን በማስወገድ መልካሙንም ለግለሰብ፣ ለማህበረሰብና ለሀገር ግንባታ እንዲውል በማጠናከር ከሌላ የዓለም ክፍልና የዕውቀት ማዕዶች የምናገኘውን መልካሙን በማከል ወደተሻለ ደረጃ መሸጋገር የምንችል መሆኑን ለመጠቆም ወደድኩ።

ሰላም!



ሐሙዲ:

# የሞራል እና የቁስ ልእልና ልሽቀት

ውይይት የሰው ልጅ የተለያየ ሀሳብና አመለካከቱን የሚለዋወጥበት፤ መረጃዎች በሁለትዮሽ ቃለምልልስ የሚንሸራሸሩበትና የሚመዘኑበት፣ በዚሁም የተሻለው ገዢ ሀሳብ የበላይነት የሚያገኝበት የሀሳብ መድረክ ነው። የሰው ልጆች ከሌላው ፍጥረት የሚለዩበት ትልቁ ነገር አእምሮ ነው። ሆኖም ሁሉም ሰው አንድ አይነት አስተሳሰብ አልተሰጠውም። እንደ ቋንቋው፣ እንደቀለሙና ተክለቁመናው የማንነቱ ማዕከል የሆነው አስተሳሰቡም ይለያያል። በመሰረቱ ሰዎች በተፈጥሮ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ይዘው ቢፈጠሩ ኖሮ ዓለም ምን ልትመስል እንደምትችል አስበዋል? ሰውን ሰው ያስባለው አስተሳሰቡ ከሆነና በዓለማችን አንድ አይነት አስተሳሰብ ካለ አዲስ ነገር የለም ማለት ነው። በመሆኑም ዓለም ስትፈጠር ባለችበት ሁኔታ እንድትቆይ ትገደድ ነበር። ይልቁንም አንድ ሀሳብ ከሌላኛው ሀሳብ ጋር ሲዋሀድ ሌላ አዲስ ሀሳብ ይወለዳል፤ በዚሁም አዲስ ቅኝት አዲስ ግኝት ይፈጠራል። ዓለምም ከትላንት ዛሬ፣ ከዛሬ ነገ፣ በአዲስ አስተሳሰቦች፣ አዲስ ቅርጽ እየያዘች ትሄዳለች።

የዓለምን ታሪክ ብናጠና ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሏ እሙን ነው። ለውጧም በዋናነት ቁሳዊና ሞራላዊ/ግብረገብ ብለን ልንከፍለው እንችላለን። ይህን የሚወስነው የአስተሳሰብና ሀሳብ ልውውጥ ደረጃ ሲሆን ምህዋሩ ሚዛናዊ ከሆነ በሞራልም ሆነ በቁሳዊ ለውጥ ተመጣጣኝ መሻሻል እንደሚመጣ ይጠበቃል። ይህ ሳይሆን ሲቀር አንዱ ከፍ አንዱ ዝቅ የሚል ሲሆን የሚከተለው ሚዛን መሳት አሉታዊ ውጤትን ይፈጥራል።

ከለውጥ ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ የምንሰማቸውን ሁለት ቃላቶች ላንሳ፣

## 1. ሉላዊነት (Globalization)

ጆን አርት የተባሉ ምሁር ሥልጣኔን "ማኅበራዊ ትስስር ወይም በሰዎች መካከል ያለ አዎንታዊ መስተጋብር እንደሆነ ይገልጹታል።

በመሆኑም በቁሳዊ ፈጠራዎች መበልጸግ የአእምሮን ምጥቀትን የሚያሳይ ሲሆን ይኸውም የአንድን ማኅበረሰብ እድገት ማሳያ ነው። ነገር ግን በዚያው ልክ ሞራላዊ አስተሳሰቡ ካልበለጸገ፣ ደመነፍስ በአእምሮ ላይ የበላይ ይሆንና ቁሳዊ ብልጽግናው ለማኅበራዊ ትስስር ጥፋት ምክንያት ይሆናል። ለዚሁም ነው በአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች ቁሳዊ ስልጣኔ ጫፍ ደርሶ በዚያው እኩል የበለጸገው የግንዛቤ ብስለት ከሰው አልፎ ለእንስሳት መብት መከበር ዘብ የሚያስቆመው፤ በተመሳሳይ በቁሳዊ እድገት ቢበለጽጉም ወደኋላ በቀረው የግንዛቤ ብስለት ሳቢያ አእምሮ በፈጠረው ቁስ የሰው ልጅ ነፍስ እንደቅጠል የሚረግፈውና ሰብኣዊነት የሚረክሰው፤በአሁን ጊዜ በሁለቱም እድገት ወደኋላ የቀረው የዓለማችን ክፍል የአፍሪካ አህጉር ሲሆን ከፍተኛ ድህነት፣ ረሀብና የእርስበርስ እልቂት ዋነኛ መገለጫዎቹ እንደሆኑ ግልጽ ነው።

እርግጥ ነው፣ የዓለምን ታሪክ ላጠና ሰው በሆነ ጊዜ በሞራልም ሆነ በቁስ አለያም ከሁለት በአንዱ በልጽገው የነበሩ ሀገራት በሌላ ጊዜ ተሽመድምደው ይታያሉ። በተቃራኒውም እንዲሁ። ይህ የሚያሳየው ሥልጣኔ እንደ እያንዳንዱ ሀገር ተተኪ ትውልዶች እድገት የሚወሰን መሆኑ ነው። የሀገራችንንም ተጨባጭ ሁኔታ በዚህ መልኩ መፈተሽ እንችላለን።

## 2. ውህደት፣ማህበራዊ ትስስር (Integrity)

ይህ በአብዛኛው የሰው ልጆች ከሌላው ፍጥረተ ዓለም የሚለዩበት የማሰብ ውጤት ሲሆን የአንዱ ሰው ሀሳብ ከሌላው ሰው ሀሳብ ጋር ተምሮ በሚገኘው አዲስ ሀሳብ ሁለቱም ሰዎች አንድ ሀሳብና አቋም የሚያራምዱበት ሂደት ነው። ይህም በፍልስፍናው እሳቤ ሁለት አንድ ቁጥሮች ባይኖሩ፣ ሁለት ቁጥርን መፍጠር አይቻልም ነበር ፤ስንል መጀመሪያ የተለያየ አንድ ቁጥር የነበሩት በስያሜ ተመሳሳይ እንጂ በይዘት አንድ እንዳልነበሩና በሂደት ፣በስያሜም ፣በይዘትም አንድ እንደሆኑ ማሳያ ነው።

በሌላ አገላለጽ እያንዳንዳቸው አንዶች የራሳቸው የሆነ መገለጫ ያላቸው ሲሆን ወደ ሁለት ለመምጣት እያንዳንዳቸው አንድ ነገር ሰጥተው በመቀበል የከፈሉት መስዋእት አለ ማለት ነው።

የሥነመለኮት ተመራማሪው ዓለማየሁ ፋንታሁን በግንቦት 2001 ዓ.ም በሁለተኛ ዲግሪ የማሟያ ጽሑፋቸው እንደገለጹት "ብዝኃነትና አንድነት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ከአብላጫ/ Majority/ እና ከአናሳ/ Minority/ ድምጽ ጋር አያይዘን ማየት እንችላለን። ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊሰደዱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የትም ቢሄዱ ሰውነታቸው የሚቀድም በመሆኑ ለዚሁ ክብር ሲባል ድምጻቸው ይስተናገዳል። በመሆኑም በኖርዌይ ሀገር የሚኖሩ ስደተኞች በአናሳ ድምጽ ባለቤትነትም ቢሆን በራሳቸው ማንነት ላይ የተመሰረተው ሀሳባቸው ሊሰማ ግድ ይለዋል። ለዚሁም ሲባል የውህደት ፓሊሲ/Integration Policy/ በስደተኛ ዳይሬክቶሬት የሚመራ ሆኗል።

ይህ የሚያሳየን እንደ ኖርዌይ ያሉ ሥልጡን ሀገራት የሌላውን ሰው ባህል፣ ወግና ማንነት ለማክበር የሄዱበትን ርቀት ሲሆን በእኛ ሀገር አንዱ ብሔር ከሌላው ጋር የሚኖረው መስተጋብርና የመከባበር ደረጃ ከምን እንደ ደረሰ ለመታዘብ ያስችለናል። እርግጥ ነው የትላንት

> **የአእምሮ ብስለት እውቀትን የማከማቸት አቅም ማደግ ሲያሳይ የግንዛቤ ብስለት ደግሞ አንድም እውቀቱን እንዴት እንደሚጠቀመው አለያም ካወቀው በመነሳት አዲስ ነገር እንዴት መፍጠር እንደሚችል ማሰብ መቻል ነው**

ታሪካችን ከላይ በጠቀስነው ቁሳዊም ሆነ ሞራላዊ ሥልጣኔ ታላቅ የነበርን መሆናችንን ያመላክታል። ሆኖም ከተወሰኑ ክፍለዘመናት ወዲህ ከተለያዩ ግዛቶች ወደ አንድ ውህደት መጥተን እንደ ሀገር ለመቆም ባደረግነው ጥረት የኢትዮጵያችንን መልካምድር ምሉእ ማድረግ ቢቻለንም ቁሳዊም ሆነ ሞራላዊ ሥልጣኔያችን ከትላንት ዛሬ እየተንኮታኮተ ለመውረዱ ምንም ጥርጥር የለውም።

የትላንቱን ታሪካችንን ስናወራ ሁሉም ብሔር ብሔረሰብ በአንድ ወቅት የራሱ የሆነ ቁሳዊና ሞራላዊ ሥልጣኔ እንደነበረው ይታወቃል። ሸንጎ፣ ዳጉ፣ ገዳና መሰል የፍርድና የመግባቢያ ስርአቶች ለዚህ ማሳያ ናቸው። ታዲያ ያ ሁሉ ስልጣኔ፣ ያ ሁሉ መከባበር የት ገባ? ምክንያቶቹስ ምንድን ናቸው?

## ፍላጎት/ Interest/

ሁሉም ሰው የራሱ የሆነ ፍላጎት አለው። ይህም ማለት ከሌላኛው ሰው ጋር በሚኖረው ግንኙነት ማግኘት የሚፈልገው ወይም እንዲሟላለት የሚሻው ቅድመ ሁኔታ ነው። ማንነቱ ለተገነባበት አስተሳሰቡ መደመጥና መከበር ትልቁ መሻቱ ነው። ይህ ደግሞ ቁሳዊውንም ሞራላዊም ፍላጎቶቹን ያጠቃልላል። በመሆኑም ከሌላው ጋር ለመደመር ቅቡልነትን በመሻት እንጂ የርሱ ተጥሎ የሌላውን ለመቀበል የሚያስችል ልቦና

ቀሪውን በገጽ 27 ይመልከቱ

# ግዮን መጽሔት

## በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት

መጽሔታችን ከተጀመረች ጀምሮ የእናንተ ውድ አንባቢያን አቀባበልና አስተያየት ሳይለየን ቆይተናል። በአዲስ ዓመት በአዳዲስ አምዶች

**ትምህርት፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያሳያል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ፍኖተ ካርታን በተመለከተና ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች

**ኢትዮጵያዊነት፡-** አገራችን የአንድነት ጉዞ በምትጀምርበት ወቅት ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ እናቀርባለን።

በእነዚህ አምዶች ላይ ባለሙያ የሆናችሁና የተለየ ሀሳብ አለን የምትሉ ተሳታፊዎች በኢሜል ፅሁፍ መላክ ትችላላችሁ።

በልዩ አቀራረብ፣ በአዳዲስ አምዶችና በሳል ፀሃፊያን በመታገዝ

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!






+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.faceboook.com/enqu2013
Facebook
Gihon-meg Fekadu

ኢ-ሜይል፡
enqu2013@gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com